# ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ

መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

በአሜሪካ አገር በሜሪላንድ ግዛት
ቦልቲሞር ከተማ ተጀምሮ በብሪታንያ ለንደን ከተማ
ባራክ ኦባማ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾኖ በተመረጠበት ዕለት
ተጠናቀቀ።

ጥቅምት ፳፭ ቀን ፳፻፩ ዓ. ም.
November 4, 2008

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

© 2008 BY Melak Berhan BERHANU
BISRAT
All Rights Reserved


ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት ኃላ. የተ. የግ.ማ.
H.Y International Printing Enterprise Pv.Ltd. Co.
P.O.Box 50676
Addis Ababa, Ethiopia

ይህን መጽሐፍ ለመግዛት
እንዲሁ ስለጽሑፉ አስተያየት
ከዚህ በታች ባለው አድራሻ መገናኘት ይቻላል።

P.O.Box 24842 Code 1000

E-mail address
berhanukes@yahoo.co.uk

ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ



ለእናቴ
ለወይዘሮ ጥሩወርቅ በረደድ ወልደጊዮርጊስ

ልጇ ዓለማየሁ ተፈራ በወጣትነቱ በሰረፍተ ሞት ስለተለያት
ይህ መጽሐፍ መታሰቢያው እንዲኾናት አበርክቼላታለሁ።

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
© 2008 BY Melak Berhan BERHANU
BISRAT
All Rights Reserved

ኤች ዋይ ኢንተርናሽናል የኅትመት ሥራ ድርጅት ኃላ. የተ. የግ.ማ.
H.Y International Printing Enterprise Pv.Ltd. Co.
P.O.Box 50676
Addis Ababa, Ethiopia

ይህን መጽሐፍ ለመግዛት
እንዲሁ ስለጽሑፉ አስተያየት
ከዚህ በታች ባለው አድራሻ መገናኘት ይቻላል።

P.O.Box 24842 Code 1000

E-mail address
berhanukes@yahoo.co.uk

ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ



ለእናቴ
ለወይዘሮ ጥሩወርቅ በረደድ ወልደጊዮርጊስ

ልጇ ዓለማየሁ ተፈራ በወጣትነቱ በሰረፍተ ሞት ስለተለያት
ይህ መጽሐፍ መታሰቢያው እንዲኾናት አበርክቼላታለሁ።

## ምስጋና

ይህ ጽሑፍ ተጀምሮ እስኪፈጸም በሐሳብና በጉልበት የተራዱትን ኹሉ ከልብ አመሰግናለሁ ። ይልቁንም በሐዋርያዊ አገልግሎቴ እንድተጋ እና ይህን ጽሑፍ ስጽፍ ላበረታታችኝ ለባለቤቴ ፤ ለወይዘሮ መቅደስ ወርቅ ዓለሙ፤ ለልጆቼ፤ ለዲያቆን ለይኩን ብርሃኑ፣ ለዲያቆን ትንሣኤ ብርሃኑ እና ለወይዘሪት ማኀሌት ብርሃኑ ምስጋናዬ በጣም ከፍ ያለ ነው።

የመጽሐፉን ረቂቅ አንበው እጅግ ጠቃሚ የኾኑ አስተያየቶች የሰጡኝን እንጂነር ከበደ ኀበናን እና አቶ መኩንን ወዳጄነህን ከልብ አመሰግናለሁ።

ረቂቁን በማንበብ በሐሳብ ሲራዱኝ ቆይተው የዚህን መጽሐፍ ውጤት ሳያዩት "መሬት ነኽና ወደመሬት ትመለሳለህ" (ዘፍ. 3፥19) በተባለው በእግዚአብሔር ሕግ በዐረፍተ ሞት ከዚህ ዓለም ለተለዩት ወዳጄ አቶ አድማሱ ጀመረ ከፍ ያለ ምስጋና ሳቀርብ እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በጻድቃን ነፍሳት ዘንድ ዐሳርፍልን በማለት እጸልያለሁ።

የመጽሐፉንሽፋን ዲዛይን ያደረጉልኝ አርቲስት ፍቅርተ በላይ ነህን እና ልጄ ትንሣኤ ብርሃኑን ፤ ፎቶ ኮፒ በማድረግ የተባበረኝን አቶ ዳዊት ሀብተ ማርያምን አመሰግናለሁ።

በአሜሪካ በወንጌል አገልግሎት የተባበሩኝ እና ይኽን ዝግጅቴን አስመልክቶ ገንቢ ሐሳባቸውን ለለገሡኝ ለቦልቲሞር ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ አባላት እና ምክትል ሊቀ-መንበር ለአቶ ሕይወት መንበረ ፤ እንዲሁ በዚያው አገር ሐዋርያዊ ተግባር ለመፈጸም ለተራዱኝ ለሊቀ ማእምራን ዶክተር አማረ ካሣዬና ለሊቀ ኅሩያን ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ባጠቃላይ መጽሐፉ ለኅትመት በቅቶ ለአንባቢያን እንዲደርስ በተለያየ መልክ ለተራዱኝ ኹሉ ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ኤች ዋይ ኢንተርናሽንል የኅትመት ሥራ ድርጅት ኃላ. የተ. የግ.ማ. ሥራ አስኪያጅ አቶ ሀብቴ ፈርሻ እና ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ይሳለሙሽ ተክሌ እንዲሁም የመሥሪያ ቤቱን ሠራተኞ ስለትብብራቸው በእግዚአብሔር ስም ከልብ አመሰግናለሁ:: እንዲሁም ለአቶ ታምራት ከበደ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::



## ማውጫ


መቅድም ........ 10
መግቢያ ........ 14

### ክፍል አንድ

ምዕራፍ ፩ ዐዲሲቱ ዓለም አሜሪካ ........ 18
(፩) ክርስቶፎር ኮለምበስ ........ 18
(፪) የሥልጣኔ ዘመናት አከፋፈል ........ 21
(፫) ሬኔሳንስ ........ 22
(፬) አሜሪጎ ቬስፑቺ ........ 25
ምዕራፍ ፪ የተሐድሶ ንቅናቄ በአውሮፓ ........ 25
(፩) ተሐድሶ በጀርመን ........ 26
(፪) ተሐድሶ በሲውዘርላንድ ........ 30
(፫) ተሐድሶ በእንግሊዝ ........ 32
ምዕራፍ ፫ የእንግሊዝ ተሐድሶ ወደ አሜሪካ መሰደድ ........ 37
(፩) የአራሽ ገበሬዎች ቡድን ........ 38
(፪) መንፈሳዊ ተጓዦች ........ 41
(፫) የአሜሪካ ተወላጆች ኢንዲያን ........ 45
(፬) ስብከተ ወንጌል ለኢንዲያኖች ........ 48
(፭) ቅኝ ገዥ የብሪታንያ መንግሥት ........ 49
(፮) 150 ዓመት የባርነት ስቃይ ........ 54

ምዕራፍ ፬ የአሜሪካውያን ነዋሪዎች የነጻነት ትግል ........ 59
(፩) የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን ........ 61
(፪) የነጻነቱ አዋጅ (ሐምሌ 4 ቀን 1776) ........ 65
(፫) ፕሬዚዳንት፤ ኩንግረስ እና የጸሎት ቤት ........ 68
(፬) ሕገ መንግሥት መርቀቅ ........ 70
(፭) የመብት ሕግ (BILL OF RIGHTS)መረቀቅ ........ 74
(፮) የነጻነቱ አዳራሽ ........ 76
(፯) የነጻነቱ ደወል ........ 76
(፰) የአሜሪካ ባንዲራ ........ 77
(፱) የአሜሪካ ማኅተም እና ዶላሩ ........ 78
(፲) ፪ኛ ፕሬዚዳንት ጆን አደምስ (ኮንግርጌሽናል) ........ 80
(፲፩) ፫ኛ ፕሬዚዳንት ቶማስ ጃፈርሰን (ኤጲስኮፓል) ........ 81
(፲፪) ፬ኛ ፕሬዚዳንት ጀምስ ማዲሶን (ኤጲስኮፓል) ........ 83
(፲፫) ፭ኛ ፕሬዚዳንት ጀምስ ማንሮ (ኤጲስኮፓል) ........ 84
(፲፬) ፮ኛ ፕሬዚዳንት ጆን ኩንሲ አደምስ (ዩኒቴርያን) ........ 86

(፲፭) ቤንጃሚን ፍራንክሊን (ኤጲስቆጶል) ........ 87

ምዕራፍ ፭ ጥቁር አሜሪካውያን ........ 88
(፩) ባርነት መጥፋት አለበት (አቦሊሽኒስት) ........ 92
(፪) ፍሬድሪክ ዳግላስ ........ 94
(፫) ሀሪይት ተብማን ........ 95

ምዕራፍ ፮ ሰሜን እና ደቡብ የሕዝቦች ጦርነት ........ 97
(፩) ፲፮ኛ ፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን (ባፕቲስት) ........ 99
(፪) የእርስ በእርስ ጦርነት ........ 103
(፫) የነጻነት ሕግና አዋጅ ........ 106
(፬) የጌትስበርግ ንግግር ........ 106
(፭) የፕሬዘዳንት አብርሃም ሊንከን ሞት ........ 108
(፮) ኩ ክላክስ ክላን ........ 110

ምዕራፍ ፯ ዐዲሲቷ አሜሪካ እና ስደተኞች ........ 112
(፩) በኒው ዮርክ የገቡ ስደተኞች ........ 114
(፪) የነጻነት ሐውልት ........ 118
(፫) ከላቲን አሜሪካ የገቡ ስደተኞች ........ 120
(፬) ካሊፎርኒያ የገቡ ስደተኞች ........ 120
(፭) ቻይናውያን በአሜሪካ ........ 121
(፮) ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ........ 122

ምዕራፍ ፰ የኢትዮጵያ ወዳጆች ........ 127
(፩) ማርቆስ ጋርቬይ ........ 127
(፪) ራስ ተፈሪያን ........ 132

ምዕራፍ ፱ የዓለም ጦርነቶች እና አግኝቶ ማጣት ........ 135
(፩) ፴፪ኛ ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሮዜቬልት (ኤጲስቆጶል)... 139
(፪) የጣሊያን ወረራና የኢትዮጵያ ድምጽ በአሜሪካ ........ 140
(፫) የጀርመን ወረራ ........ 146
(፬) ፴፫ኛ ፕሬዚዳንት ሀሪ ትሩማን (ባፕቲስት) ........ 150
(፭) አሜሪካ አይሁዳውያንን አሰፈረ ........ 151
(፮) ፴፬ኛ ፕሬዚዳንት ድ. አይሰንሀወር (ጆሆቫህ ዊ) ........ 153

ምዕራፍ ፲ የ20ኛው መቶ ክ. ዘመን የጥቁር መብት ተከራካሪዎች.... 158
(፩) ማርቲን ሉተር ኪንግ ........ 160
(፪) ኪንግ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው ትምህርት ........ 162
(፫) ኪንግ እና ሮዛ ፓርከር ........ 163


ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ


(፬) "መቀመጥ" (Sit-ins) ........ 167
(፭) የጥቁር እና የነጭ ትምህርት ቤት ........ 169
(፮) የቤርሚንገሃም ሰላማዊ ሰልፍ ........ 170
(፯) የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ሰላማዊ ሰልፍ ........ 171
(፰) ዐራት የሰንበት ተማሪዎች ሞት ........ 173
(፱) በጥቁርነቴ እኮራለሁ ........ 174
(፲) ማልኮልም ኤክስ ........ 175
(፲፩) ለዊስ ፋራካን ........ 178
(፲፪) የቨዬትናም ጦርነት ........ 178
(፲፫) የሜምፊስ ሞት ........ 180

ምዕራፍ ፲፩ ከፕሬዚዳንት ኬኔዲ በኋላ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ........ 185

(፩) ፴፭ኛ ፕሬዚዳንት ጆን ኦፍ ኬኔዲ (ካቶሊክ) ........ 185
(፪) ፴፮ኛ ፕሬዚዳንት ሊንደን ጆንሰን (ዲሳይፕል ኦፍ ክራይስት)... 191
(፫) ፴፯ኛ ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን (ኳከር) ........ 193
(፬) ፴፰ኛ ፕሬዚዳንት ጀራልድ ፎርድ (ኤጲስቆጶል) ........ 195
(፭) ፴፱ኛ ፕሬዚዳንት ጀምስ ካርተር (ባፕቲስት ቦርን አጌን)..... 196
(፮) ፵ኛ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬጋን (ዲሳይፕል ኦፍ ክራይስት).. 197
(፯) ፵፩ኛ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ሄርበርት ዎከር ቡሽ (ኤጲስቆጶል). 199
(፰) ፵፪ኛ ፕሬዚዳንት ዊልያም ጀፈርሶን ክሊንተን (ባፕቲስት).. 200
(፱) ፵፫ኛ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ዎከር ቡሽ (ሜተዲስት ቦርን አጌን). 202
(፲) ፵፬ኛ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ (ክራይስት ቸርች) ........ 208

ምዕራፍ ፲፪ አሜሪካንን የሚያጠቁ አደጋዎች ........ 215

(፩) ሚሲሲፒ ወንዝ ........ 216
(፪) ኃይለኛ የውሽንፍር ነፋስ (ኸሪኬን) ........ 217
(፫) ኃይለኛ አውሎ ነፋስ (ቶርኔዶ) ........ 220
(፬) ሰደድ እሳት ........ 221
(፭) የመሬት መንቀጥቀጥ ........ 222
ማጠቃለያ ........ 223

ኦሮና ክርስትና በአሜሪካ

## ክፍል ኹለት
## የክርስትና እምነት በአሜሪካ

### ኦርቶዶክስ


ምዕራፍ ፲፫ ኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ ............ 228
(፩) ግብፅ ኦርቶዶክስ (ቅብጥ) ............ 229
(፪) ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ............ 230
(ሀ) ዌስት ኢንዲያን እና አፍሪካን አሜሪካ ............ 231
(ለ) በኢትዮጵያ የለውጥ ዘመን ............ 234
(ሐ) ፬ኛ ፓትርያርክ እና ቅዱስ ሲኖዶስ በአሜሪካ ............ 235
(መ) ፭ኛ ፓትርያርክ እና ቅዱስ ሲኖዶስ በኢትዮጵያ.. 237
(ሠ) የካህናት ማህበር በአሜሪካ ............ 238
(ረ) የሰላም መልእክተኞች ወደ አሜሪካ ............ 240
(ሰ) ካህናት እና ምእመናን ጉባኤ በአሜሪካ ............ 241
(ሸ) ቀናው መንገድ ............ 243
(ቀ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ. ቤ. ክ. ቁጥር በአሜሪካ.246
(፫) አርሜንያ ኦርቶዶክስ ............ 250
(፬) የሶርያ ኦርቶዶክስ ............ 251
(፭) የሕንድ ኦርቶዶክስ ............ 252
ምዕራፍ ፲፬ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤ. ክ. በአሜሪካ ............ 253
(፩) ግሪክ ኦርቶዶክስ ............ 253
(፪) ሩስያ ኦርቶዶክስ ............ 254


### ካቶሊክ (1054)


ምዕራፍ ፲፭ ካቶሊክ ቤ. ክ. ............ 256
ካቶሊክ በአሜሪካ ............ 257


### ፕሮቴስታንት (1517)


ምዕራፍ ፲፮ ፕሮቴስታንት ............ 260
(፩) ሉተራውያን በአሜሪካ ............ 262
(ሀ) ሉተራውያን ቸርች ሚዙሪ ሲኖዶስ ............ 262
(ለ) ዊስኮንሲን ኢቬንጀሊካል ሉተራውያን ሲኖድ ............ 263
(፪) አንግሊካን በአሜሪካ ............ 264
(ሀ) ኤጲስኮፓል ............ 265
(፫) የእስኮትላንዱ ፕሬስቤተርያን ............ 267
(ሀ) ዳች ተሐድሶ ............ 268
(፬) ሜተዲስት በአሜሪካ ............ 269
(ሀ) አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ............ 270
(ለ) አፍሪካን ሜተዲስት ኤጲስኮፓል ዛዮን ............ 271
(ሐ) ሳልቬሽን አርሚ በአሜሪካ ............ 271
(፭) አናባፕቲስት 1525 ............ 272
(ሀ) ሜኖናይት ............ 272
(ለ) አሚሽ ............ 273
(ሐ) ብራዘር ኢን ክራይስት ............ 274
(፮) ኮንግሬሽናሊስት ወይም ፒሩታንስ ............ 275
(ሀ) ዩናይድ ቸርች ኦፍ ክራይስት ............ 275
(ለ) ዩኒቴርያኒዝም ............ 276
(፯) ባፕቲስት በአሜሪካ ............ 276
(ሀ) ባፕቲስት ቦርን አጌን ............ 278
(ለ) ናሽናል ባፕቲስት ኮንቬንሽን ............ 279
(ሐ) ጀነራል አሶሴሽን ሬጉላር ባፕቲስት ............ 279
(መ) ሳውዝ ባፕቲስት ኮንቬንሽን ............ 280
(፰) ኳከር ............ 280

ምእራፍ ፲፯ በአሜሪካ የተፈጠሩ የአገር ተወላጅ ሃይማኖቶች ............ 281
(፩) ሞርሞን ............ 281
(፪) ሰባተኛው ቀን አክባሪ (ሰቨን ዴይ አድቬንቲስት) ............ 285
(፫) የሀዋ ምስክር (ጆሆቫህ ዊትነስ) ............ 287
(፬) ክርስቲያን ሳይንቲስት (ቸርች ኦፍ ክራይስት) ............ 288
(፭) ጰንጠቆስጤ ............ 289
(፮) ሜጋ ቸርች ............ 291
(፯) ሞትሮፖሊታን ኮምኒቲ ቸርች ............ 292
(፰) ቸርች ኦፍ ሳይንቶሎጂ ............ 293
(፱) ፋንዳሜንታሊዝም እና ክራዝማቲክ ............ 294

ምእራፍ ፲፰ ፕሮቴስታንት በአሜሪካ እና በኢትዮጵያ ............ 295
(፩) በአሜሪካ ኢትዮጵያውያን ፕሮቴስታንት ............ 297

ምእራፍ ፲፱ ወደ ኦርቶዶክስ መመለስ ............ 299
(፩) ፋዘር ፒተር ኢ. ጊልክስት ............ 299
(፪) ቤነዲክት (አባ ዮሐንስ) ............ 300
(፫) ወጣት ታንያ ............ 302
ምእራፍ ፳ ማጠቃለያ በፍጻሜ ዘመን ............ 304
የአሜሪካ ካርታ ............

# መቅድም

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አሜሪካ የኼድኩበት ዓላማዬ አገር ለማየትና
ዘመድ ፥ ጓደኛ ለመጠየቅ ነበር። በዚህም አጭር ቆይታዬ በትንሹ የተ
መለከትኩትን በብዙ አድንቄ ተመለስኩ ። ይህ ቆይታ ለበጎ ኾኖ ጌታ
ችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሑሩ ወመሀሩ" ኺዱና አስተ
ምሩ (ማቴ. 28፥19)፤ ብሎ ባዘዘው ትዛዝ መሠረት ፤ በድጋሚ በዚሁ
አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ መንፈሳዊ አገልግሎት ለማበ
ርከት በቦልቲሞር ከተማ በሚገኘው የደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ
ቤተ ክርስቲያን ማገልገል ጀመርኩ። በዚያም ሐዋርያዊ ተግባሬን በመ
ፈጸም ላይ ባለኹበት ወቅት ላይ ላዩን አድንቄ ከማለፍ ይልቅ አንዳ
ንድ ነገሮችን ጠለቅ ብዬ ለመረዳት ጉጉት እያደረብኝ ኼደ።

ከመንፈሳዊ አገልግሎት በኋላ በተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቼ
እና ወዳጆቼ ቤት እየተገኘኹ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ
የሓሳብ ልውውጥ አደርግ ነበር። ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የኾነኝም ሓሳብ
የተፀነሰው በአሜሪካ ውስጥ የአብያተ ክርስትያናት ሕንጻዎች በዝተው
መታየትና በእግዚአብሔር እናምናለን (IN GOD WE TRUST) የሚ
ለው በአሜሪካ ገንዘብ (ዶላር) ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ምእመናኖችን
ሲያከራክር በተመለከትኩበት ወቅት ነበር ፤ እውነት የዚህ ኅብረተሰብ
እምነት የተመሠረተው በእግዚአብሔር ላይ ነው ? ወይስ ዶላር ላይ
በጽሑፍ በመስፈር የሚታይ ከንቱ ውዳሴ ? የሚለው ጥያቄ በኅሊናዬ
ተፀንሶ እንዳስብበት አደረገኝ።

ለረዥም ዘመን በእግዚአብሔር እምነት ላይ የተመሠረተ ጽኑ
ሃይማኖት ያላት አገራችን ኢትዮጵያ ገንዘብ ላይ ይህ ለምን አይ
ታይም? የሚል ሓሳብ በአእምሮዬ ተጉላላ። እንደ ዛሬው ሳይኾን ፤
ከንጉሥ ኢዛናና ከዐፄ ካሌብ (4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን) ጀምሮ እስከ
ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ድረስ ያሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት በገንዘቦቻቸው
ላይ የክርስትና ምልክት የኾነው መስቀል ተቀርጸባቸው እንደነበረ
ተረዳሁ።[1]

አንድ ዶላር ላይ ያለው የማን ፎቶ ግራፍ ነው? ዐምስት ዶላሩ
ላይ ያለውስ ? የሚለው ጥያቄ ወደምርምር ጥናት ወሰደኝ። አንድ
ዶላር ላይ የሚታየው ምስል አሜሪካውያን "የአሜሪካ አባት" ብለው

[1] African Zion the sacred art of Ethiopia p. 107 London 1993



የሚጠሩት ጆርጅ ዋሽንግተን መኾኑን ተረዳሁ ። አምስት ዶላሩ ላይ
ያለው ምስል ደግሞ "የነጻነት እና የሰው ዘር እኩል ነው " ብሎ የታ
ገለውን ተከራካሪው አብርሃም ሊንከን መኾኑን ተረዳሁ ። በዚያው
ቀጥሎ እዛው ዶላሩ ላይ ያለው የፕሬዘዳንቱ ቤት ለምን "የነጭ ቤት"
(ዋይት ሀውስ) ተባለ? የሚለው የኹል ጊዜ ጥያቄዬ ነበር። አንድ ቀን
አንድ ወዳጄን ፥ ለምን ነጭ ቤት ተባለ? ብዬ ስጠይቅ የሰጠኝ ምላሽ
ለቀልድ ያህል "የነጮች ቤት" ስለኾነ ይኾናል የሚል ነበር። ጥቁሮቹ
አሜሪካውያን ባለቤት አይደሉም እንዴ ? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ።

ከሞላ ጎደል "አገር የጋራ ነው ፥ ሃይማኖት ግን የግል ነው"
በሚል ፍልስፍና ላይ በተመሠረተ ኅብረተሰብ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ
ሕይወት ውስጥ የክርስትና እምነት ያለውን ቦታ እና አስተዋጽኦ በተ
ለይም ቀድሞ በባርነት እና ዛሬ ደግሞ በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ እና
በፈቃዳቸው ተሰደው በሚኖሩ አፍሪካን አሜሪካን ሕይወት ላይ የክር
ስትና እምነት ምን ጉዳትና ጥቅም አስከትሏል የሚለውን ማጥናት
ጀመርኩ።

የዚህን ሰፊ አገር የታሪክ ዕድገት ኢትዮጵያውያን ቀርቶ
ዜጎቹ ተወላጆቹ አሜሪካውያን እንኳን በጥልቀት ካልተማሩና ካላነበቡ
በውል አያውቁትም ። በአገሩ እየኖሩ የአሜሪካንን ሕይወት ኑሮውን
እና ባህሉን እንዲሁም በተለያየ ጊዜ እየተስፋፋ የመጡትን የፕሮቴስ
ታንት፣ የካቶሊክ እና የኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት ዘርፎች አመጣ
ጣቸውን በመጠኑም ቢኾን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ማሳወቅ እና ድር
ሻዬን ማበርከት አለብኝ የሚል ሓሳብ አደረብኝ። በዚህም የተነሣ ኑሮ
በጀመርኩበት በሜሪላንድ ግዛት (ስቴት) በቦልቲሞር ከተማ ፤ በደብረ
ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በማገልገል ላይ እያለሁ ስለ
አሜሪካ ኑሮ እና ስለ አሜሪካ ክርስትና ሃይማኖት ስብሰቦች የነዋሪው
የዕለት ተዕለት ሕይወት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት ጀመርኩ ።
(ይኽን ሥራዬን በኋላ በለንደን ኮሌጅ "የአሜሪካ እምነቶች ታሪክ"
እና በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ የኅብረተሰብ ጥናት[2] ትምህርት
በመከታተል አኀለበትኩት።)

በንባብ ያገኘሁትን ዕውቀት ለማጠናከር እንዲረዳኝ አንዳንድ
ታሪካዊ ቦታዎችን ጎብኝቻለሁ ። የመጀመሪያ ጉዞዬ ያደረግኹት የአ
ገሪቱ ርእሰ ከተማ ወደ ኾነችው ዋሽንግተን ዲሲ ነበር። በዚያ የአገሩ
ፕሬዘዳንት መኖሪያ የኾነውን ዋይት ሀውስን ፤ የሕግ መምሪያና መወ

[2] American Religious History & Sociology of Religion

## መግቢያ

እንደሚባለው በዚህ በያዝነው ዘመን ላይ ወደ ኹለት ቢሊዮን የሚጠጋ የዓለም ሕዝብ በክርስትና እምነት ሥር ይገኛል። በዚያው ልክ ደግሞ በምዕራቡ ዓለም የክርስትና እምነት ክፍፍል ብዛት ወደ 22 ሺ ደርሷል ይባላል። በዓለም ላይ በየዓመቱ 270 ዐዳዲስ የክርስትና የእምነት ስብስቦችም እንደሚፈጠሩ ተዘግቧል።[3] ምንም እንኳ የተለያየ የክርስትና የመሠረተ እምነት (ዶክትሪን) አመለካከት ልዩነት ቢኖርም 86 በመቶ የአሜሪካ ነዋሪዎች ክርስቲያኖች ነን ብለው ያምናሉ ። በአሜሪካ ክርስቲያኖችና ሌሎች የሃይማኖት ስብስብ ተጨምሮ 157 ሚሊዮን አማንያን አሉ።

አሜሪካ በመልክአ ምድር አቀማመጧ በጣም ትልቅ አገር ስትኾን ፤ በሰሜን በኩል ካናዳ፤ በደቡብ በኩል የሜክሲኮ አገር ሲያዋስኗት፤ በምሥራቅ ደግሞ የአትላንቲክ ውቅያኖስ፤ በምዕራብ የሰላማዊ ውቅያኖስ (ፓስፊክ) ያዋስኗታል። አገሪቷ የተመሠረተችውም ዘመናዊ የምዕራባውያን የሥልጣኔ ዘመንና በአውሮፓ በክርስትና ሃይማኖት ላይ ክህደትና መከፋፈል በተጀመረበት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው።

አሜሪካ የብዙ ዜጎች መኖሪያ ወይም ብዙዎች በተለያየ ዘመን ሃይማኖታቸውን ይዘው ከአውሮፓ ፣ ከአፍሪካ፣ ከእስያ እና ከሩቅ ምሥራቅ በተለያየ ምክንያት ፈልሰው የሚኖሩባት አገር ነች ። ስለኾነም ከብዙ የዓለም አገሮች ታሪክ ጋራ ግንኙነት አላት። ሰው ከእናት አገሩ፣ ከቤተሰቡ ፣ ከዘመዱ እና ከባህሉ ተለይቶ ያልተለመደ የማያውቀው አገር ሲደርስ መጠጊያ የሚኾነው ጎጆ እንደሚቀልስ ኹሉ ፤ የማንነቱን መለያ ምልክት መጽናኛ ስለሚፈልግ በአገሩ ይከተለው የነበረ እምነቱን ለመቀጠል የማምለኪያ ቦታ ማዘጋጀቱ የተለመደ ነው። በክርስትና እምነትም ዙሪያ ብቻ ብንመለከት የኦርቶዶክስ ፣ የካቶሊክ ፣ የፕሮቴስታንት ተከታዮች ሲኖሩ፤ ከክርስትና ውጭ አይሁድ፤ እስላም እና ሒንዱ የመሳሰሉት ይኖሩባታል ። በቁጥር ብዛት የበላይነቱን የያዙት ግን በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ ተገንጥለው የተመሠረቱት የፕሮቴስታንት የእምነት ክፍሎች ናቸው ። የዚህ የተሐድሶ ፕሮቴስታንት መሥራቾች ተብለው በግልጽ የሚታወቁት ማርቲን

[3] Jeffrey B. Webb, *the complete Idiot's Guide to Christianity* chapter1 p.4



ሉተር እና ጆን ካልቪን ናቸው ። የአሜሪካ መንግሥትም ሕገ መንግሥቱ በጆን ካልቪን ሐሳብ ላይ የተመሠረተ ነው ። በመኾኑም ይህ የክርስትና እምነት በአሜሪካውያን ፖለቲካዊም ኾነ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በጉልሕ የሚታይ አስተዋጽኦ አለው ። ይኽንንም ለመግለጽ አንዳንድ ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል።

አሜሪካኖች ከእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ነጻ ከወጡ በኋላ በፕሬዚዳንትነት ከተመረጠው ጆርጅ ዋሽንግተን እስከ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ ድረስ ያሉት በንግግራቸው የሚያስገቡት ቃላት አሉ ። ለምሳሌ "እግዚአብሔር አሜሪካን ባርክ !" (God Bless America!) የሚለው የተለመደ አባባል ነው ። በተጨማሪም ፕሬዚዳንቶቹ በትረ ሥልጣን ሲረከቡ እጃቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አድርገው በእግዚአብሔር ስም ቃለ መሐላ መፈጸም፤ ፖለቲካቸው ሲበላሽ፤ ሕዝብን ሲያሳስቱ፤ ንስሐ መግባት ወይም ይቅርታ መጠየቅ የመሳሰሉት ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው። ይቅርታን መጠየቅ ከእግዚአብሔር የታዘዘ በመኾኑ እና ከፈጣሪ በላይ የሚኾን ስለሌለ ተግባሩ ታላቅ ነገር ነው። ለምሳሌ፦ ፕሬዘዳንት ኒክሰን በድጋሚ ለመመረጥ ሲሞክር ያላግባብ በፈጸመው የምርጫ የመጭበርበር ተግባር ተደርሶበት የአሜሪካንን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቋል ። ፕሬዚዳንት ክሊንተን ደግሞ በጋብቻው ላይ በፈጸመው ስሕተት በሜተዲስት የክርስትና እምነት ካህን ፊት ንስሐ ገብቶ ያሳሳተውን ሕዝብ እና ባለቤቱን ይቅርታ ጠይቋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች እና ተራ ሰዎች የአብዛኞዎቹ ስማቸው በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተመሠረተ ነው። ለምሳሌ ጆርጅ (ጊዮርጊስ)፤ ጀምስ (ያዕቆብ)፤ ጆን (ዮሐንስ)፤ አደምስ (አዳም)፤ ቤንጃሚን (ብንያም) የመሳሰሉትን የመጀመሪያ ስሞች (የክርስትና ስሞች)[4] መጥቀስ ይበቃል ። ከነዚህ ውስጥ የአንዳንዶቹን ፕሬዚዳንቶች ታሪክና ከክርስትና ጋር ያላቸውን ግንኙነት በጥቂቱ እናያለን።

ሌላም ማስረጃ ቢፈለግ የሆሊ ውድ ፊልም ሠሪዎች እና ዘፋኞች በዘፈኖቻቸው ጣልቃ የሚያስገቡት አንዳንድ አነጋገር ፤ እስፖርተኞችና የእስፖርት ተመልካቾች እንዲሁም ተጫዋቾች ለድል ሲበለፉ ማማተባቸው፤ ሲደነግጡ እና ሲደሰቱ "ኦ ማይ ጋድ!" (Oh My God!)

[4] በኢትዮጵያውያን ባህል መጠሪያ ስም እና የክርስት ስም (ሉቃ.10፥20 ፤ ዘፀ. 32፥32) ብዙ ጊዜ የተለያዩ ናቸው።

የሚለውን ኀይለ ቃል ዘወትር የሚታይ የአሜሪካ ባህል መኾኑን መጥቀስ ይቻላል ።

በሕጉ ዓለም ብንመለከት ደግሞ አሜሪካኖች እንደ ኦሪቱ ሕግ የገደለ ይገደል (ዘጸ. 21፥24) የሚል ሕግ የሚከተሉ ግዛቶች አላቸው ። በዚህም የተነሳ ሰው የገደለ በፍርድ ቤት ተፈርዶበት በኤሌክትሪክ ተጠብሶ ወይም በመርፌ ተወግቶ እንዲሞት ይደረጋል።

በአገሪቱ ዜና ማሠራጫዎች በተለይም በራዲዮና በቴሌቪዥን ባለማቋረጥ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የወንጌል የስብከት ስርጭት በማስፋፋት ወድድር መግባታቸው በግልጽ ይታያል ። በጣም በዙ ሀብት ያላቸው የፕሮቴስታንት ሰባክያን በዚሁ ተግባር ላይ ተሠማርተው በሀብት ላይ ሀብት ይጨምራሉ። በግል አውሮፕላኖቻቸው በመኳንዝ እና እንዲሁ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሕዝብ መገናኛ (Mass Media) በመጠቀም በየአህጉራቱ የፕሮቴስታንትን ትምህርት ያስፋፋሉ።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው አንዳንድ ኹናቴዎች የክርስትና ሃይማኖት በአሜሪካውያን የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያለውን ቦታ ለማሳየት ይጠቅማል ብዬ አምናለሁ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በእንግሊዞች ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩት የአሜሪካ ነዋሪዎች በትግልና በጦርነት ነጻነታቸውን አወጀው የአሜሪካንን መንግሥት አቋቋሙ ። ነገር ግን ይህ ነጻነት የጠቀመው ከአውሮፓ ፈልሰው የመጡትን ነጮች እንጂ የአገሩን ተወላጆች አልነበረም። ነጭ የተመረጠ ዘር ነው በሚል ትዕቢት ከቀድሞ ጀምሮ በአገሪቷ ነዋሪዎች የኾኑ ባለ አገሮቹን (በኋላ በሰፊው እንደምናየው ኢንዲያን ተብለው የተጠሩትን) በአገራቸው እስረኛ በማድረግ፤ ከዚያም አፍሪካውያንን ከአፍሪካ በማጋዝ በባርነት በመግዛት ከእንስሳ ባልተሻለ ኹኔታ ለዘመናት ስቃይ ዳርገዋቸዋል። ይህ የአሜሪካ አንዱ አሳዛኝ ገጽታ ነው።

የባርነት ሥርዓትን ለማስወገድ የተደረገው ትግል በኋላ በዝርዝር እንደምናየው በ1860 የርስ በርስ ጦርነት እንዲካኼድ ምክንያት ኾኗል ። ከዚያም ቀጥሎ ደግሞ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ትግሉ ተስፋፍቶ እንደ ማርቆስ ጋርቬይ (1914) ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ እና ማልክልም ኤክስን (1960) የመሳሰሉ ታዋቂ የነጻነት መብት እንቅስቃሴ መሪዎች ተፈጥረው በጥቁሮች የነጻነት ትግል ታሪክ ውስጥ ዘላለም የሚታወስ ዝና እና ክብር አትርፈው እንዲያልፉ ምክንያት ኾኗል።



ብዙዎች ጥቁሮች ነጮች ይፈጽሙት በነበረው የዘረኝነት አስከፊ አድራጎት የተነሳ በፕሮቴስታንት ክርስትና እምነት ላይ ጥላቻ ካላደረባቸው ወደ እስልምና ተቀይረዋል ፤ ግማሾቹም "ራስን ማወቅ" በሚል ዓላማ ተነሳስተው የዘር ሐረጋቸውን ሥር እስከ መፈለግ ደርሰዋል ። የአፍሪካ አህጉራችን እና የአፍሪካ ባህላችንን እንመሥርት፣ ወደ ኢትዮጵያ አገራችን እንመለስ የሚል ሕልም እንዲያልሙ አድርጓቸዋል። ሕልሙም እውን እንዲኾን ታግለዋል። ይህ ትግል "ዘኔሽን ኦፍ እስላም እና ራስ ተፈሪያን" ተብለው የሚጠሩ ዐዲስ የእምነት ዘርፎች እንዲመሠረቱ መንገድ ከፍቷል ። ይህም እምነት በካሪቢያን ደሴቶች፤ በተለያዩ የአውሮፓ አገሮችና በአፍሪካ ጭምር ተስፋፍቶ ይገኛል።

ይህን የአሜሪካ የክርስትና እምነት ታሪካዊ አመጣጥ እና መስፋፋት ከተጀመረ ወዲህ እስካለንበት ጊዜ ድረስ ያለውን ኹኔታ ስንማትር ፥ እግረ መንገዱንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ በአሜሪካ አገር ነዋሪ የኾኑ ዜጎቿን እና ሌሎችም የአሜሪካ ዜጎችን በዚህች ሃይማኖት ጥላ ሥር ለማሰባሰብ መምህራኖቿ ያደረጉትንና በማድረግ ላይ ያሉትን ጥረት ፤ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቷ የተከሰተውን የአስተዳደር የውስጥ ችግሮች በጥቂቱ ለመረዳት ይቻላል የሚል እምነት አለኝ።

አዘጋጁ

# ክፍል አንድ

## ምዕራፍ ፩
## ዐድሲቷ ዓለም አሜሪካ

አሜሪካ ለብዙ ሺህ ዓመታት የሰው ዘር መኖሪያ ያልነበረች ባዶ ተራራዎች፣ ጫካዎች ፣ ወንዞች፣ እንስሳት እና አሳዎች ብቻ የሚኖሩባት ምድረ በዳ ነበረች። በዘመናዊው የታሪክ ጥናት እንደምንረዳው በመጀመሪያ ምድሪቷን የረገጡ ሕዝቦቿ የመጡት ከሳይቤሪያ ወይም ከእስያ ክፍለ ዓለም በሰሜን አላስካ በኩል አድርገው ወደ ደቡብና ምሥራቅ ተጉዘው የገቡ መኾናቸው የታሪክ አጥኝዎች ይናገራሉ።[5] ይህች አገር ለብዙ ሺህ ዓመታት በቀረው የዓለም ክፍል እና በአውሮፓውያን ዘንድ ሳትታወቅ ትኖር ነበር።

የአውሮፓ ነጋዴዎች ከምሥራቁ የዓለም ክፍል ማለትም ከቻይና ፣ ከህንድ እና ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋራ ተገናኝተው የንግድ ልውውጥ የሚያደርጉት በየብስ (በደረቅ መሬት) በእግር በመጓዝ ፣ በከብት ትከሻ ሸቀጥ ተጭኖ ብዙ ጊዜ እየፈጀባቸው በአስቸጋሪ ኹኔታ እያቆራረጡ ሲጓዙ ኖረዋል። ኾኖም ይህ የንግድ ልውውጥና የእርስ በርስ የሀብት ፍለጋ ውድድር እየጠነከረ ሲኼድ አስቸጋሪውን ጉዞ ቀላል የሚያደርጉበትን ኹናቴ ለመፍጠር ብዙ ዘዴ ይፈልጉ ነበር።

### (፩) ክርስቶፎር ኮለምበስ

በመጀመሪያ ዐዲሲቷን ዓለም አገኘት ተብሎ የሚነገርለት ከ1492 እስከ 1506 ባሉት ዓመታት ውስጥ ወደ አሜሪካ ደጋግሞ የተመላለሰው የጣሊያኑ መርከበኛ ክርስቶፎር ኮለምበስ ነው።

ኮለምበስ ጄኖአ በምትባለው የጣሊያን ከተማ አጠገብ ከካቶሊክ አማንያን ቤተሰብ ተወለደ ። ወላጆቹ የሸመና ሙያተኞች እና እንዲሁም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሌትና ቀን ተግተው የሚያገለግሉ አማኞች ነበሩ። ኮለምበስ የቤተሰቦቹን ሞያ የኾነውን የሸማ ሥራ ሳይከተል መርከበኛ ኾነ። ይኹን እንጂ እንደ ወላጆቹ እሱም በሮማ

[5]. WWW. Native American History.



ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የኾነ እምነተ ጠንካራ ፣ የቀን እና የማታ ጸሎት ተሳታፊ በመኾን ዘማሪም ነበር።[6]

በዚያን ዘመን ያውሮፓውያን የንግድ ሸቀጥ ብረት ፣ ወይን ፣ አትክልት፤ ሌሎችም ነገሮች ወደ ሩቅ ምሥራቅ አገሮች በተለይ ወደ ህንድ እና ቻይና በማድረስ ከዚያ ደግሞ ቅመማ ቅመም ፣ የሐር ልብስ ፣ ጌጣጌጥ የመሳሰሉት ሸቀጦች ሲለዋወጡ ይኖሩ ነበር። በዚህ በደረቅ ምድር ላይ መጓዝ ውድ እና አደገኛ እየኾነ መጣ። አንዱ ምክንያትም የእስልምና ሃይማኖት ወረራ መካከለኛው ምሥራቅን እየተቆጣጠሩት ስለመጡ፤ የእስላም መንግሥታት እየተጠናከሩ በመደራጀታቸው ያሰቡበት ቦታ ለመድረስ በጣም አሸጋሪ ኾነ ። በዚህ የተነሳ አቋራጭ መንገድ ማግኘት አስፈላጊ ነበር ። ስለዚህም የእስፓኟ የካቶሊካዊት ንግሥት ቀዳማዊት ኢዛቤላ አገሯ እስፓኝ አውሮፓን በኢኮኖሚ እንድትመራ ባላት ዕቅድ መሠረት መርከበኛው ኮለምበስ ገንዘብ ተከፍሎት በምዕራብ በኩል ወደ ሩቅ ምሥራቅ የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ እንዲፈልግ አዘዘች፤ ሀብትም እንደምትሰጠው ቃል ገባችለት ። እሱም በዋጋ ተስማምቶ ተፈራረመ ፤ ጉዞውንም ከስፓኝ ወደብ በመነሳት ሳንታ ማርያ ፣ ኒና እና ይንታ የሚባሉ ሦስት መርከቦችን አሰልፎ በበላይነት መንገድ እየመራ ህንድን እና ቻይናን ፍለጋ በምዕራብ በኩል ጉዞውን ቀጠለ።

ኮለምበስ ባላሰበውና ባልጠበቀው ጉዞ ሰፊው አትላንቲክ ውቅያኖስ ውስጥ ገባ ። ከዚያ በፊት ዓለም ጠፍጣፋ ነች ተብሎ ይታመን ስለነበረ የመርከብ ቀዛፊዎቹ ምድር ጠፍጣፋ ኾና አውሮፓን እንደ እናት ወስደው የጠፍጣፋው ምድር ዳርቻ ሲፈጸም ምን ይውጠን ይኾን እያሉ ያስቡ ነበር ። እያለቀሱ እና እየጸለዩ በአስጨናቂ ጉዞ በብዙ ችግር እና ስቃይ አትላንቲክን አቋርጠው ከሦስት ወር በላይ ተጉዘው ጥቅምት 12 ቀን 1492 በዐዲሲቷ ዓለም ጠረፍ አካባቢ ካሪቢ

[6] The Modern Age vol. 2 p.194
በነገራችን ላይ አሜሪካዊው ፕሮፌሰር ሄንሪ ልዊስ በአንድ ወቅት ኢትዮጵያን ለዓለም ሲያስታውቅ እንዲህ በማለት መስክሯል፤ ኮለምበስ አሜሪካን ከማግኘቱ ከ1000 ሺ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ክርስትና ተሰብኮባታል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቅድስት አገር ነች ( Holy-Land ) 1600 ዓመት ክርስትና የተሰበከባት ነች። አውሮፓውያን በመቶ ዓመታት ክርስቲያን ሳይኾኑ ኢትዮጵያ ክርስቲያን ነበረች ። (የኢጲስኮፓል ቤ. ክ. አባል እና የታሪክ ፕሮፌሰር
( Harry Louis Gates, Jr. AFRICAN WORLD VIDIEO documentary)

ያን (ዌስት ኢንድያን) በሐማ ፤ ሳን-ሳልቫዶር ደረሱ በዚያም አንዳንድ ትናንሽ ደሴቶችን አገኙ።

ኮለምበስ የሚፈልገው ከአውሮፓ ወደህንድ የሚወስድ የባሕር ሰርጥ የንግድ መለዋወጫ አዲስ መስመር ለማግኘት ነበር ። ኾኖም ከላይ ከተጠቀሱት ደሴቶች አጠገብ ሲደርስ ህንድ ደረስኩ አለ ። ነገር ግን ከህንድ በጣም የራቀ መኾኑን አላወቀውም ነበር። በባሕሩ ዳርቻ መርከቢቷን ያዩ የአገሪቷ ተወላጆችም ከበቡት። እሱም የህንድ ሰዎች መሰለው ስለታዩት "ኢንድያን"[7] ብሎ ጠራቸው ። ነሽር ግን ያገኘው አገር ህንድ ሳይኾን ዛሬ ዌስት ኢንዲስ ተብሎ የሚጠራውን ስፍራ ነበር። ያገኛቸው ሰዎች በባህላቸው ከአውሮፓውያን የተለዩ ነገር ግን በቀላሉ ክርስቲያን መኾን የሚችሉ ናቸው በማለት በማስታወሻው ላይ ጻፈ። ባለማቋረጥ ተጨማሪ ሦስት ታላላቅ ጉዞዎች ተጉዞ ኪዩባ፣ ፖርቶሪኮን፣ የጃማይካን ደሴቶችና የደቡብ አሜሪካ ቦታዎችን አገኘ።

የሩቅ ምሥራቅ አቋራጭ የንግድ መንገድ አግኝቶ በኢኮኖሚ አውሮፓን እንመራለን ብለው ያሰቡትን የእስፓኝን ንግሥት እና ንጉሥ የንግድ መነገጃ ዐዲስ መንገድ አላገኙም ፤ ሐሳባቸው አልተሳካም ። ኮለምበስም ይጠብቁት እና ያሰቡት የነበረውን የወርቅ ማዕድን አላገኘ ላቸውም ። እነሱም ሀብት ሊቸሩት የገቡለትን ቃል ኪዳን ሳይፈጽሙ ለት በድህነት ኖሮ በ1506 ሞተ።

በመጨረሻም ወሬው በመላው አውሮፓ ተሰማ፤ የሱ መጓዝ ለብዙዎች ከአውሮፓ አህጉራት ተጉዘው ወደ አዲሲቷ ዓለም እንዲሰ ፍሩ መንገድ ከፈተ። ለእብዛኛዎቹ ሰፋሪ ሰደተኞች ጥቅም አስገኝቶላቸ ዋል። ቀደም ብለው ለሠፈሩት ለተወላጆቹ በመሳሳት ኢንዲያን ብሎ ለጠራቸው ሕዝቦች ግን የመገፋት ዕድል አተርፎላቸዋል። እስከ ኮለም በስ ጊዜ ድረስ ግን የዓለም ትክክለኛ ካርታ አይታወቅም ነበር።

በነገራችን ላይ በዚህ በኮለምበስ የጉዞ ዘመን በኢትዮጵያ (1460 ዓ. ም.) ላይ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በመ ኾን ብዙ ለውጥ ያመጡበት ወቅት ነበር ። እሳቸውም ስምንተኛው ሺህ የሚባለው ዘመን ሲገባ እንዳያዩት ይጸልዩ ስለነበረ ዘመኑ ሳይደ ርስ ሞተዋል ። ከሌሎች ልጆቻቸው ንግሥና በኋላ የነገሡት ዐፄ ናዖድ ጊዜ ግን (1487 - 1501 ዓ.ም.) መስከረም 1 ቀን 1501 ዓ. ም.

[7] ከእኹን በኋላ አንባቢን እንዳያደናግር ኮለምበስ ነዋሪዎቹን "እንዲያን" ብሎ በጠራቸው ስም ይጠራሉ።



ስምንተኛው ሺ ገባ ተባለ።[8] ወዲያው ግራኝ መሐመድ እስልምናን ለማስፋፋት የክርስትናዋን አገር ኢትዮጵያን ወደ እስልምና ለመለወጥ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍትና አብያተ ክርስቲያናትን ፤ ክርስቲያኖችን ያጠ ፋበት ዘመን ነበር።

በዚህ ዓመታት አካባቢ ዐዲሲቷ ዓለም በኮለምበስ ተገኘች።

ዛሬ በአሜሪካ ኮለምቦስ ምድሪቷን የረገጠበት ጥቅምት 12 ቀን ብሔራዊ የሕዝብ በዓል ኾኖ በየዓመቱ "የኮለምበስ ቀን" እየተባለ ይከበራል ። ከኮለምበስ ግኝት በኋላ አዲሲቷ ዓለም በሚያስደንቅ ኹኔታ ዕድገት እያሳየች መጣች። የቀድሞው የመካከለኛው ምሥራቅ ታላቅ ሥልጣኔ በአውሮፓውያን እና በዐዲሲቷ ዓለም ነዋሪዎች ተለ ወጠ ። የሰው ልጅ የዕውቀት አድማስ እየሰፋ ኼደ ፤ መጽሐፍት በቀ ላሉ እና በብዛት መታተም ጀመሩ። ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች መስ ፋፋት እና የምርምር ተግባር በስፋት፣ በጥልቀት መከናወን ቀጠለ ። ይህ የሥልጣኔ ዘመን በትንቢተ ዳንኤል አስቀድሞ ተተንብዮ ነበር።

> ዳንኤል ሆይ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፤ መጽሐፉንም አትም ። ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ ፤ ዕውቀት ይበዛል (ትን. ዳን. 12፥4)።

## (፮) የሥልጣኔ ዘመናት አከፋፈል

የዓለም ታሪክ ተመራማሪዎች ዓለምን በሦስት የሥልጣኔ ክፍለ ዘመን ከፋፍለዋታል። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት 4000 ሺህ ዓመት ጀምሮ ከልደት በኋላ ያለውን 500 ዓመት ጨምሮ ጥንታዊ የታሪክ ክፍለ ዘመን ይባላል ። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ከ500 እስከ 1500 ዓምት ያለው ጊዜ መካከለኛ የሥልጣኔ ዘመን ይባላል ። ከ1500 ጀምሮ እኹን እስከ አለንበት ድረስ ያለው ዘመን ደግሞ ዘመ ናዊው የሥልጣኔ ዘመን ይባላል[9]።

ይህ የመጨረሻው የሥልጣኔ ዘመን በኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ልማድ ስምንተኛው ሺ የገባበት ዘመን ነው ። ስምንተኛው ሺ ማለት 5500 ዓ. ዓ. ከክርስቶስ ልደት በፊት ፤ ከዚያም 1500 ከክር

[8] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል ገጽ 27

[9] The Modern Age vol. 2 p. 3

ስቶስ ልደት በኋላ ተጨምሮ በአንድ ላይ ሲደመር 7000 ይኾናል። 7000 ሺ አልቆ ስምንተኛው ሺ ከገባ ከ500 ዓመታት በላይ አልፏል፤ (አኹን 7500 ነው) በዚህ ባለፉት ዘመናት ውስጥ ብዙ የተነገሩ ትንቢቶች ተተንብየው ተፈጽመዋል። እንዲህ ከኾነ በቀረው 500 ዘመን ምን ይታይ ይኾን?።

የዚህ ጽሑፍ ትኩረት ከጌታ ልደት ከ1500 ዘመን በኋላ ባሉት 500 ዓመታት ውስጥ በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል በጉዞ ኺደት የተፈጠረውን ለውጥ እና ልዩነት ከአሜሪካ ታሪክ ጋር እያገናዘቡ ማቅረብ በመኾኑ ወደተነሳንበት ጥንተ ነገር እንመለሳለን ።

## (፫) ሬኔሳንስ

በዚህ የመካከለኛው የሥልጣኔ ማብቂያ የዐዲሱ የሥልጣኔ መግቢያ ዘመን ሬኔሳንስ (RENAISSANCE)[10] ( የዕውቀት ዳግመኛ ልደት) እንቅስቃሴ በኢጣሊያ ተጀመረ። በተለይ ከፍተኛው እንቅስቃሴ የነበረበት ጊዜ (the HIGH RENAISSANCE) ከ1490 እስከ 1520 ድረስ ነበር ። ብዙ የዘመኑ ዐዋቂዎች እና ተመራማሪዎች የክርስትና እምነትን ችላ በማለት የግሪክን እና የሮማውያንን ሥልጣኔ መከተል ጀመሩ ። ከነዚህም ውስጥ ብዙዎቹ ሠዐሊዎች ነበሩ ። ከሠዐሊዎች አንዱ ታዋቂው ሊዮናርዶ ዳቪንቺ ነው።

ዳቪንቺ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያገለገለ የኖረ ክርስቲያን አይደለም። ሥዕል ሠዐሊ እና ሳይንቲስት (Humanists) እንዲኹም በእግዚአብሔር የማያምን ሰው እንደነበር ይነገራል። ሥዕሎችን በመሳለው ጥበብ ይስል ነበር። በሥዕል ቅብ ዝነኛና አድናቆትን ያገኘ ሰው ነው ። ይህን ዝና ካስገኙለት ሥዕሎች አንዱ በ1498 ኢጣሊያ ውስጥ በዶሚኒካን ኮንቬንት ግድግዳ ላይ የሳለው የጸሎተ ሐሙስ መታሰቢያ ነው ብሎ የሚገምተው ሥዕሉ ነው ። ይህም ሥዕሉ "የመጨረሻው ራት (The Last Suppr)" በመባል የሚታወቅ ነው ። በዮሐንስ ወንጌል እንደተገለጸው በጸሎተ ሐሙስ የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ላይ የተገኙት ደቀ መዛሙርት እንጂ የማርያም መቅደላዊት መገኘት አልተ

[10] RENAISSANCE = Artists and historians use the term “Renaissance” to refer the period in European history when there was a rebirth of the arts and sciences based on Greek and Roman sources. The term is appropriate because it is a combination of the Latin prefix re, meaning “back” or “again, and the Latin verb nascere, meaning, “to be born.”



ጠቀሰም ። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ የተቀመጠው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው።

> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስቱን አንስቶ ባረከ ፤ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ ። ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህም አለ ኹላችኹ ከርሱ ጠጡ። ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።
> (የሐ. 21፥20 ፤ ማቴ. 26፥26 ፤ ኤር. 31፥31)

ብሎ ጌታ የተናገረው ዘላለማዊ የኾነ ለክርስቲያኖች የተሰጠ ቃል ኪዳን ነው ።

ዳቪንቺ ይህን ሥዕሉን የተንኮል ሥራ ጨምሮበት ምስሉን በዮሐንስ ቦታ የማርያም መቅደላዊት ምስል አድርጎ ሣለው ብለው በዚህ ዘመን ያሉ ሰዎች ይናገራሉ። (Modern critic)። ከነዚህ ውስጥ አንዱ በአሜሪካ ነዋሪ የኾነው ዳን ብራውን ያዘጋጀው የዳቪንቺ ኮድ ብሎ የጻፈው የልብ ወለድ መጽሐፍ ነው ። ዳን ብራውን ላንድ ሰሞን ምእመናን አደናገረ። ሊዮናርዶ ዳቪንቺ የጸሎተ ሐሙስን ሥዕል በግል እምነቱ መልእክት ለማስተላለፍ ያዘጋጀው ነው በማለት ጮሌነት የተሞላበት የመላምት መጽሐፉን ጻፈ ። ይህ ደራሲ እውነትን እና ግምትን (ታሪክን እና ልብ ወለድን) አደባልቆ አንባቢን በሚስብ አቀራረብ የጻፈው የልብ ወለድ መጽሐፍ ከፍተኛ የገንዘብ ጥቅም አስገኝቶለታል።

> በእኔ ከሚያምኑት ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ኹሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር (ማቴ. 18፥3)።

ይህን የጥርጣሬ መንፈስ በአማንያን ላይ ለማሳደር ተቀነባብሮ የተዘጋጀው የዳን ብራውን መጽሐፍ የሮማው ሊቀ ጳጳስ (ፖፕ) በ2006 በዕለተ ዐርብ የጌታ ስነስቅለት መታሰቢያ ወቅት ባደረጉት ቃለ ምዕዳን (ስብከት) ጉዳዩ አሳዝኗቸው ፤

> "ይሁዳ ጌታ ኢየሱስን በሠላሳ ብር ሸጠ። ዛሬ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ዳን ብራወን እንዲሁም ብዙዎች ሰዎች ጌታችንን በሚልዮን ብር እየሸጡት ይገኛሉ" በማለት ብሶታቸውን ገልጸዋል።

ሊቀ ጳጳሱ (ፖፑ) ሊገልጹ የሞከሩት በዚህ ዘመን በገንዘብ ላይ ወይም በፍቅረ ንዋይ የተነደፈ ሰው የሚቻለው ኾኖ ከተገኘ ፈጣሪንም ለመሸጥ ወደኋላ የማይል (ከይሁዳ የማይተናነስ) መኾኑን ለመግለጽ ነው።

በዚህም ድርሰት ላይ ብዙ ሰዎች ትንተና ሰጥተውበታል ፤ በዚህ ጽሑፍ ደካሞች ይሰናከሉበታል ተሰናክለውበታል ፤ ጽኑዎች የበለጠ ተጠናክረውበታል ። ገንዘብ ለማግኘት ኾን ተብሎ ውሸትን ሸምጥጥ አድርጎ እውነት ለማድረግ መሞከርና የእምነትን መሠረት ለማናጋት መሞከር ኃጢአት መኾኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

ዳቪንቺ ሥዕሎቹን ከመሳሉ በስተቀር ምንም ነገር ስለ ክርስትና የጻፈው መረጃ የለም ። የነገረ መለኮት አዋቂ ወይም ባለሙያ አልነበረም። ነገር ግን የዐዲሱ ዘመን መግቢያ ላይ የተፈጠረ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የምርምርና የፈጠራ ሥራ ችሎታ ያለው ሠዐሊ ነበር ። ሊዮናርዶ ዳቪንቺ በ67 ዓመቱ ግንቦት 2 ቀን 1519 ሞተ።

ይህ ወቅት ማይክል አንጀሎ እና ራፋኤል ሳንዚዮ የሥዕል እና የሥነ ጥበብ ሰዎች የተነሱበት እና ሥነ ጥበብ በሰፋት እና በጥልቀት ዳብሮ ፀታየበት ጊዜ ነበር ። ይህ ዘመን የዓለም ታሪክ የተለወጠበት ዘመናዊ የሥልጣኔ መግቢያ ዘመን በመባል ይታወቃል ። ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው ምርምር እና የሳይስን መሥራቾች ጋሊልዮ፣ ኒውተን እና ኬፕለር እንዲሁም ሌሎችም ሳይንቲስቶች የተፈጠሩት።

ከኮለምበስ ቀጥሎ በ1498 ከፖርቱጋል በመነሳት የገበያ ፍለጋ አሰሳ ያካኼደው አንዱ ቫስኮ ዳጋማ ነው። እሱም በከፈተው ጥርጊያ መንገድ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ በመጓዝ ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ባርያ ሌሎችንም ነገሮች ከአፍሪካ በማጋዝ በፖርቱጋል የካፒታሊዝም ሥርዓት እና አፍሪካን የቅኝ አገዛዝ ማድረግ የተጀመረበት ዘመን ነበር ። ሥርዓቱን የጥቅም ማስከበሪያ እና የኀይል ምንጭ የኾነው የጠመንጃ ባሩድ የተፈለሰፈውም በዚህ ዘመን ነበር።

ከዚያም በላይ ይህ የታሪክ ምዕራፍ የእስልምና ሃይማኖት ከዐረብ አገሮች ወደ አፍሪካ እና እስያ ክፍለ ዓለማት የተስፋፋበት፤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ስብከት እንዲሁም የኃጢአት ማስተሥርያ እያለች ባወጣችው የገንዘብ ማግኛ ዘዴ እንቅፋት ገጥሟት የተሐድሶ እምነት መሪዎች ሉተር እና ካልቪን ሌሎችም የተነሱበት፤ በምዕራባውያን ዘንድ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች አንድነት እንደ ክር መበጣጠስ የጀመረበት ዘመን ነው።

እንዲሁም ዘመኑ የቅኝ አገዛዝ እና የዳርዊን ፍልስፍና የተፈጠረበት ፤ የካፒታሊዝምን ሥርዓት አጠፋለሁ ፤ የሶሻሊዝምን እና የኮምኒዝምን ሥርዓት እመሠርታለሁ ብሎ የተነሳው እግዚአብሔርን በመካድ ዓለምን ሲያባስት የነበረው የማርክስ ፍልስፍና የተፈጠረበት ዘመን



ነው ። አኹን እኛ የደረስንበት ወቅት ደግሞ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ ምርምር እና ዕድገት በከፍተኛ ኹኔታ እየፈጠነ ያለበት እና ካፒታሊዝም ወደ ግሎባላይዜሽን (Globalization) ደረጃ የተሸጋገረበት ደሀ እና ሀብታም ተራርቀው መቸም ሊገናኙ የማይችሉ መስለው በሚታዩበት ዘመን ላይ እንገኛለን።

## (፬) አሜሪጎ ቬስፑቺ

ከኮለምበስ ቀጥለው ከተጓዙት ሌሎች ተጓዦች ውስጥ አንዱ ደግሞ ለእስፓኝ እና ለፖርቱጋል መንግሥታት አገልጋይ የነበረው አሜሪጎ ቬስፑቺ (Amerigo Vespucci) የተባለ የጣሊያን ነጋዴ ነው። ይህ ለእስፓኝ እና ለፖርቱጋል መንግሥት አገልጋይ የነበረው ቬስፑቺ የኮለምበስን ፈለግ ተከትሎ ወደ ዐዲሲቱ ዓለም በ1499 እና በ1502 ለዐራት ጊዜ ያህል ተመላለሰ። የእስያ ክፍል ያልኾነ አዲስ ክፍለ ዓለም ማግኘቱን ተረዳ ። ይህን ያየውን ቦታ በጣም ትልቅ አገር መኾኑን እና ይህ ዐዲስ ዓለም አባቶቻችን ጨርሶ የማያውቁት አገር ነው በማለት በጽሑፍ በማስፈር አረጋገጠ።[11]

በ1507 ማርቲን በመባል የሚታወቅ ጀርመናዊው አሜሪጎ ያየውን ቦታ ጨምሮ የዓለምን ካርታ አዘጋጀ። በዚህ ጊዜ የአውሮፓ ነጋዴዎች ከበርቴ ለመኾን ወርቅ ፍለጋ ይገሠግሡ ጀመር። የወንጌል ሰባኪዎችና ምእመናኖች ከተበጣበጠው የአውሮፓ ክፍለ ዓለም ከመኖር የሃይማኖት ነጻነት ለማግኘት እና ወንጌልን ለመስበክ (ሚሽን) አሜሪጎ ወደ ኼደበት እንኺድ ሲሉ “አሜሪካ” ብለው አገሪቷን ጠሯት።

የጣሊያኑ መርከበኛ ነጋዴ አሜሪጎ ዐዲስ ዓለም በመኼዱ ስሙ ለዘላለም የማይሻር በመታሰቢያነት የሚታወቅ መጠሪያ ኾኖ ተተከለለት።

# ምዕራፍ ፫
# የተሐድሶ ንቅናቄ በአውሮፓ

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሬኔሳንስ (የዕውቀት ዳግም ልደት) በኢጣሊያ ተጀምሮ ቀስ በቀስ ወደ ጀርመን ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ተዛመተ ። ከሬኔንሳንስ ንቅናቄ ጀምሮ ካህናት ፣ ምእመናን መጽሐፍ

[11] The Modern Age vol. 2 p. 198

ቅዱስን በላቲን ብቻ ሳይኾን በዕብራይስጥና በግሪክ ማጥናት ጀመሩ። መጽሐፍ ቅዱስ በእጅ መጻፉ ቀርቶ በማተሚያ መታተም ተጀመረ ። በ1517 ብዙ የጽሑፍ ማተሚያ ቤቶች ተቋቋመው ስለነበር ጽሑፎችን ለማሳተም ከቀድሞው ዘመን ይልቅ ቀላል ኾኖ ተገኘ ። እነዚህ የመጽሐፍ ማሳተሚያ ማሽኖች ግኝት እና ዕድገት ለተሐድሶ እንቅስቃሴ መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ። ሌላው ቀርቶ ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉትም ምእመናን ዐዲስ የታተመው መጽሐፍ ሲነበብ ለመስማት በየጊዜው ወደሚቀርባቸው አብያተ ክርስቲያናት በመኼድ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት መከታተል ዠመሩ ። ብዙ ሰዎች የማስተማሪያ ቦታ (ዩንቨርሲቲ) እና አስተማሪ ቀሳውስት ባሉበት ቦታዎች እየተዘዋወሩ ጥናታቸው በመቀጠላቸው ቀስ እያለ የተለያዩ አመለካከት እና አስተሳሰብ መፈጠር ጀመረ።

## (፩) ተሐድሶ በጀርመን

የጀርመን ተሐድሶ (Reformation) በመባል የሚታወቀው ዐዲስ የክርስትና እምነት ዘርፍ የጀመረው መሪ መነኩሴው ማርቲን ሉተር ነው። ሉተር ኅዳር 10 ቀን 1483 የመዳብ ማዕድን ሀብት ካላቸው ቤተሰቦች ሓንስን እና ማርግሬት ከሚባሉ ጀርመናውያን ተወለደ ፤ የትውልድ ቦታው ማንስፌልትና አይስሌቨን ይባላል፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በ18 ዓመቱ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ትምህርት መከታተል ጀመረ። ይኹን እና በ1505 በድንገት የሉተር ሕይወት ተለወጠ ። በአውሮፓ ለመቶ ዓመታት ብላክ ዴዝ (Black Death)[12] የሚባል በሽታ ወይም ተስቦ በየጊዜው እየተነሳ ሕዝቡን ይጨርስ ነበር ። በዚህ ብዙ ሕዝብ በየመንገዱ ይረፈረፍ በነበረበት ዓመት የሉተርም ሦስት ጓደኞቹ በዚህ በሽታ ሞቱ ። በ23 ዓመት ዕድሜው ቤተሰቡን ለመጠየቅ በመንገድ ላይ እየተጓዘ ባለበት ወቅት ኀይለኛ ዝናብ ዘንቦ መብረቅ ወረደበት፤ ነገር ግን አልገደለውም። የሚማረውን የሕግ ትምህርት ትቶ ብዙ መከራ ደርሶብኛል ከእንግዲህ ጓደኞቼ ጥለውት የኼዱት ዓለም ለእኔስ ምን ሊረባኝ ብሎ በቅድስና ለመኖር የምንኩስናውን መንገድ መረጠ ። በአውግስትያ ገዳም ገብቶ መነኰሰ ። ከልጅነቱ ዠምሮ እእምሮው ያልተረጋጋ ስለነበር የገዳሙ አባት (አበምኔት) እንዲረጋጋ በማ

---

12 **Black Death**= killed between one-third to half of the population in Europe (about 70 million people)



ሰት መጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር ማንበብ እና መጸለይ እንደሚገባው ይመከረው ነበር። በ1507 በካቶሊክ ቤተክርስቲያን የቅስና ክህነት ተቀበሎ ማስተማር ጀመረ።[13]

የሮማ ከተማ የካቶሊክ ዋና መንበር እና የሊቀ ጳጳሱ (የፖፑ) መኖሪያ ቦታ ናት ። ስለዚህ ብዙዎች ቅዱስ ጴጥሮስ እና ቅዱስ ጳውሎስ ሰማዕት ወደ ኾኑባት ወደዚህች ከተማ መንፈሳዊ ጉዞ አደረገ ። ከብዙ ቀናት ጉዞ በኋላ ሮም ደረሰ ። ኾኖም ግን የናፈቃት ታላቂቷ ከተማ ባልጠበቀው ኹናቴ አሽብርቃ አገኛት ። የኑሮው ኹናቴ እሱ ከሚኖርበት የገዳም ሥርዓት በጣም የተለየ ኾኖ አገኘው ። በነማይክል አንጀሎ ሥዕሎች የደመቀውን የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ፣ የደመቀችውን ከተማ እና ቤተ መንግሥቱን አየ ። መንፈሳውያን ናቸው የሚላቸውን የሃይማኖት መሪዎች እንደጠበቀ ኾነው ሳያገኛቸው በመቅረቱ ተሰናከለ ። ወደአገሩ ጀርመንም ተመልሶ ይህ ኹናቴ የተፈጠረበት ምክንያት በምን እንደኾነ በውል ማጤን ጀመረ።[14]

የሮም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቫቲካን ፖፕ ሊዮን 10ኛ (1513 -1521) የቅዱስ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን የሕንጻ ሥራ ማስፈጸሚያ የሚኾን ለሠዐሊዎቹ ለማይክል አንጀሎ እና ለራፋኤል የሚከፈል ገንዘብ አስፈልጎት ነበር ። በዚህ የተነሳ ከዐሥር አንድ (ግብር) በአውሮፓ ያሉት የካቶሊክ ገዳማትና ካህናት ለኃጢአት ማስተሥረያ ለሟች ቤተሰብ የንስሐ ቦታ (Indulgence)[15] እንዲኾናቸው በማለት ገንዘብ እንዲከፍሉ ተጠየቁ ። የዶሚኒካን መነኰሳትም እየተዘዋወሩ ገንዘብ መሰብሰብ ጀመሩ ። የጀርመን ሕዝብ ድህነት ሲያጠቃው ሊዮን 10ኛ እና ተከታዮቹ ግን በሀብት በልጽገው ነበር ። የጀርመኑ ተወላጅ መነኵሴ ሉተር በዚህ ባየው ነገር አልተደሰተም ፤ ሮምን ከጐበኘ በኋላ የፖፑ ብልጽግና እና የተንደላቀቀ ኑሮ አላስደሰተውም ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሻሻል እና መታደስ አለባት የሚል ሓሳብ

---

13 **Richard Hooker** Reformation Martin Luther WWW.wsu.edu/-dee

14 **Michael Collins &Matthew** *The story of Christianity New York* p.130 -133

15 (INDULGENCE) ኢንደልጀንስ ማለት ፣ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለኃጢአት ይቅርታ ወይም የተኰነነች ነፍስ በጎ ነገር ቢደረግላት ወዲያው ይቅር ተብላ ነጻ ኾና ከንስሐ ቦታ (ከፐርጋቶሪ) ትቀያለች። ከዚያም ወደ መንግሥተ ሰማይ ትገባለች ማለት ነው ። ባኹኑ ጊዜ ግን ኢንደልጀንስ ወይም ኃጢአትን የማስተሥረይ ሥልጣን ያለው ሊቀ ጳጳሱ (ፖፑ) ብቻ ነው።

አደረበት። ኹናቴውን ለመግታት እርምጃ ለመውሰድ ተነሳ። በመቀጠልም "ጀርመን የጀርመኖች ብቻ መኾን አለባት" በማለት ገንዘብ ወደ ቫቲካን እንዳይኼድ አስደረገ።

ሉተር የቅዱስ መጽሐፍ ጥናቱን እንዲኹም አስተማሪነቱን ቀጠለ ። ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክት የጻፈውን ጥሬ ንባቡን በማንበብ ትርጕሙን ሳይመለከት የተሳሳተ የክርስትና መሠረተ እምነት (ዶክትሪን) ያሠራጭ ጀመር ፤ ይኸም

> ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በርሱ ይገለጣልና (ሮሜ 1፥17 ፤ 10፥9-10)።[16]

ከሚለው ሲደርስ ማንኛውም ክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ብቻ በእግዚአብሔር ጸጋ የሚድን ነው አለ ። በእምነት ብቻ እንጂ በደጋግ ሥራዎች መዳን አይቻልም የሚለውን ሐሳቡን ገፋበት ፤ ነገር ግን

> በሰማያት ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ኹሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ። በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህ አጋንንት አላወጣንምን፥ በስምህ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን ? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዐመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ (ማቴ. 7፥21)።
>
> ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደኾነ እንዲሁ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው (ያዕቆ. 2፥20)።

የሚለውን የጌታን ቃል እና የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብን ቃል አላስተዋለም ወይም አላጤነም ነበር።

ሉተር ዐመፁን ቀጥሎ ዘጠና አምስት አወዛጋቢ ሐሳብ (ቲሲስ) አከራካሪ ጥያቄዎች አሰባስቦ በመጸፍ ጥቅምት 13 ቀን 1517 ለሊቀ ጳጳሱ (ፖፑ) ላከ ። ይህን የጻፈውን አወዛጋቢ ሐሳብ አላፊውና አግዳሚው ኹሉ እንዲያየው በዊትንበርግ ዩንቨርሲቲ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ለጠፈው፤ በያገሩም እንዲበተን አደረገ።

ሉተር ጥቅምት 31 ቀን 1517 ጀምሮ እስከ 1520 ድረስ የትችት ጽሑፉን እና ክርክሩን ቀጠለ ። የዚህ የሉተር ድፍረት የሮማ ሊቀ ጳጳስ ፖፕ ሊዮንን እና ካርዲናሎችን አስደነገጣቸው። ከካቶሊክ

[16] **Richard Wanger** *Christianity for Dummies p. 323*



ቤተ ክርስቲያን ላይ በማመፁ ከቤተ ክርስቲያኗ በውግዘት የሚለይበትን ደብዳቤ ጻፉለት ፤ እሱም ደብዳቤውን አቃጠለው ። የሮማ ፖፕ እና ባለሥልጣናት ሉተርን ማውገዝ እና ማግለል ብቻ አልበቃቸውም። ቀደም ባሉት ዘመናት ከካቶሊክ የክርስትና እምነት ያፈንግጡትን ተቃዋሚዎች በእሳት እንዳቃጠሏቸው እና በሰይፍ እንደሰየፋቸው[17] ሉተርንም ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ በእሳት ለማቃጠል እና ለማጥፋት ታጥቀው ተነስተው ነበር ። ነገር ግን ጀርመናውያን በብሔራዊ ስሜት የበላይ መኾናቸውን በመፈለግ ስለደገፉት ፤ በይበልጥም የልዑላኑ ድጋፍ ስለነበረው የተፈረደበት የሞት ቅጣት እንዳይፈጸምበት ሸሸጉት። እሱም ከሞት ከተረፈ በኋላ የጀመረውን የመሳፍንቱን ዓላማ እና የሱንም ፍላጎት ችላ ባለማለት በትጋት ይገፋበት ጀመር።

ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን በጀርመን ቋንቋ በመተርጎም አዘጋጀ፤ መዝሙሮችን ደረሰ ፤ የሚበትነውም አነስተኛ ጽሑፍ በከተሞች እና በየገበያ ቦታዎች ኹሉ ሕዝብን ያከራክር ነበር። ስለዚህም በ1521 በካቶሊክ እምነት ላይ ከፍተኛው መለያየት ደረሰ። በ1529 ፕሮቴስታንት (ተቃዋሚ) የሚለው ስም ተሰጠው ፤ ሉተር የከፍለ ዘመኑ ፕሮፓጋንዲስት ነበር ። በጊዜው ራሱን ነፃ ለማድረግ ያዘጋጅ በነበረው ፕሮፓጋንዳ ብዙ ሚልዮን የሚቆጠር የዓለም ሕዝብ ተከተለው ። በአንድ በኩል ደግሞ የጀርመን ቋንቋ እንዲስፋፉ በማድረጉ ጀርመናውያንን ጠቅሟል።

ሉተር ከጀርመን ታላላቅ ፖለቲከኞች ውስጥ አንዱ እንደነበረም ይነገራል። በሉተር ዐመፅ የተነሳ ከካቶሊክ ደጋፊዎች ጋር ጦርነት ከ1531 እስከ 1547 ድረስ ተካኼደ። በተለይም ራሱ ያስተባበረውን የገበሬዎችን ዐመፅ በመጨረሻ በመክዳቱ እና የመንግሥት ጦርን በመደገፉ ገበሬዎችም የፖፕ ዋና ረዳቶች እና ተወካዮች ዳቢሎሶች ናቸው በማለት እንዲጨፈጨፉ አስደረገ። በደረሰባቸው ግፍ እሱን ተከትለው ከነበሩት በኋላ የጠሉት አናባፕቲስት እምነት እንዲመሠረት መንገድ ከፍቷል። (ስለ አናባፕቲስት ወደፊት እናያለን) ገበሬዎቹን ብቻ አይደለም አይሁዳውያን ወንጌልን ለመቀበል እንቢተኛ በመኾናቸው ታድነውም

[17] Inquisition ኢንኩዚሽን ማለት ፥ በቀድሞ ጊዜ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እና እምነት የማይስማማውንና ያፈነገጠውን ሰው በንስሐ ካልተመለሰ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ በእሳት ይቃጠላል፤ እንዲሁም በተለያየ መንገድ ስቃይ ይደርስበት ነበር።

እንዲፈጁ ፣ ምላሳቸው ከሥሩ እየተቆረጠ እንዲጋዙ ፤ ዜግነታቸው ተገፎ ከጀርመን መባረር አለባቸው በማለት አስወስኖባቸዋል። ይህም ለበኋላው ለሒትለር ጭፍጨፋ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል ብለው ብዙዎች የታሪክ ሊቃውንት ይናገራሉ ። ቆየት ብሎም ምንኩስና አያስፈልግም በማለት አስተምሯል።

> ስለስሜ ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ኹሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል ፤ የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳል (ማቴ. 19፥29)።
> በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ራሱን ይካድ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ፥ (ማር. 8፥34)።

የሚለውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል እፈጽማለሁ ብሎ ተገንዞ፣ ታጥኖ ለምንኩስና በቃለ መሐላ ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ፤ የገባውን ቃል ኪዳኑን አፈረሰ ። ከዚያም ካትሪንን የምትባል መነኩሲት አግብቶ ስድስት ልጆች ወልዷል፤ በመጨረሻም በልብ ድካም በ1546 ሞተ።

የሉተር የተሐድሶ እምነት ከጀርመን ውጭ በዴንማርክ፣ በኖርዌይ፣ በስዊድን ከዚያም ወደ አሜሪካ በኀይልና በተለያየ መንገድ ተሰብኮ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ በየአገሩ ተዛመተ ። በዚሁ ዘመን ውስጥ እንደገና ሌላ የተሐድሶ መንፈስ ሲዊዘርላንድ ውስጥ ከሉተር ትንሽ ለየት ባለ መልክ በዝዊንግሊን እና በካልቪን መስፋፋት ጀመረ።

## (፪) ተሐድሶ በስዊዘርላንድ

የስዊዘርላንድ ተሐድሶ መሥራቾቹ ዝዊንግሊን እና ካልቪን ይባላሉ ። ዝዊንግሊን ከካቶሊክ ገበሬ ቤተሰብ በ1484 የተወለደ ነው ። በ1506 የዩንቨርስቲ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ክህነት ተቀብሎ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ነበር። በ1518 የዙሪክ የካቶሊክ ካቴድራል ሰባኪ ኾኖ ተመደበ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለጻድቃን የሚደረገውን ስግደት ፤ በበጎ እና በደጋግ ሥራዎች መዳን ፤ የፐርጋቶሪን መኖር፤[18]

[18] (PURGATORY) ፐርጋቶሪ ማለት፥ በካቶሊክ የክርስትና ትምህርት ጊዜያዊ የኃጢአተኞች የቅጣት ቦታ እና ይቅርታም የሚደረግበት ቦታ ነው ። ሙታን ወደመንግሥተ ሰማይ ከመግባት በፊት በዕረፍት ቦታ (መካነ ዕረፍት) በፐርጋቶሪ ይቆያሉ።



አጽዋማትን፣ ማዕርገ ክህነትን፣ ምንኩስናን፣ ሥርዓተ ቅዳሴን፣ ቅዱሳን ሥዕሎችን፤ የፖፑን የበላይነት እና ሥልጣን በመቃወም አስተማረ ። በዙሪክ የተወሰኑ ነዋሪዎችም በትምህርቱ ተደሰቱ። በ1522 ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በመውጣት የተሐድሶ (ሪፎርምድ) ቤተ ክርስቲያን በዙሪክ ከተማ አቋቋመ። ከዚህ ከዝዊንግሊን ሞት በኋላ ጆን ካልቪን የሚባለው በቦታው ተተካ።

ጆን ካልቪን ፈረንሳይ ውስጥ ኖዮን እተባለች ከተማ በ1509 የተወለደ ነው ። በኦርሌአንስ ዩንቨርስቲ የሕግ ተምህርት ተምሮ በጥብቅና ተግባር ከተሠማራ በኋላ ፤ በፓሪስ የነገረ መለኮት (ተዮሎጂ) ትምህርት እንዲሁ ላቲን፣ ግሪክ፣ ዕብራይስጥ ቋንቋዎችን አጠንቷል። ከፕሮቴስታንቶች ወይም ከሉተር ተከታዮች ጋራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በአንድ ላይ ማጥናት ጀመረ ። ቀስ እያለ ከፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ጋር በመተባበር የሊቀ ጳጳሱን (የፖፕ) የበላይነት በቅዱስ መጽሐፍ ያልተደገፈ መኾኑን ይናገር ጀመር።[19]

ካልቪን እንደ ሉተር የክርስትና እምነት መገኛ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ መኾኑን እና ቀሳውስት (ካህን) ኹሉም ሰው መኾን ይችላል አለ። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ፣ የጻድቃን ፣ የመላእክት አማላጅነትን ካለመቀበሉም በላይ ቅዱሳት ምስሎች ከቤተ ክርስቲያን እንዲወገዱ መንበር እንዲነሳ ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመስበኪያ ቦታ (Pulpit) ብቻ እንዲኖር አደረገ ። ይኽን ትምህርት እና ትእዛዝ የማይፈጽመውን የሚወገዝ እና ቅጣት የሚፈጸምበት መኾኑን የሚደነግግ ሕግ አወጣ ። በዚህ ዐዲስ ነገር የተነሳ በጄኔቫ ውስጥ ከባድ የመከፋፈል ችግር ተፈጠረ። ከፈረንሳይ ቀጥሎ እንደ ኹለተኛ አገሩ የሚያያት ስዊዘርላንድ ጄኔቫ ከተማ ውስጥ ለ24 ዓመታት አስተማረ።

የእስፓኝ ተወላጁ ሚካኤል ሴርቡቴስ የሥላሴን አንድነት እና ሦስትነት በመካዱ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተይዞ በእሳት እንዲቃጠል ተፈርዶበት ሳለ ከታሰረበት ጠፍቶ ገኔቫ በመግባት ጆን ካልቪን ጋራ ተገናኘ ። ጆን ካልቪን ግን ተቃዋሚዎች ያስነሳብኛል ብሎ ስለሰጋ ሊያስጠጋው አልፈለገም። በ1553 ከከተማዋ ባለሥልጣናት ጋራ በመስማማት ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አሳልፎ በመስጠት በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አደረገው፤ (ኢንኩዚሽን)።

[19] Michael Collins &Matthew *The story of Christianity New York* p. 136 - 137

በሌላ በኩል ደግሞ ጆን ኮኖክስ የሚባለው የእስኮትላንድ ዜጋ ከጆን ካልቪንጋራ ይሠራ ነበር ። በ1559 ከስዊዘርላንድ ወደ እስኮትላንድ ሲመለስ አዲስ የፕሮቴስታንት ስብስብ ፈጠረ፤ ይኸን ስብስብ ፕሬስቤተርያን ብለው ጠሩት ። በ1560 ፕሬስቤተርያን የእስኮትላንድ ቤተ ክርስቲያን ተባለ። (ታሪኩን በክፍል ኹለት እናየዋለን)

ሉተር ቤተ ክርስቲያን በልዑላን ሥር እንድትተዳደር ሲያደርግ፤ ዝዊንግሊ ቤተ ክርስቲያን እና መንግሥት ባንድነት እንዲሠሩ ለማድረግ ሞክሯል ። ጆን ካልቪን ግን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመተዳደር ያገሩ መንግሥት ጣልቃ ሳይገባ እና ተፅዕኖ ሳይኖርባት እንድትሠራ አስተምሯል። ይህ የጆን ካልቪን ትምህርት እና እምነት የአሜሪካ ሃይማኖት እና ሕገ መንግሥት መሠረት ነው።

ጆን ካልቪን በ1559 የጀኔቫን አካዳሚ ከፈተ። በዚህ አካዳሚ የእንግሊዝ ተማሪዎች እና የአውሮፓ ተማሪዎች መማር ጀመሩ ፤ በዚህም የተነሳ ትምህርቱ አውሮፓን አጥለቀለቀ ። ይህ መንግሥት እና ቤተ ክርስቲያን ይለይ የሚለው የጆን ካልቪን ሓሳብ እንግሊዝም ገብቶ መበጣበጥ ጀመረ ። ይኹን እንጂ የጆን ካልቪንን ሐሳብ ተቃዋሚዎች ብዙዎች ስለነበሩ አይኹንም በማለት ጥንካሬ አሳዩ ። በዚህም መግባባት ያልቻሉት አኩራፊዎቹ እምነታቸውን ይዘው ዐዲሲቷ ዓለም ተብላ ወደምትጠራው አሜሪካ፣ ካናዳና ሜክሲኮ ለመሰደድ ተገደዱ።

አንደኛው ትልቁ የአሜሪካ እምነት የተመሠረተው ስደተኞች ከአውሮፓ ይዘው በገቡት በጆን ካልቪን እምነት ተከታዮች ነው።[20]

## (፫) ተሐድሶ በእንግሊዝ

የእንግሊዝ ተሐድሶ የተጀመረው በእንግሊዙ ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ (1509–1547) ነው ። ይህ ንጉሥ የሉተርን እንቅስቃሴ በመቃወም መጽሐፍ በመጻፍ ለካቶሊኩ ሊቀ ጳጳስ (ፖፕ) ሊዮን በለታገለለት ለዚህ ወሮታው ይኾን ዘንድ የቤተ ክርስቲያኒቷ የበላይ ጠባቂ (Defender of the Faith)[21] የሚል ሥልጣን ተሰጠው ። ይህን ሥልጣን የእንግሊዝ

[20]በ1582 ፖፕ ጎርጎሪዮስ የቀን አቆጣጠርን ዐደሰ፤ ታላቋ ብሪታንያና (የአሜሪካ ቅኝ ገዢ) በ1752 ይኸን የጎርጎርዮስን ቀን አቆጣጠር ተቀበሉት። David E.D. *The Calendar 1988*

[21] *The Modern Age vol. 2 p. 139*



ነገሥታት እስከ ዛሬ ድረስ ይጠሩበታል ። የብሪታንያ ሳንቲሞች "የእምነቱ የበላይ ጠባቂ" በላቲን ቋንቋ F.D. (FIDEE DEFENSOR) የሚል ተቀርጾ ተጽፏል ። በአኹኑ ጊዜም በብሪታንያ ንግሥት ኤልሳቤጥ ምስል አናት (ሳንቲም) ላይ ተጽፎ ይገኛል ። ነገር ግን ማንም ሰው ምስሉን ከማየት በስተቀር ጽሑፉን ሥራዬ ብሎ ስለማያጤነው ብዙ የሚታወቅ ነገር አይደለም።

ይህ የእንግሊዝ ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ የእስፓኝ ገዢዎች ነገሥታት ከነበሩት የፌርዲናንድ እና የኢዛቤላን ልጅ ልዕልት ካትሪንን አገባ ። ይህች ሴት የመጀመሪያ ሚስቱ ነበረች ። ቤተሰቦቿ ፌርዲናንድ እና ኢዛቤላ ቀደም ሲል ዐዲሲቷን ዓለም (አሜሪካ) ያገኛት ክርስቶፎር ኮለምበስን የባሕር መንገድ እንዲፈልግ የላኩ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ንጉሥ እና ንግሥት ናቸው።

ይህች የእንግሊዝ ንጉሥ ሄነሪ ያገባት ካተሪን በመጀመሪያ ሜሪ የምትባል ሴት ልጅ ወለደች። በድጋሚ የወለደችው ወንድ ልጅ ግን ሞተ። ንጉሡ ግን መንግሥቱን የሚወርስ ወንድ ልጅ ለመውለድ ቢጓጓም ንግሥት ካተሪን ልትወልድለት አልቻለችም ። በዚህ የተነሳ ለ24 ዓመት በጋብቻ አብሯት የኖረውን ሚስቱን ፈትቶ ወጣቷን አን ቦሊይን ለማግባት ፈለገ ። በካርዲናል ቶማስ ዌልሴይ በኩል ከሮም ፖፕ የፍች ፈቃድ ጠይቆ ተከለከለ። በጋብቻ ፍች ምክንያት ኹለተኛ ሚስት ማግባት እንደማይችልና ይህን ቢያደርግ ከዙፋኑ እንደሚወርድ ንግሥናው እንደሚፈርስ ተነገረው ። በዚኹን ጊዜ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመለየት ዓላማውን በእንግሊዝ ፓርላማ አስወሰነ ።

በንጉሡ ግፊት በተመሩት የፓርላማው አባላት ውሳኔ መሠረት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተለይታለች በማለት ሮምን ጨርሶ ላለማንሳት የአንግሊካንን ሃይማኖት በ1530 መሠረቱ። ይህ ከካቶሊክ መገንጠል በፓርላማ መጽደቁ መንፈሳዊ ሳይኾን የራሱን ዓላማ ለማስፈጸም የተደረገ ፖለቲካዊ ተግባር ነበር።

ሉተር ያሠራጨው መልእክት በአገሪቷ ገብቶ ስለነበረ ንጉሥ ሄንሪ 8ኛ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመገንጠሉ ብዙ ተቃውሞ አልደረሰበትም። የሉተር እና የካልቪን ዐዲስ ትምህርት ለእሱም መንገድ ከፈተለት። ለፖፑ የሚላከው ገጸ በረከት ዐሥራት ተቋረጠ። የእንግሊዙ የካቶሊክ ተጠሪ ካርዲናል ከሥልጣኑ ተወገደ።

ንጉሡ ሄንሪ በ1533 ሐሳቡን የሚደግፈውን ቶማስ ክራንሜር የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ከእሱ ቀጥሎ በበላይነት እንዲመራ የካንተርበሪ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾመው ። በኋላ በዚኹ በሊቀ ጳጳስ ቶማስ ክራንሜር ትእዛዝና ፈቃድ ከመጀመሪያ ሚስቱ ካተሪን ጋር የነበረው ጋብቻ ፍቺ ተደረገ ። ከዚያም ኹለተኛ ሚስት አን ቦሊይን አገባ ። እሷም ሴት ልጅ ኤልሳቤጥን ወለደች ። አኹንም የፈለገው ወንድ ልጅ አልተገኘም። ቆይት ብሎ የኤልሳቤጥ እናት አን ቦሊይን አመነዘረች በሚል ሰበብ አንገቷን (በታወር ኦፍ ለንደን) አስቆረጣት። ቀጥሎም ለሦስተኛ ጊዜ ሴይሙርን አገባ። እሷም ኤድዋርድ የሚባል ወንድ ልጅ ወለደች ። በዚህ ጊዜ የመንግሥቱ ወራሽ የሚኾን ወንድ ልጅ አገኘ።

ንጉሡ ሄንሪ የእሱን የቤተ ክርስቲያን የበላይ ምሪ መኾን የተቃወሙና ታማኝነታቸውን በቃለ መሐላ ለመግለጽ አሻፈረን ያሉትን ፤ የካቶሊክ ተከታዮች ታማኙ ቶማስ ሞር እንዲሁም ጆን ፊሽርን አንገታቸው እንዲለየፉ አስደርጓል ። እነዚህ ሰዎች በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሰማዕታት ተብለው ይጠራሉ ። ሌሎቹ ክህናት ግን ንጉሡን በመፍራት የቤተ ክርስቲያኒቷ የበላይ ጠባቂ መኾኑን አምነው በቃለ መሐላ አረጋገጡ።

ንጉሡ ሄንሪ ሲሞት ከሴሙር የተወለደ ወንድ ልጁ ኤድዋርድ 6ኛ ነገሠ።[22] የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ ቶማስ ክራንሜር ኤድዋርድ ንጉሥ ኾኖ እንግሊዝን እንዲመራ ይረዳው እና ይደግፈው ነበር ። ነገር ግን ኤድዋርድ ጤንነት ስላልነበረው በልጅነቱ ሞተ ።

ከኤድዋርድ ዕረፍት በኋላ ለንጉሥ ሄንሪ ካተሪን የወለደችለት የመጀመሪያ ሴት ልጁ ሜሪ የእንግሊዝ ንግሥት ኾነች ።[23] የካቶሊክ እምነት እንደገና በኀይል በእንግሊዝ አገር ተስፋፋ ። ንግሥት ሜሪ እንደ እናቷ እንዲኹ የእስፓኝ የካቶሊክ ነገሥታት እንደነበሩት አያቶቿ የካቶሊክን ሃይማኖት ትወድ ስለነበረ የሮሙን ፖፕ መንበር ለመመለስ ቆርጣ ተነሳች ። ብዙዎቹ እንግሊዛውያን ካቶሊክ እንዲመለስ የሚፈልጉት ደገፏት ። የእንግሊዝ አገርን ከእስፓኝ ግዛት ሥር ለማዋልና ቤተ ክርስቲያኒቱም በሮሙ ፖፕ ሥር እንዲኾን በ1554 በዕድሜ

[22] የኤድዋርድ የንግሥናው ዘመን 1547 -1553

[23] የንግሥት ሜሪ የንግሥና ዘመኗ 1553-1558



11 ዓመት የሚያንሳትን ቻርለስ 5ኛ የሚባለውን የንጉሥ ልጅ ዳግማዊ ፊሊፕን አገባች፤ እሱም በጣም አጥባቂ ካቶሊክ ነበር።

ንግሥት ሜሪ የእናቷን ፍች ወስኖ ያጸደቀውን ሊቀ ጳጳስ ቶማስ ክራንሜር በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት በማዘዝ ብቀላ ተበቀለች። እሷ በነገሠችበት በዐምስት ዓመታት ውስጥ የነበሩ ካህናቶች እና ምእመናኖች ፕሮቴስታንት ተብለው የተጠረጠሩ ኹሉ ወደ 280 የሚደርሱ የካልቪን ተከታዮች በኦክስፎርድ የጥንታዊ ከተማ በእሳት እንዲቃጠሉ አስደረገች ። በአገሩ ነጻነት ባለመኖሩ አብዛኛው የእንግሊዝ ሕዝብ ደስተኛ አልኾነም ። በዚህ ጊዜ የካቶሊክ የክርስትና እምነት በጣም እየተጠላ ኼደ ። የእንግሊዝ ሕዝብ ደም አፍሳሿዋ ሜሪ (Bloody Mary) በማለት ይጠራት ጀመር ፤ ሜሪ ዙፋኗን የሚወርስ ዘር ሳትተካ ዐምስት ዓመት ነግሣ በ1558 ሞተች።

በንግሥት ሜሪ ምትክ የአን ቦሊይን ልጅ ኤልሳቤጥ ቀዳማዊት ንግሥት ኾነች፤[24] ማንኛውንም የጋብቻ መንገድ መፈጸም ፖለቲካዊ መጠቀሚያ ኾኖ ስላገኘችው ለክብሯ ስትል "ድንግሊቷ ንግሥት" (Virgin) የሚለውን የቅጽል ስም ይዞ መኖርን መረጠች ። ኤልሳቤጥ ጳጳሳትን ፣ ቀሳውስትን እንዲኹም ቅዱሳን እና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶችን አልተቃወመችም። የሮማ ካቶሊክ ሥርዓተ ጸሎት ብትወድም እንኳ ለዙፋኗ ተቀናቃኞች እና የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን አንግሊካን ተብሎ መገንጠል ስለማይደግፉ እሷም ወደ አባቷ እምነት በማዘንበል "የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ" የሚለውን የማዕረግ ሥልጣን ጨበጠች።

አብዛኛው የእንግሊዝ ሕዝብ ኤልሳቤጥን ከመውደዱ የተነሳ ለኤልሳቤጥ ሲሰግድ ለአገሩ ለእንግሊዝ እንደ ሰገደ ይቆጥረው ነበር። እሷም ለሕዝቦቿ ስትል ትዳር ሳትመሠርት አገሯን አግብታ ኖረች ይኗታል ። ወደፊት እንደምናየው በአሜሪካም የመጀመሪያ የእንግሊዝ ሠፋሪዎች ሲሠፍሩ ለዚህች ንግሥት የሠፈሩበትን ቦታ "ቨርጂንያ" ብለው ለክብሯ መታሰቢያ አድርገው ሰየሙ ። ዛሬ ኹለቱ ግዛቶች ኖርዝ ቨርጂንያ እና ዌስት ቨርጂንያ በመባል ይጠራሉ ።

ሌላው ድንግል ተብላ የተጠራችበት ምክንያት ደግሞ ከላይ እንደ ተገለጸው ፖለቲካዋን ለመጠበቅ ሲኾን ፤ አንዳንዶች ደግሞ

[24] የንግሥት ኤልሳቤጥ ቀዳማዊት የግዛት ዘመኗ 1558–1603፤ የኖረችበት ዘመን ከ1533 እስከ 1603 ነው።

የሚሉት ፕሮቴስታንቶች ጸረ ማርያም ስለኾኑ ካቶሊኮችን ለማበሳጨት እና ለማናናቅ ኾን ተብሎ የተሰየመ ነው የሚሉም አሉ ። ካቶሊኮች ድንግል ማርያምን ያከብራሉና በአሜሪካ የሠፈሩበትን ቦታ ሜሪ ላንድ (አገረ ማርያም) በማለት ሰይመዋል ፤ ኹለቱም የተቀራረቡ ግዛቶች ናቸው።

ንግሥት ኤልሳቤጥ ቀዳማዊት 45 ዓመት ከነገሡ በኋላ በ1603 ሞተች። በምትኳ ዙፋኑን የሚወርስ ልጅ አልነበራትም። በዚህ የተነሳ ዘር ቆጥረው በእስኮትላንድ በኤደንብራ የሄንሪ 7ኛ የልጅ ልጅ የእስኮትላንድ ንግሥት ሜሪ እና የሎርድ ዳርነሌይ ልጅ የኾነ ቀዳማዊ ጀምስን አነገሡት ። ጀምስ የተወለደው ሰኔ 19 ቀን 1566 በእስኮትላንድ ቤተ መንግሥት ነው።

ጀምስ ንግሥት ኤልሳቤጥ ቀዳማዊት ከሞተች ጊዜ ጀምሮ የእንግሊዝ ንጉሥ ኾነ።[25] ከዚያም እንግሊዝን እና እስኮትላንድን በማዋሐድ አንድ መንግሥት አድርጎ ለመግዛት "ታላቋ ብሪታንያ" በማለት ኹለቱን አገሮች ጠቅሎ ነገሠ ። ኾኖም ግን በርሱ ንግሥና ዘመን ብዙ የእንግሊዝ የፕሮቴስታንት ቡድኖች አልተደሰቱም ። የጆን ካልቪን መንፈስ ይዘው የሚንቀሳቀሱት ፕሮቴስታንቶች በተለየ ስማቸውም ፒዩሪታንስ የሚባሉት በፓርላማው ውስጥ ሳይቀር ተሰግስገው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ እምነት እና ሥርዓት በደንብ አልጠራችም እና ከጥቃቅን ነገሮች ኹሉ መጥራት አለባት ይሉ ነበር።

የጆን ካልቪንን ሐሳብ ተከትለው የሚንቀሳቀሱት በተለየ ስማቸው ፒይሪታንስ የሚባሉት በዚህ በንጉሡ ጀምስ ዘመን ከቀድሞው የበለጠ በጣም ጠነከሩ ። አብዛኛዎቹ በፓርላማ ውስጥ ያሉ የፓርላማ አባላት ነበሩ ፤ ንጉሡ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ስለኾነ የፈለገውን ጳጳስ እንዲያከብር እና እንዲሾም አልፈለጉም ። የበላይ ጠባቂያችን "ንጉሥ ክርስቶስ ነው" ይሉት ነበር። እሱም በበኩሉ እነዚኽን ተቃዋሚዎቹን ነጻነታቸውን ገፈፈ ። ጸቡም እየተካረረ ስለመጣ ግማሾቹም ወደ ሆላንድና በየጊዜው ወደ ዐዲሷ ዓለም (አሜሪካ) መሰደድ ጀመሩ።

በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሡ ጀምስ ቀዳማዊ ፕሮቴስታንት አንግሊካን በመኾኑ የሚቃወሙት የካቶሊክ ቡድኖችም ነበሩ ። የሚፈልጉት የካቶሊክ ንጉሥን ማንገሥ ነበር። በዚህ የተነሳ ኅዳር 5 ቀን 1605

[25] የንጉሥ ጀምስ የግዛት ዘመን 1603–1625



ካቶሊካዊ የኾነ ጋይ ፎክስ የሚባል ሰው ከጓደኞቹ ጋር ንጉሥ ጀምስን እና ፓርላማው ውስጥ ያሉትን ፕሮቴስታንቶች ሊያጠፉአቸው ሴራ አደረጉ ። ንጉሡ ጀምስ በዚህ ቀን የፓርላማ ጉባኤውን ሊከፍት ለማጥፋት ሠላሳ ስድስት ሳጥን ፈንጂ በፓርላማው ምድር ቤት በማዘጋጀት አጠመዱ። ነገር ግን የተጠመደውን ፈንጂ ለማፈንዳት ሳይሳካለቸው ወሬ ተሰምቶ ከሸፈ፤ ጋይ ፎክስ እና ስምንቱ ጓደኞቹ በንጉሡ ወታደሮች ተያዙ ። በዓመቱ የሞት ቅጣት ተበየነባቸው ፤ ሕዝቡም ይህንን ሲሰሙ ደስታቸውን ገለጹ ። ንጉሣችንን ጀምስን ያኑርልን እያሉ ችቦ እያበሩ በከተማው እየተዘዋወሩ ይጨፍሩ ጀመር። ይህ በዓል በኅዳር አምስት ቀን ጋይ ፎክስ እየተባለ በብሪታንያ በታላቅ ድምቀት ይከበራል። በዚህ ንጉሡን ለማጥፋት በተደረገው ሸመቃ በካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ የእንግሊዝ አገር ሕዝቦች ተጨማሪ ከፍተኛ ጥላቻን አሳደሩባቸው ። በኋላ እንደምናየው ብዙ የካቶሊክ እምነት ተከታዮችም በዚህ ጥላቻ የተነሳ ወደ አሜሪካ ተሰደዋል።

ካቶሊኮችን ጨምሮ ከእንግሊዝ ብዙ የተለያዩ ቡድኖች በተለያየ ኹኔታ አትላንቲክ ውቅያኖስን በአደገኛ ኹኔታ አቋርጠው ዐዲሲቷ ዓለም አሜሪካ ገብተዋል። ከእነዚህ ቡድኖች መካከል በጣም ዕውቅና ያላቸው የአራሽ የገበሬዎች ቡድን እና የሃይማኖት ቡድን ተብለው የሚጠሩ የመጀመሪያው የእንግሊዝ ሰፋሪዎች እና ስደተኞች ይገኛሉ።

# ምዕራፍ ፫
## የእንግሊዝ ተሐድሶ ወደ አሜሪካ መሰደድ

በቀድሞው ጊዜ የአውሮፓ ኀያላን መንግሥታት እስፓኝ፣ ፈረንሳይ ፣ እንግሊዝ፣ ኔዘርላንድ እና እስካንድኔቪያን ነበሩ ። እስፓኝ እና ፖርቹጋል[26] የመጀመሪያዎቹ የአሜሪካ ቅኝ ገዢዎች ናቸው። ከ1513 ጀምሮ እስፓኝ ፍሎሪዳን ይዛ ነበር። ከዚያም በ1682 ቴክሳስን ፤ በ1769 ካሊፎርንያን ያዘች ። ፖርቱጋሎች የካቶሊክ እምነታቸውን ይዘው በደቡብ

[26] በ16ኛው ክ. ዘመን ፖርቹጋሎች በኢትዮጵያ ላይ አይናቸውን የጣሉበት ዘመን ነው። ግራኝ መሐመድ ለዐሥራ ዐምስት ዓመት ኢትዮጵያን ወሮ የቆየበት ዘምን ነው። (1514 ዓ. ም.)

[26] David Mauk and John Oakland *American Civilization an introduction (New York 1997).,* *354*

እና በመካከለኛው የአሜሪካ ክፍል እየተሰደዱ በመስፋፋት በቅኝ ግዛት ያዙ።[27]

ፈረንሳይ ከ1524 ጀምሮ መካከለኛውን እና ሰሜኑን የአሜሪካ ምድር ከሚሲሲፒ ወንዝ እስከ ካናዳ ድረስ በቅኝ ግዛት ይዛ ነበር ። እንግሊዝ እና ፈረንሳይ በዚህች ዐዲስ ዓለም አሜሪካ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ከፍተኛ ውድድር አደረጉ ። እንግሊዛውያንም ከ1587 ጀምሮ እንደተጠቀሱት አገሮች ኹሉ የመስፋፋት እና የዘመኑ ፍላጎት አደረባቸው።

## (፩) የአራሽ ገበሬዎች ቡድን

የአራሽ ገበሬዎች ቡድን በመባል የሚታወቁት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ አማንያን (አንግሊካኖች) ነበሩ። በለንደን ከተማ ለዚሁ ጉዞ በተደራጀው ኩባንያ አማካኝነት ገንዘብ ወጭ ተደርጎ 144 ሰዎች ሦስት መርከቦች ላይ ተሣፍረው ወደ አዲሲቷ ዓለም ተጓዙ ። ይዚህ የአራሽ ገበሬዎች ቡድን ግንቦት13 ቀን 1607 ጉዞ ሲጀምሩ የያዙት የጉዞ መመሪያ ቀደም ብሎ በ1605 የተነደፈው የዓለም ካርታ ነበር ፤ ይህም ካርታ በዊልያም ጃንስዞን ብሌዩ የተነደፈ ነው።[28]

በዚህ ካርታ ላይ የሰፈረው ንድፍ እንደሚያሳየው ዛሬ አትላንቲክ በመባል የሚጠራው ውቅያኖስ "ኢትዮጵያ ውቅያኖስ" ተብሎ ይጠራ ነበር። ይህም ማለት እንደ ህንድ ውቅያኖስ ማለት ነው። እስከ 17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የተነደፉት ብዙ ካርታዎችም ውቅያኖሱን ኢትዮጵያ ውቅያኖስ በሚል ስያሜ ይጠሩት ነበር። ይህ ሊኾን የቻለው ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጠቀሷ ፤ እንዲሁም የክርስቲያን አገር በመኾኗ ፤ ነገሥታቶቿ ክርስቲያን መኾናቸው እና ከአውሮፓውያን ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው፤ ቀደም ብሎ ጀምሮ ታላቅ አገር መኾኗ ይታወቅ ስለ ነበረ ነው።


እነዚህ የእንግሊዝ የአራሽ ገበሬዎች ቡድን ይኾን የቀድሞ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ የዛሬውን አትላንቲክ አቋርጠው ከብዙ እስጨናቂ ጉዞ በኋላ በምሥራቁ የአሜሪካ ክፍል ሠፈሩ። እነዚህ ገበሬዎች በአሜሪካ የመጀመሪያዎቹ የእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ናቸው ። ዋና

[27] *The new Encyclopedia Britannica 2002 P.,* **Jeffrey B. Webb,** *the complete Idiot's Guide to Christianity (New York 2004) p., 58*
[28] William Janszon Blaeu BLAEU WALL MAP



ዓላማቸው ግዛት ለማስፋፋት እና ሀብት ወርቅ ፍለጋ እንዲሁ ሃይማኖት ለመስበክ ነበር ። በዚህ በሰፈሩበት ቦታ የቅኝ ግዛት ከተማ መሠረቱ ። የክርስትናን እምነት ላልተቀበሉ ሰዎች እንሰብካለን የሚል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወዲያው ከመርከቢቷ እንደ ወረዱ አምልኮታቸውን ለመጀመር በካፒቴን ስሚዝ እንዲሁም በቄስ (ሬቨረንድ) ሮበርት ሀንት መሪነት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ።[29]

ንጉሡ ጀምስ የቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ጠባቂ (Defender of the Faith) ስለኾነ በዚሁ በመሠረቱት ቤተ ክርስቲያን በጸሎታቸው "ንጉሡን እግዚአብሔር ያኑርልን፥ ይጠብቅልን" እያሉ ስሙን መጥራታቸውን ቀጠሉ ። ነገሥታት የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ በመኾናቸው በጸሎት መጥራት የጥንታውያን አብያተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠፉትን ፣ ክርስቲያንን የሚያሳድዱትን ኃያላን (አላውያን) ነገሥታትን አይጠሩም። (ቲቶ 3፥1 ፤ 1ኛ ጴጥ. 2፥13)



በቨርጂንያ ቢች በጀምስ ታውን የተመሠረተው
የመጀመሪያው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን።

እነዚህ ሰዎች የመኖሪያ ቦታቸውን በዚሁ በእንግሊዝ ንጉሥ ስም "ጀምስ ታውን" ብለው ጠሩት። ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ የኾኑት ዐዲስ ሰፋሪዎች ከአገሬው ተወላጆች ከኢንድያኖች ጋር ሊግባቡ አል

[29] *The Modern Age vol. 2 p. 203*

ቻሉም ፤ በዚህም የተነሣ ውጊያ ጀመሩ ። ከአራሽ ገበሬዎቹ በዙዎች በጦርነቱ ቆሳሰሉ ። በበሽታ እና በቂ ምግብ በማጣት በረሀብ ያልቁ ጀመር።

ፖካሆንታስ የምትባል የኢንድያኖቹ አለቃ ሴት ልጅ የካፒቴን ጆን እስሚዝ ጓደኛ ኾነች። ቀስ በቀስም እሷን እና የተወሰኑትን እንዲያኖችን ወንጌል ተሰብከው በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን (አንግሊካን) እምነት አጥምቀው አማኞች እንዲኾኑ አደረጓቸው ። ፖካሆንታስ ካፒቴን ጆን እስሚዝን እና ሌሎችን እንግሊዞች በጣም ትረዳቸው ነበር ። በኋላ ደግሞ ጆን ሮልፍ የሚባለው እንግሊዛዊ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አግብቷት ወደ እንግሊዝ አገር አብረው በመጓዝ በዚያ ኑሮ ጀመሩ፤ ኾኖም ግን ወደ አሜሪካም ሳትመለስ ከዓመታት በኋላ በእንግሊዝ ዐረፈች ። ዛሬ በትልቁ የካፒቶል ሕንጻ ውስጥ በኰንግረስ አዳራሽ ፖካሆንታስ በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን እምነት ስትጠመቅ የሚያሳይ ሥዕል በግድግዳ ላይ በሞዛይክ ተሥሎ ይታያል።

ዐዲሶቹ የእንግሊዝ ገበሬዎች ቀስ እያሉ ለመዱ። በቀላሉ ትንባሆ፣ ጥጥ ፣ ሸንኮራ አገዳ እንደሚመረት በይበልጥ ለትንባሆ እርሻ የሚስማማ መሬት መኾኑን ተረዱ ። እነዚህ ዘሮች እንዴት እንደሚመረቱ ትምህርት ያገኙት ከተወላጆቹ ኢንዲያን ነበር። በዚህ የተነሳ ከአውሮፓ እና ከአፍሪካ የሰው ጉልበት አስፈለገ ፤ በመጀመሪያ በመቅጠር በኋላ ግን በገንዘብ እየገዙ የጉልበት ሥራ ማሠራት ተጀመረ ። እያደር ይህ ተግባር የባርነት ሥርዓትን ፈጠረ ። ትንባሆ ማጨስ የዘመኑ የአውሮፓ እና የአሜሪካ ባህል (ፋሽን) ኾነ ። በዚህ የተነሳ የአሜሪካ የትንባሆ ገበያ ደራ ፤ በአውሮፓውያን ዘንድ በጣም ተወዳጅ ኾነ፤ የገበያውም ስም "ወርቃማው የሬከታንግሉ ንግድ" ተባለ፤ የብሪታንያ መንግሥት ሀብት ፍሰጋ ተሳካ።[30]

[30] *ትንባሆ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይጨስ ያደረጉ እና በሲኖዶስ ያስገዘቱ ዐፄ* ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው። በአኹኑ ዘመን ትንባሆ ማጤስ በአሜሪካ እና በአውሮፓ ጤንነትን ይጎዳል ዕድሜንም ያሳጥራል በሚል የተወገዘ እና የተጠላ ኾኗል ። ከዘመናት በፊት ግን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እና ነገሥታት ዘንድ የተወገዘ ነው። (መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ገጽ 77)



ንጉሡ ጀምስ[31] መንግሥቱ እንዲረጋጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትርጉም አንድ እንዲኾን በፓርላማ ተጠየቀ ፤ እሱም በጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ፣ ከግሪክ እና ከላቲን እየተነፃፀረ እንዲተረጐም አዘዘ። በትእዛዙ መሠረት በካህናት ጉባኤ ውሳኔ በተመረጡ ሊቃውንቶቻቸው ዐዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተተርጐሞ በመከናወን ሥራው በ1611 ተጠናቀቀ። ሕዝቡ ትክክለኛ ትርጉሙን በጉጉት ይጠብቅ ነበር ። ተተርጕሞ ካለቀ በኋላ ንጉሡ የበለጠ ክብር አገኘ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ "የኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ" ተብሎ ይጠራል
[32]

ይህ የኪንግ ጀምስ መጽሐፍ ቅዱስ በአሜሪካ እና በመላው ዓለም ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ነው ተብሎ ይገመታል ። በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢትዮጵያ የሚለው ስም 45 ጊዜ ተጠቅሷል።

እግረ መንገዳችንን ለመጥቀስ ያህል ይህ ወቅት (1600 ዓ.ም - 1625 ዓ.ም) ጀስዊች የሚባሉት የካቶሊክ መነኰሳት ለወንጌል ስብከት ወደ ኢትዮጵያ (ሚሽን) የገቡበት ዘመን ነበር። በወቅቱ ኢትዮጵያን ያሚመሩት አፄ ሱስንዮስ ነበሩ። ይህ ወቅትበኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና በካቶሊክ እምነት ተከታዮች መካከል ታላቅ አለመግባባት ተፈጥሮ መጤዎቹ ሰባክያን ከዐፄ ሱስንዮስ መንግሥት በወረሰው ልጅ በንጉሥ ፋሲለደስ የተባረሩበት ዘመን ነው ። እነዚህ ጀስዊቶች ኾኑ የእንግሊዝ ሰፋሪዎች አሜሪካ ገብተው የሰፈሩት ከላይ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በዚሁ ዘመን ውስጥ ነበር።

## (፪) መንፈሳዊ ተጓዦች (ፒዩሪታንስ ወይም ሰፓሬቲስት)

የኹለተኛው ቡድን ጉዞ ደግሞ እንደዚህ ነው። ከላይ እንደተገለጸው ንጉሥ ሄንሪ ከሮም ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቢመሠረትም ፤ መንግሥቱን ከወረሱት ልጆች ውስጥ የካቶሊክ

[31] JAMES, = TO THE MOST HIGH AND MIGHTY PRINCE BY THE GRACE OF GOD KING OF GREAT BRITIAIN, FRANCE, AND IRELAND, DEFENDER OF THE FAITH. Etc..(KING JAMES OR AUTHORIZED VERSION)

[32] *The Modern Age vol. 2 p. 163*

[32] **Gary De Mar** *America's Christian Heritage p., 58*

እምነት ተከታይዋ ንግሥት ሜሪ በአባቷ የተመሠረተው አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ወደ ካቶሊክ ይመለስ በማለቷ መከፋፈል ቀጥሎ ተበጣብጠው ነበር። ቀዳማዊት ንግሥት ኤልሳቤጥ ንግሣ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የፕሮቴስታንት አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን እምነትን የአገሪቷ ዋና የመንግሥቱ ሃይማኖት ነው ብላ እንደ አባቷ በማወጇ አገራዊ ስሜት ስለያዘች ብዙኃኑ የእንግሊዝ ሕዝብ ወደዳት፤ የዐመፅ ትግሉ እና ችግሩ ግን አልቆመም ። ከሷ በኋላ መንግሥቱን በወረሰው በንጉሡ በጀምስ ዘመነ መንግሥት የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ሥርዓት ፈጽሞ አልነጻም የሚሉት ተቃዋሚዎች ስለነበሩ ክፍፍሉ እና ብጥብጡ ሳይበርድ ኖረ።

የጆን ካልቪን የፕሮቴስታንት ሐሳብ የተቀበሉ ተከታዮች ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ በንጉሡ ጀምስ ትእዛዝ ቢተረጐምም ደስተኞች አልነበሩም ። በዚህ የተለያየ አቋም የተነሳ በእንግሊዝ አገር መኖር ያልፈለጉ ብዙዎች ነበሩ ። አገራችን "በኃጢአት የረከሰች ኾነች" ብለው ባለመስማማታቸው ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን እና መንግሥት መለየት ፈልጉ። የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ማጥራት እና በደንብ መታደስ አለባት በማለታቸውም ፒዩሪታንስ ተባሉ ። ራሳቸውንም የተለየ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች መኾናቸውን ለማሳወቅ ሲሉ እንግሊዝ ሰፖሬቲስት[33] ብለውም ይጠሩ ነበር። በኋላም እነዚህ ሰዎች ካለባቸው ውዝግብ እና ጭቅጭቅ ነጻነት ለማግኘት ሲሉ አገራቸውን ጥለው በስደት ወደ ሆላንድ ተጉዘው በመግባት በላይደን ከተማ መኖር ጀመሩ ። (በቅጽል ስማቸው የተባበሩት ክርስቲያኖች ተብለው ይጠራሉ።)

እነዚህ ስደተኞች በሆላንድ ጥቂት ዓመታት ከኖሩ በኋላ ልጆቻቸው የሆላንድን ባህልና ቋንቋ በመከተላቸው እንግሊዛዊ ባህላችንና ቋንቋችን ሊለቁብን ነው የሚል ፍርሀት አደረባቸው ። እንዲሁም በጊዜው በሆላንድ ዐዲስ የተመሠረተው “ሪፎርምድ ቸርች” አላስደሰታቸውም ነበር።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የጀርመናዊው ማርቲን ሉተርና የካልቪን እንዲሁም ሌሎች ዐዲስ ሐሳቦች በጊዜው አውሮፓን አጥ

[33] English Separatist– the Separatists believed that every local church, every church congregation should be independent, free from any and all religious hierarchy and entirely self-governing.



ለቅልቀውት ነበር።[34] ከምዕራብ አውሮፓ እስፖኝ ፣ ፖርቹጋል እና በከፊል ፈረንሳይ የካቶሊክ ሃይማኖትን አጥብቀው ይዘው ነበር።

ስለዚህ እነዚህ ስደተኞች ይህ ኹሉ የክፍፍል ብዛት ስላላስደሰታቸው እንደገና ከሆላንድ ወደ አዲስቷ ዓለም (አሜሪካ) ለመሰደድ ወሰኑ ። ቀደም ብለው ከተጓዙት በቨርጂንያ ጀምስ ታውን ከሰፈሩት የአራሽ ገበሬዎች ጋር እንዲቀላቀሉ እና እንዲሠፍሩ ከለንደን የቨርጂንያ ኩባንያ (ካምፓኒ) ፈቃድ ተሰጣቸው። በ1620 በቄሱ (ሪቨረንድ) ሮቢንሶን አሰባሳቢነት ጸሎት ተደርጎ ከሆላንድ ወደብ በመነሳት ጉዞው ተጀመረ ፤ እነዚህ ሰዎች በቁጥር 101 ይደርሱ ነበር ። ከሆላንድ ተነስተው ወደ አሜሪካ በሰሜን ምሥራቅ ከኹለት ወር በላይ ተጉዘው ፕሌይመውዝ ሮክ ማሣቹሴትስ ደረሱ። በሃይማኖታቸው ጠንካራ አቋም ያላቸው ስለነበሩ መንፈሳዊ ተጓዥ አባቶች (Pilgrim Fathers) በመባል ይታወቃሉ ። ከለንደኑ ኩባንያ (ካምፓኒ) በተፈቀደላቸው መሠረት ከአራሽ ገበሬዎቹ ዘንድ ሊሰፍሩ የፈለጉት እና የታዘዙት በሰሜን ጀምስ ታውን በቨርጂንያ ነበር ። ነገር ግን ሜይፍሎወር የተባለችው መርከባቸው ጀምስ ታውን ሳትደርስ በማዕበል ተገፍታ በመወሰድ በሰሜኑ ምሥራቅ ማሣቹሴት ላይ ዐረፈች፤[35] እነዚህ ሰዎች ከመርከቧ ወርደው ጉዟቸውን አራገፉ ፤ ኑሯቸውን በዚያ አደረጉ።

በ1621 ላይ መሪያቸው ካርቨር ሲሞት ዊልያም ብራድፎርድ በቦታው ተተካ ። ኹለተኛው ከፍተኛ የእነዚሁ የፒዩሪታንስ ደጋፊዎችን ደግሞ በ1630 ከዐሥር ዓመት በኋላ በብዛት ከእንግሊዝ ተነስቶ ተጨመረ።[36] እነዚህ ኹሉ ከቨርጂንያው አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የተለዩ ነበሩ ። በአሜሪካ እነዚህ አትላንቲክን አቋርጠው የተጓዙ ስደተኞች በዚያ እንደ ደረሱ ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ነጻ ቤተ ክርስቲያናቸውን ማስፋፋታቸውን ቀጠሉ ። ሃይማኖተኞች ብቻ አልነበሩም፤ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች በመኾን የከብት ቆዳ እንደዚሁም የንስሳት ጠጉር ከኢንድያኖቹ እየገዙ መልሰው እያተረፉ ለአውሮፓውያን ነጋዴዎች የሚነግዱ ነበሩ።

ዊልያም ብራድፎርድ የቅኝ ገዢ አስተዳደር መሥራች ኾነ ፤ እነዚህ መጤዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥት አስተዳደር መመሪያዎች አውጥተው በራሳቸው መንግሥት መተዳደር ጀመሩ ፤ በአሜሪካ

[34] Gary De Mar *p., 17*
[35] *The Modern Age vol. 2 p. 227*
[36] Gary De Mar *p., 18*

እንደፈለጉት መኾን ቻሉ ። የቤተ ክርስቲያኒቷ የበላይ ጠባቂ (Defender of the Faith) የሚለው በንሱ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም ፤ ቤተ ክርስቲያናቸው እንዳሰቡት ነጻ ኾነች። ነገር ግን በኑሯቸው ብዙ ጊዜ በሽታና ረሀብ ያጠቃቸው ነበር። አሜሪካ በገቡ በመጀመሪያው ዓመት የሚኖሩበት ቦታ ረግረግ ስለኾነ በግማሽ የሚደርሱት በወባ በሽታና በረሀብ አልቀዋል ። በወዳጅነት የሚያዩዋቸው ፣ የሚረዷቸው የአሰካንቶ ኢንዲያን ጎሳዎች ጥራጥሬ እንዴት እንደሚዘራ ፥ እንደሚመረት አስተማሩዋቸው ። በጸደይ ወራት (Autumn) ዐዲሲቷ ዓለም አሜሪካ በደረሱ በዓመቱ ታኅሣሥ 4 ቀን 1621 ሐሙስ ዕለት፣[37] እርሻ አርሰው ያመረቱትን የመጀመሪያ የምርት ውጤት በአንድ ላይ ተሰባስበው እግዚአብሔር እናመሰግን ብለው ታላቅ የራት ግብዣ አደረጉ ። ይኽንን ቀን "ዕለተ አኮቴት" (Thanksgiving) አሉት ። ዛሬ አሜሪካውያን ባህላቸው አድርገው በታላቅ ድምቀት ከሚያከብሯቸው ዓመታዊ በዓላት ውስጥ አንዱ ይህ በዓል ነው።[38] በዚህ ቀን ከቤተሰቡ የተለየ ልጅ ይኹን ዘመድ አዝማድ ብዙ ኪሎ ሜትር አቋርጦ ካለበት ቦታ ተጓጉዞ በመኼድ ከቤተሰቡ፣ ከዘመዱ የሚገናኝበት እና አብሮ በመመገብ በዐሉን የሚያከብርበት የምስጋና ቀን ነው።

ለምሳሌ ያህል በ2003 ፕሬዘዳንት ጆርጅ ቡሽ ኢራቅ ውስጥ በጦርነቱ ግንባር ላይ ያሉትን ወታደሮች ለማስደሰት ሲል በዚህ የምስጋና ቀን ላይ ድንገት በመገኘት ከጦሩ ጋራ የተርኪ ዶሮ አብሮ በመብላት በዓሉን በማክበሩ የዕለቱ ታላቅ ዜና ኾኖ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ የአገር ተወላጅ የአሜሪካ ዜጎች (ኢንዲያን) ያረስነው እና ያመረትነው እኛ ስለኾን በዓሉ የመጤዎቹ ሊኾን አይገባም የሚል እምነት አላቸው። እነዚህ ለአገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ የኾኑ የመጀመሪያዎቹ የብሪታንያ የእንግሊዝ ሰፋሪዎች ቀስ እያሉ የእርሻ ቦታ እና የጸሎት ቤት መሥራት እንዲሁም ቅኝ ግዛታቸውን ማስፋፋት ቀጠሉ፤ ኒው ሄሽን፥ ኒው ኢንግላንድ፣ ኒው ዮርክ በማለት የመጡበትን በብሪታንያ በእንግሊዝ ግዛት ያሉትን ስፍራዎች በማስታወስ ዐዲሲቷ የሚል ቅጽል ስም እየሰጡ ቦታዎችን መጥራት ጀመሩ።

[37] ዕለተ አኮቴት የሚከበርበት ቀን የተወሰነው በኋላ ዘምን ጆርጅ ዋሽንግተን ኅዳር 26 ቀን 1789 እንዲከበር አድርጎ ነበር። ነገር ግን አብርሃም ሊንከን በ1863 ሐሙስ ቀን በኅዳር ወር ቀኑም የወሩ መጨረሻ እንዲኾን አደረገ። በጠቅላላው ቀናቱ ሦስት ጊዜ ተለዋውጧል።
[38] **Gary De Mar** *p., 77* (Christianity Idiots Guide p. 36)



በጊዜው የነበሩት አብዛኞዎቹ ሰፋሪዎች እንግሊዞች ነበሩ ፤ በ1629 ወደ 20 ሺ የሚደርሱ ፒሩታንስ ተጨመሩ።

ከነዚህ ሌላ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አኩርፎ የተገነጠለ ሌላ ቡድን የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን በ1639 በአሜሪካ ደረሰ። የባፕቲስት እምነት ከፒዩሪታንስ (ኮንግርጌሽናሊስት) ጋራ መሠረታዊ የኾኑ ነገሮች ስለሚያገናኟቸው አብረው ተባብረው መሥራት ጀመሩ ። የካልቪንም ኾነ የባፕቲስት የኹለቱም ወገኖች አመለካከት የመንግሥት አስተዳደር በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ መፈለጋቸው አንድ ያደርጋቸዋል።

## (፫) የአሜሪካ ተወላጆች "ኢንዲያን"

ከእስፓኝ የካቶሊክ መንግሥት የተላከው ኮለምቦስ በዐዲሲቷ ዓለም በደረሰበት ጊዜ በተለያዩ ቦታ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይኖሩ ነበር ። እሱም ህንድን ያገኘ መስሎት ኢንዲያኖች ቢላቸውም እነሱ ግን የየራሳቸው የተለያየ ጎሳ እና የተለያየ ቋንቋዎች፣ ባህል እና ሃይማኖት ያላቸው ነገዶች ነበሩ ። የግድ ኾኖባቸው ነው እንጂ እንደ አንድ ሕዝብ ኢንዲያኖች ተብለው መጠራታቸውን አይቀበሉትም።

በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እነዚሁ አውሮፓውያን አገሪቷን በቅኝ ግዛት መያዝ ሲጀምሩ፥ 10 ሚሊዮን[39] የሚደርሱ የአሜሪካ ተወላጆች ኢንድያኖች ነበሩ፤ አኗኗራቸውም በአደን እና በእርሻ ላይ የተመሠረተ ነበር። እነዚህ ሰዎች ከአውሮፓውያን በተለይ ከእስፓኞች ፈረስ ባገኙ ጊዜ ጎሽ የሚባለውን በሬ የሚመስል ዝርያ እያደኑ ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለጫማ፣ ለቢላዋ መሥሪያ ይጠቀሙበት ነበር[40]። ለፈረንሣዮችም ቆዳ እና የሌሎችንም የእንስሳት ጠጉር ይሸጡ ነበር።

ኽንደተገለጸው ከቀድሞ ጀምሮ የሰደተኛ ቁጥር ከአውሮፓ ወደ አሜሪካ ይጓዝ ነበር። ፈረንሣዮች በብዛት ተጉዘው የሰፈሩበት ቦታበሰሜኑ ኩቤክ (የካናዳ ግዛት) በምትባለው ቦታ እና በሎራንስ ወንዝ አካባቢ ነው። እንግሊዞች ደግሞ በኒውኢንግላንድ እና በቨርጂንያ ሲኾን ዳቾች በኒው ዮርክ ማንሀተን ሰፈረው ይኖሩ ነበር። በዚህ ጊዜ

[39] **David Mauk and John Oakland** *"American Civilization" 2001., p.28*
[40] **Alison Baxter** *The USA Oxford 2001., p., 8*

ከፍተኛ የኾነ የንግድ ውድድር ተጀመረ ። የከብት ጸጉር፥ ጥጥ እና የከብት ቆዳ ሌሎችንም ነገሮች ወደ አውሮፓ ለመላክ የሚደረገው ውድድር ከፍተኛ ነበር። ይህን የንግድ ጥቅም በማየት ሰደተኛ በብዛት ከአውሮፓ ይፈልስ ጀመር ። እነዚህ ዐዲስ መጤዎች ለጥቅም ሲሉ በጦርነት እና በበሽታ ነዋሪዎቹን እንዲያኖች ይጨርሷቸው ጀመር። ዋና ምክንያታቸው ለሥልጣኔ እንቅፋት እና ኋላ ቀሮች ፤ የእርሻ ምርት ዕድገት እንዲታይ የማይፈልጉ መስለው ስለሚታዩዋቸው ነበር።

በሰሜን ምዕራብ የሚገኙት ጎሳዎች ሳሊሽ ፣ ኩዋኪኡቲል ፣ ኖትካ ፣ ፖሞ፣ ሾሾኒ፣ ሆፒ፣ ናቫሆ ፣ ፑኤብሎ፣ አፓቼ፥ ይባላሉ ። በመኻል ሜዳማውን አገር ይዘው የነበሩት ደግሞ አሲኒቦየን ፣ ብላክ ፊት ፣ መእነዳን፣ ሲዮክስ፣ ቼይኔንኮማንቺ ሲኾኑ። በሰሜን ምሥራቅ ይኖሩ የነበሩት ጎሳዎች አጂባዋ፣ ኢሮኪዮይስ ፣ ዋመፓኖአግ ሲባሉ፤ ደቡብ ምሥራቁ ሴሚኖሌ በመባል ይታወቃሉ ። እነዚህ ኹሉ እኗኗ ራቸው የተለያየ የኾነ የራሳቸው ባህልና አምልኮት ያላቸው (በጣዖት የሚያመልኩ) ነበሩ።

አብዛኛው የአሜሪካ የቦታ እና የአገር ግዛት ስሞች፣ ከተሞች እና ወንዞች መጠሪያ ስማቸው የመጣው ከነዚሁ ብዙ ቋንቋ ከሚናገሩ ኢንዲያኖች ጎሳ የተገኘ ነው።[41] እነዚህ የተለያዩ ጎሳዎች ይጠቀሙበት

[41] አላስካ ማለት ፤ "ታላቅ አገር" ሲኾን በየህም ጎሳ ቋንቋ የወጣለት ነው ከነክቲኬት "የውሃ ማዕበል የሚያማታው ወንዝ"። ኢንዲያና የተባለችው ግዛትም በአገሬው ተወላጅ ኢንዲያን ማለት ነው። ኢዳሆ "በተራራ ላይ የ ያበራ" ኢልኖይስ "ጦረኞች"፤ ከንሳስ በሱይክስ ጎሳዎች ትርጕም "የደቡብ ንፋስ ሕዝቦች"፤ ማሣቹሴት "ታላቅ ተራራ ትንሽ ቦታ"፤ ሚችጋን ማለት "ታላቅ ሐይቅ"፤ ሚኒሶታ "ዳመናማ ውሃ"፤ ሚሲሲፒ "ታላቅ ውሃ"፤ ሚዙሪ "ጭቃማ ውሃ" አሀዮ "የሚያምር ወንዝ" አክሎሆማ "ቀይ ሕዝቦች" ቴክሳስ ጓደኞች"፤ ዩታ "የተራራ ሰዎች"፤ ዊስኮንሲን "የሳር ቦታ"፣ ሌሎችም... በ ባል በነዚህ ጎሳዎች ቋንቋ የተሰየሙ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ በእንግሊዝ ፣ ረንሳይ እና በእስፓኝ ቋንቋዎች የተሰየሙ ሲኾኑ አንዳንዶቹ ከክርስትና ሃ ማኖት ጋር የተያያዙ ናቸው። ሜሪ ላንድ (የማርያም አገር)፣ ሎዛ እንጀለስ ፊላዳልፊያ ሌሎችም ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በሰው ሰሞች ተሰይመዋል ለምሳሌ በኮሎምቦስ ልጅ ዲያጎ በካሊፎርንያ ደቡብ ክፍል ያለው ቦታ ሳን ያጎ ተብሎ ተሰይሟል። ዋሽንግተን፣ ጀምስ ታውን፣ ቨርጂንያ፣ ኮለምበስ ት ጉም አላቸው።



የነበረው ቋንቋ ዛሬ አንዳንዶቹ ከገጸ ምድር በመጥፋት ላይ ናቸው።[42] እንዲያኖች ሲገናኙ የመግባቢያ ቋንቋ ፤ የምልክት መነጋገሪያ ነበራ ቸው። ዛሬ በዘመናችን መናገር የተሳናቸው (ዲዳ) ሰዎች የሚግባቡበት የምልክት ቋንቋ አይነት ማለት ነው ። በርቀት ላይ ኾነው መልእክት ሲለዋወጡም በእሳት ጭስ ቅታሬ ምን እንደሚፈልጉ እና ምን እንደ ደረሰባቸው ይነጋገራሉ፣ ይተዋወቃሉ።

የምዕራብ አሜሪካ ክፍል ዐዲሱ ሕይወት እና ዐዲስ ሰፋሪዎች በነዚሁ በተወላጆች እንዲያኖች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖና ግፍ በየጊዜው አድርሰውባቸዋል ። ባህላቸውን፣ ኑሯቸውን፥ አፈራርሰውባቸዋል ። ይዞታቸው የነበረውንና የሚኖሩበትን መሬታቸውን አስለቅቀዋቸዋል ። ቁጥራቸውን ለመቀነስ የእርሻ ቦታቸውን እና መሬታቸውን ለመውሰድ ሲሉ በፈንጣጣ እና በሳንባ የተበከለ የመርዝ ብርድ ልብስ፤ የአልኮል መጠጥ በማጠጣት ጨርሰዋቸዋል።[43] እነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ከመ ጤው የቅኝ ገዢ መንግሥት ወታደሮች ጋራ ውጊያ ይገጥሙ ነበር ። ነጮቹ የሚጠሯቸው "ሬድ ኢንዲያን" በማለት ነው ። ይህም በጣም ያልጠቆሩ የነጭነት መልክ የሌላቸው ስለኾኑ ነው ። ኢንዲያኖቹ ደግሞ ነጮቹን "ዋሹቺ" ብለው ይጠሯቸዋል። አሜሪካኖቹ በአሜሪጎ ስም አሜሪጎውያን ነን ብለው ራሳቸውን ይጠራሉ። ጦራቸውም የሚታ ወቀው በአሜሪጎውያን ነው።

በዚህ በመንግሥት እና በተወላጆቹ ኢንዲያን መካከል በ1890 በተካኼደው ዎኑድድ ክኒ በሚባለው ጦርነት ላይ በጣም ብዙ ሲዮኡ ክስ ወንዶችና ሴቶች እንዲኹም ሕፃናት በአሜሪካ ወታደሮች በደቡብ ዳኮታ ቆስለዋል፣ ተጨፍጭፈዋል ፤ እንዲያኖቹ ለውጊያ ሲሰለፉ ለመ ሞት ቆርጠው በጀግንነት በመነሳት "ጥሩ የመሞቻ ቀን"(Good day to die) የሚል መፈክር ነበራቸው ። በጣም የሚፈራና የሚከበር ሲቲንግ ቡል (1831 - 1890) የሚባል ሰው ሕይወቱን በሙሉ ከነጮች ጋራ ሲዋጋ የኖረ ተወዳጅ የጦር መሪ ነበራቸው። በኋላ ግን በሊትል ቢግ ሆርን ውጊያ ላይ ተሸንፎ ተማረከ።[44] በ1930 እነዚህ ነዋሪዎች ቁጥራቸው ወደ 300,000 ዝቅ ብሎ ነበር፤ የቀነሰበት አንዱ ምክንያት በዚሁ በጦርነቱ ነው።

[42] Robert S. *Cobble Stone the History magazine for young people 31*

[41] *Population History of American Indigenous Peoples*, (www. Wikipedia. Org/wiki/)

[44] Harry Smith *Ultimate Biography 2002, p., 53*

ዛሬ ከ2 ሚሊዮን እስከ 3 ሚሊዮን የሚደርሱ ኢንዲያኖች
በመካከለኛው የአሜሪካ ግዛት በተከለለ ሥፍራ ይገኛሉ።[45] አብዛኛዎቹ
ሥራ የላቸውም ። በድህነት እና በዘር መድልዎ ተጠቅተው የሚኖሩ
ናቸው ። በዚህ የተነሳ ብዙዎቹ ኢንዲያን የአሜሪካ ተወላጆች በክር
ስትና ላይ የከፋ ጥላቻ አላቸው ። ምክንያቱም አውሮፓውያን የክርስ
ትና ስብከትን ምክንያት አድርገው ስላጠቋቸው መስቀልን እና ሰይፍን
አንድ አድርገው እንደሚያዩት አንዳንዶቹ ይናገራሉ። አብዛኛዎቹ ስለክ
ርስትና በራሳቸው ሰዎች እንዲሰበኩ እንጂ በሌሎች ወይም በአውሮፓ
ውያን ነጮች መሰበክ እንደማይሹ ይናገራሉ ። አንዳንዶቹም ደግሞ
እኛ እውነተኞቹ የጥንት አይሁዳውያን ነን ብለው ያምናሉ። ይህ ከአ
ንዳንድ ኢንዲያኖች ጋር ባጋጣሚ በተደረገ የሐሳብ ልውውጥ የተገኘ
መረጃ ነው።

## (፬) ስብከተ ወንጌል ለኢንድያኖች

ከመጀመሪያው ጊዜ ጀምሮ እነዚኽን ኢንድያኖች የራሳቸውን እምነት
ትተው የክርስትናን ሃይማኖትን እንዲቀበሉ ለማድረግ አውሮፓውያን
ሰባኪዎች የተለያየ መንገድ ተጠቅመዋል።

የሉተር የፕሮቴስታንት ዐዲስ ሐሳብ በመፈጠሩ ይኽን ለመቋ
ቋም የተደራጁት የፈረንሳይ የካቶሊክ መነኰሳት ጀስዊት[46] የሚባሉት
እንዲያኖቹ በፕሮቴስታንት እምነት እንዳይወሰዱ በመፍራት ምልመላ
ጀመሩ። የመመልመያ ዘዴያቸውም ተጠምቃችሁ ክርስቲያን ከኾናችሁ
እና ቀሳውስት ከኾናችኹ ሥራ ይሰጣችኋል ፤ ሕክምና በነጻ ታገኛላ
ችኹ ይሏቸው ነበር። በቋንቋቸው እያስተረጐሙ በመስበክ በብዙ ሺህ
የሚቆጠሩትን በሴይንት አገስቲን በ1630 ላይ ወደ ካቶሊክ የክርስትና
እምነት ለውጠዋቸዋል፤ አንዳንዶቹም ነጋዴዎች የእንስሳት ጠጕር እን
ዲያመጡላቸው እያደረጉ ብርድ ልብስ፣ ጠመንጃ፣ ምግብ፣ አልኮል
መጠጥ ይሰጧቸው ነበር።

የካቶሊክ ሃይማኖት ከዐሥራ ሦስቱ የአሜሪካ የቅኝ ተገዢ ግዛ
ቶች ውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ለስብከት ፍራንሲስካን የሚባሉትና ጀስ
ዊት የሚባሉት የካቶሊክ መነኰሳት የወንጌል ሰባኪዎች ካሊፎርንያ፣
ፍሎሪዳ፣ ኒው ሜክሲኮ፣ ሳንት አንቶንዮ እና ቴክሳስ ተብለው የሚጠ

[45] **Indian Reservation**

[46] **Jesuit** order, (the Society of Jesus Christ.)



ሩትን ቦታዎች መሠረቱ ። እንዲኹ የአልሞ ሕንጻም በ1716 መሠ
ረቱ።[47] ሳን-ታፌ፣ ሳን-ዲያጎ፣ ሎሳ-አንጀለስ እና ሳን-ፍራንሲስኮ እነዚህ
ኹሉ በአሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የካቶሊክ እምነት የተጀመረባቸው
ቦታዎች ናቸው ። ከእስፓኝ የሮማ ካቶሊክ መነኰሳት የኾኑት ጀስዊ
ቶች በዚህ ቦታዎች ተሰማርተው ከላይ እንደተገለጸው እንዲያኖች
የነበሩበትን የጣዖት አምልኮ (አምልኮ ባዕድ) ትተው ወደ ካቶሊክ
እምነት ለመለወጥ የሰበኩባቸው ቦታዎች ናቸው።

የፕሮቴስታንት እምነትም "አሜሪካን ባይብል ሶሳይቲ" የአሜሪካ
የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በማለት ማደራጃ በመመሥረት ከጥንት የጣ
ዖት አምልኮታቸው ወደ ፕሮቴስታንት እምነት እንዲለወጡ ጥረት
ያደርግ ነበር። ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ብዙዎቹ በአኹኑ ጊዜ
ክርስትና የነጭ እምነትነው በሚል በከፍተኛ ጥላቻ የሚናገሩና ደስተኛ
አለመኾናቸውን የሚያንጸባርቁ ናቸው።[48]

## (፭) ቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት

ከ1688 እስከ 1763 ፈረንሳይ እስፓኝ እና ታላቋ ብሪታንያ አውሮፓን
እና አሜሪካንን ለመቆጣጠር ለብዙ ዓመታት ብዙ ጦርነት አደረጉ ።
በ1763 ታላቋ ብሪታንያ ለሰባት ዓመት ከፈረንሳይ ጋራ በጦርነቱ ተዋ
ግታ የሰሜን አሜሪካ ምሥራቁን ክፍል ያዘች።

ብሪታንያ በጣም በክርክር በፖለቲካ የማትቻል አገር ነበረች፤
የመጨረሻዋ የቅኝ ገዢ ከኾኑት አገሮቹ ኃያል የኾነች መንግሥት
በመኾኗ የቅኝ ግዛት መንግሥቷን በምሥራቁ ጠረፍ ያሉትን ቦታዎች
በ13 ከፋፍላ አቋቋመች ። ጊዜውም 1700–1740 ሲኾን 2500 ሺ
የሚደርሱ ዐዲስ ዜጎቿ በአሜሪካ እንደገና ተጨመሩ፤ ይበልጡን የሰ
ፈሩቷ በሰሜኑ ክፍል ነው። ትውልዱ በጣም እየበረከተ ኼደ። በ1750
ከኹለት ወደ ሦስተኛው ትውልድ በመጨመር የሕዝቡ ቁጥር በእጥፍ
ከፍ በማለት ወደ አንድ ሚሊዮን ደረሰ።[49] ብዙ ሰዎች ከብሪታንያ
ሀብትና ነጻነት ለማግኘት ምኞት ስላደረባቸው ወደዚህ ቦታ ተጓዙ ።

[47] **Alison Baxter** *The USA Oxford 2001 p., 9*

[48] **Jeffrey B. Webb,** *the complete Idiot's Guide to Christianity (New York 2004) p., 47 - 60*

[49] **David Mauk and John Oakland** *American Civilization an introduction New York 1997., p 30*

ለጉዞ የሚኾን ገንዘብ መክፈል የማይችሉት እዚያ ስንደርስ በጉልበታችን እያገለገልን እንከፍላለን በማለት ቃል ይገቡ ነበር።[50] ቃልም የሚያስገቧቸው ባለሀብቶች ከኹለት እስከ ሰባት ዓመት በጉልበታቸው እንዲያገለግሉ ነው።

ወንጀል ፈጽሞ የተፈረደበትም እንግሊዝ እስር ቤት ገብቶ ብዙ ወጭ ከሚያስወጣ ይልቅ እንዲያገለግል ይላክ ነበር ፤ በኋላ ግን አፍሪካውያንንም ጨመሩ ። በዚህ ዓይነት ዘዴ ለአገልግሎት ሲያሠማሯቸው ኖሩ ። እያደርም ይህ ልማድ ወደ ባርነት ሥርዓት ተተካ ። ከብሪታንያ በመርከብ ወደ አሜሪካ ለመጓዝ ጉዞው የሚፈጀው ዐርባ ቀናት ያኽል ሲኾን ከስደተኞቹ ውስጥ በጉዞ ላይ እያሉ ቢያንስ ከዐሥሩ አንዱ ይሞታል።[51] በብዛት ተጉዘው ይሰፍሩበት ቦታ በሰሜን ምሥራቅ ክፍል ነው። በዚህም እንግሊዝን ላለመርሳት የቦታውን ክልል በሙሉ በእንግሊዝ አገር ባሉት ከተሞች እና ወረዳዎች ሲይመዋል ። ይህ ማንኛውም ስደተኛ አገሩን ስለሚናፍቅ ለመታሰቢያ የሚያደርገው ነው።

በደቡብ ምሥራቅ ያለው የቨርጂንያው ሰፋሪ የአንግሊካኑ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሰሜኑ በፒዩሪታንስ ሳይደሰት በቅሬታ ይኖር ነበር። ምክንያቱም ፒሩታንስ ንጉሥ አልቀበል በማለቱ አንግሊካኑ ንጉሥ አስፈላጊነቱን በመጽሐፈ ሳሙኤል ምዕራፍ 8 ያለውን በማንሳት ዘወትር ሲገናኙ ይከራከሩ ነበር።(1ኛ ሳሙ. 8፥22)

ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በ1634 በሜሪላንድ የካቶሊክ ተከታዮች የኾኑ የብሪታንያ ተወላጆች ሰፈሩ። እነዚህ የብሪታንያ ካቶሊክ እምነት ተከታይ ቡድኖች በአገራቸው እንደ ኹለተኛ ዜጋ ይቆጠሩ ነበር ። የካቶሊክ እምነት በብሪታንያ (በእንግሊዝ) አገር አንዱ የተሰቃየ ቡድን ነው። በዚህ የተነሳ ካቶሊኩ ሎርድ ቦልቲሞር ቀደም ብሎ የንጉሥ ቻርለስ ቀዳማዊ ፈቃድ ጠይቶ ወደ አሜሪካ ተጉዞ የቅኝ ግዛት መሠረተ ። ካቶሊክ ሃይማኖት ተከታይ የኾኑ ኹሉ በሃይማኖታቸው ምክንያት የሚሰባሰቡበት የሚሰፍሩበት ቦታ ሜሪ ላንድ (አገረ ማርያም) በመባል ተሰየመ። ካቶሊክን ይዞ በተሰደደው በሎርድ ቦልቲሞር ስም የሜሪላንድ ኹለተኛ ከተማ ቦልቲሞር ተብሎ ተሰየመ።

[50] INDENTURED SERVANTS
[51] **Steck Vaughn** *PRE-GED Social Studies 2000 USA.,*



የታወቀው የዴዜደራታ[52] አስደናቂው የሕይወት ምክር ሰጪ ጽሑፍ ተብሎ የሚታወቀው በዚሁ በቦልቲሞር ከተማ ቅዱስ ጳውሎስ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በ1692 ተገኘ ፤ በጽሑፉ ውስጥ እንዲህ የሚል ምክር ይገኛል።

> ...ከዕፀዋት እና ከከዋክብት የማታንስ የዚህ ታላቅ ፍጥረተ ዓለም ዝርያ ስለኾንክ በዚች ዓለም ላይ የመኖር መብት አለህ። ኹኔታው ላንተ ግልጽ ኾኖ ባይታይም ይህ ታላቅ ፍጥረተ ዓለም ያለ ጥርጥር ምስጢሩ እያደር እየተገለጠ በመኼድ ላይ ይገኛል፤ ስለዚህ ሐሊናህ አውጥቶ አውርዶ ከተቀበለው አምላክ ጋር ግንኙነትህ የሠመረ ይኹን። ...

ይህ አስደናቂ ጽሑፍ በብዙ ቋንቋዎች ተተርጕሟል ። በዐማርኛም ተተርጕሞ ብዙ ሰዎች መጽናኛ እና የሕይወት ምክር እናገኝበታለን ብለው በየቤታቸው ግድግዳ ላይ ለጥፈው ያነቡታል።

በፔኒሲልቫንያ ቅኝ ገዢ በመኾን የያዙት እንደዚሁ ከእንግሊዝ የተሰደዱ ኴከር የሚባሉት የሃይማኖት ቡድኖች ነበሩ ። ይህ የሃይማኖት ቡድን በእንግሊዝ አገር የተመሠረተ ነው ። የእንግሊዝ ባሕር ኃይል ወታደር ሰው ልጁ ዊልያም ፔን መጋቢት14 ቀን 1681 በብሪታንያው ንጉሥ ቻርለስ 2ኛ ተሹሞ ተላከ ። ዊልያም ፔን ፔንሲልቫንያን እና ፊላዳልፊያን መሠረተ ። ፊላዳልፊያ ማለት ከኹለት የግሪክ ቃል የተወሰደ ነው ፤ የወንድማማች ፍቅር ማለት ነው ። እነዚህም ኴከር የተባሉ ቡድኖች ወንድማማች በመባባል ይጠራራሉ።

እነዚህ በአሜሪካ በየቦታው ያሉ የቅኝ ገዢዎች የራሳቸው የኾነ የግዛታቸው ማኅተም ነበራቸው። በሕገ መንግሥታቸው ውስጥ በእግዚአብሔር ስም እናምናለን የሚል መግለጫ አስገብተው ነበር ። የሚመሯቸው የቅኝ ገዢው ተወካይ አለቃ ነበራቸው።[53] በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር የነበሩ ግዛቶችም የሚከተሉት ናቸው ።

### የቅኝ ገዢው መንግሥት መሪ ተወካዮች

1. ማሣቹሴትስ ተወካይ ጆን ዊንቶርፕ 1620
2. ቨርጂንያ ተወካይ ጆን ስሚዝ (የቨርጂንያ ኩባንያ) 1628[54]

[52] ዴዜደራታ ቃሉ የላቲን ሲኾን፤ በሕይወት ውስጥ ደስታ ማግኘት ማለት ነው ። ማን እንደጻፈው ግን አይታወቅም።
[53] **Gary De Mar.,** *p. 23*
[54] **Stephanie Abraham H.** *States and Regions., p., 147*

3. ሜሪላንድ ተወካይ ሎርድ ቦልቲሞር 1632
4. ሮዴ አይላንድ ተወካይ ሮጀር ዊልያም 1635
5. ደላዌር ተወካይ ፒተር ሚኑዩት 1638
6. ከነክቲኬት፣ ተወካይ ቶማስ ሁከር 1639
7. ኖርዝ ካሮላይና ተወካይ አንቶኒ አሽሊ 1663
8. ሳውዝ ካሮላይና ተወካይ አንቶኒ አሽሊ 1663
9. ኒው ሀምፕሸር ተወካይ ጆን ዊልራይት 1679
10. ፔንሲልቫንያ ተወካይ ዊልያም ፔን 1681
11. ኒው ዮርክ ተወካይ የዮርክ መስፍን 1685
12. ኒው ጀርሲ ተወካይ ሎርድ ቤርኬሊ 1702
13. ጆርጂያ ተወካይ ጀምስ ኦልግሌቶፎር 1732

እነዚህ ተወካይ የቅኝ ገዢ ክፍሎች ከብሪታንያ ከእንግሊዝ የትምህርት መመሪያ (Curriculm) በማምጣት ብዙ ቦታዎች ላይ ትምህርት ቤት ከፈቱ። ልጆቻቸውንም በመጀመሪያ የሚያስጠኑት በብራና ላይ የተጻፈ የፊደል መማሪያ ኤ ቢ ሲዲ እና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን የጸሎት ሥርዓት አባታችን ሆይ የሚለውን መገቢያ በማድረግ ነበር። ከዚያም መዝሙረ ዳዊትን ፣ ቀስ እያሉ ለስብከተ ወንጌል ወንዶች ልጆችን ለማስተማር ማሠልጠኛ ኮሌጅ ከፈቱ።

ከዚህ አርስት ሳልወጣ የኢትዮጵያም የጥንት የትምህርት መመሪያ እንዲሁ በጥቂቱ ከዚህ ከአሜሪካውያን የትምህርት አሰጣጥ ጋር የሚመሳሰል ነበር ። በብራና ላይ የተጻፈ ፊደለ ሐዋርያ ፤ ወንጌል ፣ ዳዊት እና የቃል ትምህርት ተምሮ ከተፈጸመ በኋላ፤ መጽሐፍት ቤት፤ ቅኔ ቤት፤ ጸዋትወ ዜማ ቤት ይካኼዳል ። ይህም የትምህርት ተቋም ኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ ማለት ነው ። ከኹሉ የሚደነቀው ደግሞ ሊቃውንቱ (ፕሮፌሰሮቹ) ኹሉንም ትምህርት በቃላቸው የሚይዙ ነበሩ ። በጥንታዊነቱ የታወቀው በ1524 በግራኝ መሐመድ ጦር ሠራዊት የፈረሰው የደጋ እስጢፋኖስ የትምህርት ማዕከል እንደ ምሳሌነት የሚወሰድ ነው።[55]

በአሜሪካ የመጀመሪያው ሐርቫርድ ኮሌጅ በ1636 ተቋቋመ ፤ በዚያ የትምህርት መመሪያው ነገረ መለኮት (ቲዮሎጂ)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ጥናት፣ በሕዝብ መካከል እንዴት ንግግር ማድረግ (እንዳለባቸው ወይም የስብከት ዘዴ (ሪዮቶሪክ) ነበር። ቀስ እየተባለ መጽሐፍ ቅዱስን በዕብራይስጥ እና በግሪክ የቋንቋ ጥናት ተጨመረ። በመጀመሪያው ዓመት ከተመረቁት ጆን ኤሊት (1604-1690) የሚባለው አንዱ ነበር። ይህ ሰው በማሣቹሴት የእንግሊዝ ፕሬስቤተርያን የክርስትና እምነት ተከታይ የኾነ ሰው ነበር ። የኢንድያኖችን ቋንቋ ተምሮ ዋና ሰባኪያቸው ኾነ ። የመጀመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስ በቋንቋቸው ተረጐመ ። ፔኩቶ የሚባሉትን የኢንዲያን ጎሳዎችን አስተምሮ ብዙዎችን አጠመቃቸው ። ይህ ሰው በዚህ ሥራው የኢንድያኖች ሐዋርያ ነው በመባል ይታወቃል።

55 ጌታቸው ኃይሌ፤ ባሕረ ሐሳብ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ገጽ 239



## በመጀመሪያ የተቋቋሙት ኮሌጆች

| ዘመን | ኮሌጅ | የቅኝ ግዛት ቦታው | እምነት |
|---|---|---|---|
| 1636 | ሐርቫርድ | ማሣቹሴትስ | ፒሩታንስ |
| 1693 | ዊልያም እና ሜሪ | ቨርጂንያ | አንግሊካን |
| 1701 | ዩል | ከነክቲኬት | ኮንግርጌሽናሊስት |
| 1746 | ፕሪንስተን | ኒው ጀርሲ | ፕርስቤቴርያን |
| 1754 | ኪንግስ ኮሌጅ | ኒው ዮርክ | አንግሊካን |
| 1764 | ብሮወን | ሮዴ አይላንድ | ባፕቲስት |
| 1766 | ሩተጌርስ | ኒው ጀርሲ | ዳች ሪፎርምድ |
| 1796 | ዳርትማውዝ | ኒው ሃምፕሸር | ኮንግርጌሽናሊስት |

በአኹኑ ጊዜ በአሜሪካ ግዛቶች በጠቅላላ ከ90 በላይ የሚደርሱ ታላላቅ ዩንቨርሲቲዎች ይገኛሉ። በየዓመቱ ብዙ ተማሪዎች ይመረቃሉ።

በነዚህ በ13ቱ ቅኝ ግዛቶች አብያተ ክርስቲያናት ተስፋፍተውባቸው ነበር። የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቨርጂንያ፣ ሜሪላንድ ፣ ካሮላይና ፥ ጆርጂያ እና ኒው ዮርክ በግማሽ ይዘው ኖሩ። ፒሩታንስ (ካልቪኒስት ወይም ኮንግርጌሽናሊስት) የተባሉት ደግሞ ኒው ኢንግላንድ ሰሜን ክፍል ያሉትን ቦታዎች ይዘው ነበር። ሌሎቹ ግን የእስኮትላንዱ ፕሬስቤትርያን፣ የጀርመኑ ሉተራንና ባፕቲስት በቅኝ ገዢዎቹ ተፅዕኖ ከብሪታንያ መንግሥት ጎን ባለመሰለፋቸው ብዙ አልተስፋፉም ነበር።

የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት፥ ከፈረንሳይ ጋራ (በ1770) የነበረው ጦርነት እንደ ተፈጸመ 13ቱን በምሥራቁ የባሕር ጠረፍ ዙሪያ ያሉት ቦታዎች የእንግሊዝ ፓርላማ በደንብ በቅኝ አገዛዝ ይዞ

ማስተዳደር ጀመረ ። በጦርነቱ ምክንያት ብዙ ወጭ ስለወጣ ገንዘቡን የመመለሻ ዘዴ ሕዝቦቹ ላይ ቀረጥ ወይም ግብር እንዲጨመር እና እንዲከፍሉ ጫና ተደረገ። የታላቋ ብሪታንያ ንጉሥ ጆርጅ 3ኛ በቅኝ ግዛት የያዛቸው ሕዝቦች ግብር እንዲገብሩ ወይም ቀረጥ (ታክስ) እንዲከፍሉ አደረገ።

ቀጥሎም የቴንብር ቀረጥ ሕግ በ1765 ወጣ፤ ማንኛውንም ነገር ሲገዛ የሚከፈለው ቀረጥ ከፍ እንዲል አደረጉ ። ንጉሡና ፓርላማው የሚኖሩት በእንግሊዝ አገር ለንደን ነው። ግብር ያልከፈለ ያለ ምንም ምሕረት በወታደር እየተያዘ ወደ እስር ቤት ይገባል ፤ አቤቱታ ለሚ ፓርላማ ወይም ንጉሥ የለም ኹሉም ያሉት በብሪታንያነው። ተወካዩ መንግሥትም ደግሞ ከእንግሊዝ ነጋዴዎች ጋራ በጥቅም የተሳሰረ ነበር ። በዚህ የተነሳ ነጋዴዎቹ እና የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግ ሥት በጣም ሀብታቸው እየጨመረ ኼደ ። በአንጻሩ ተራው ነዋሪ ሕዝብ ችግር እና ጉስቁልና ስለደረሰበት እየከፋው መጣ ። ነዋሪው ሕዝብ ብቻ ሳይኾን ነጋዴዎች እና ከበርቴዎቹ ከአፍሪካ በገፍ እየተ ጫነ የሚመጣው ባርያ በእርሻ ላይ ተሰማርቶ ብዙ ጥቅም አስገኝቶ ነበር ። የቅኝ ገዢው መንግሥት ከባርነት የሚያገኘው ጥቅም ፤ የሚ መረተው ምርት ፤ ብሪታንያን እንድትበለጽግ አድርጓታል።

ከ1500 እስከ 1800 ድረስ የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት እና የአውሮፓውያን ነገዴዎች ከ12 ሚልዮን የሚበልጡ ጥቁሮችን ከአፍሪካ ወደ ሰሜን እና ደቡብ አሜሪካ ግዛቶች በመርከብ በመውሰድ ለሀብታም ገበሬዎች ሸጠዋል።[56] ብዙውን ጊዜ በቤተሰብነት ያሉ እናት እና ልጅ ፣ አባትና እናት ፣ ወንድም እና እኅት፥ ዘመድ...እየተነጠሉ በመሸጥ ዳግም እንዳይገናኙ ተደርገዋል።

## (፮) 150 ዓመት የባርነት ስቃይ

በአሜሪካ ጀምስ ታውን የሰፈሩት የመጀመሪያዎቹ የብሪታንያ ሠፋሪዎች 14 ዓመት ከቆዩ በኋላ ፤ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን ጥቁ ሮች የዳች ነጋዴዎች 20 የሚደርሱትን በመርከብ ጭነው በ1619 ጀምስ ታዎን በቨርጂንያ አደረሱ።[57] በዚህ ጊዜ ግን አንዳንዶች እንደ ሚሉት በባርነት አስገድደው ሳይኾን ከላይ እንደ ተገለጠው ከአፍሪካ

[56] Susan Altman *The Encyclopedia of African- American Heritage., p., 223*
[57] Jackie Staddon *Baedeker's., p., 30*



አግዘው ያመጡበትን ደመወዝ (ዋጋ) እየሰጧቸው ለማሠራት አስበው ነበር ይላሉ ። በኋላ ግን ቀስ እያለ በአዳም ዘር ላይ ሊፈጸም የማ ይገባው ሰይጣናዊ ሥራ ቀጠለ ።

ለባርነት በሰንሰለት እያቆራኙ በማጋዝ ለከበርቴ በገበያ ቦታዎች እያዘዋወሩ እንደ ሸቀጥ ፤ ለእርሻ ወይም ለእርድ እንደ ተቀለበ ከብት ፣ ወንዶቹን ለግብርና ሥራ ፤ ሴቶቹን ለቤት እመቤቶች አገልጋ ይነት ፤ በሜሪላንድ የጥንት ዋና ከተማ አናፖሊስ እና በሌሎችም የገ በያ ቦታዎች ላይ ለሽያጭ ያውሏቸው ነበር ። ባርያ ማለት እንደ ቤት ዕቃ የሚቆጠር ማለት ነበር። ትንሽ ምግብ እየተሰጣቸው ጀንበር ወጥታ እስከምትጠልቅ ድረስ ይሠሩ ነበር። ቤታቸው በዚያው በእርሻ ቦታው ላይ ደሳሳ ጎጆ ነው ። በርግጥ ባርነት በዓለም ታሪክ ውስጥ በሮም እና በአቴና ገናናነት ወቅት ጀምሮ የነበረ እና መልኩን እየቀያ የረ የኖረ ቢኾንም ይህ እጅግ የከፋ ነበር ። ይህ የባርያ ንግድ በአሜ ሪካ ብቻ ሳይኾን ወደ ብራዚል እና ካርቢያን ደሴቶች በማጋዝ የሸን ኮራ አገዳ፣ ጥጥ እና የትንባሆ እርሻ ላይ አሰማርተዋቸው ነበር።



ለባርነት ሲወሰዱ እንዳያመልጡ በቀንበር ይጠመዳሉ ።
በሰንሰለት በማያያዝ ይታሠራሉ ።

በአሜሪካ ከጀምስ ታውንና ከማሣቹሴት ቤይ (የባሕር ሰርጥ) የብሪታንያ ነጋዴዎች ሸቀጣሸቀጥና ትንባሆ በመርከብ እየተጫነ ወደ አውሮፓ ለንግድ ሲያጓጉዙ ሀብታም ነጋዴዎች ከአውሮፓ ወደ አፍሪካ በመጓዝ ባርያን ከአፍሪካ በግድ ይዘው በሰንሰለት አስረው በመርከብ እየጫኑ ወደ አሜሪካ በመውሰድ ለአራሽ ከበርቴዎች ለሽያጭ በገበያ ላይ ያውላሉ። "ወርቃማው የሬክታንግሉ ንግድ" የተሰኘው ለዚህ ነው።

ነጻነት እስከታወጀበት እስከ 1776 ጊዜ ድረስ ለ150 ዓመት የባርነት ሥርዓት በአሜሪካ ውስጥ ተንሠራፍቶ ቆየ ። በዚህ ሥርዓት የባርያ ባለቤቶች ካህናቱና ምእመናኑ ኹሉ ናቸው ። በቅኝ ግዛት ሥር የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ካቶሊኩ ፣ አንግሊካኑ ፣ ኮንግርጌሽናሊስቱ፣ ፕሬስቤቴርያኑ፣ ባፕቲስቱ፣ ፍሬንድስ ፣ ሜተዲስት፣ ሉተራን፣ ዩኒቴርያኑ እና የተለያዩ የተሐድሶ አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ የባርያ ባለቤቶች እና የባርያ ነጋዴዎች ነበሩ ። ይህን ኢሰብአዊ ተግባር የሚቃወሙት ሜኖናይት፣ አሚሽና ኳከር የሚባሉት የክርስትና ተከታዮች ብቻ ነበሩ። የቅኝ ገዢው ክፍል ጥቅሙ እንዳይቀርበት ባርነትን አይቃወምም። በባርያ ጉልበት መጠቀም ዋናው የኢኮኖሚው ዋልታ ነበር።

የባርያው አሳዳሪውን ሥርዓት የሚደግፉ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሚሰጡት ምክንያት ሐዲስ ኪዳን በተሰበከበት ጊዜ እንኳ ባርነት ነበር፤ ስለዚህ ይህ ሥርዓት (ባህል) በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ሲጠቀሙበት ኖረዋል የሚል ነበር። በዚህ የተነሳ ተቃውሞ እና አለ መግባባት ክርክሩ ቀጠለ በአሜሪካ የክርስትና አማንያን መኻከል አለ መግባባት ተከሠተ።

የባርያን ሥርዓት ደጋፊው ክፍል

- (ሀ) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባርነትን በግልጽ አልከለከለም።
- (ለ) በኖኅ ካም ስለተረገመ የካም ልጆች አፍሪካውያን ናቸው።
- (ሐ) የእግዚአብሔር ሕዝቦች እስራኤላውያን ባርያዎች ነበሯቸው። በማለት ይኸን የመሳሰሉትን ምክንያቶች ያቀርባሉ።

ተቃዋሚው ክፍል ደግሞ

- (ሀ) ማንም ባርያ መኾን የሚፈልግ የለም ። ስለዚህ ማንም ሰው ሌላውን ባርያ ሊያደርግ አይገባውም ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በራስኽ ላይ ሊደረግ የማትወደውን በወንድምኽ ላይ አታድርግ" ብሏል።
- (ለ) ኖኅ የረገመው ልጁን ከነዓንን ነው እንጂ ካምን (ኩሽ) አይደለም (ዘፍ. 9፥18)።
- (ሐ) የእግዚአብሔር ሕዝቦች እስራኤላውያን አላስተዋሉትም አልሠሩበትም እንጂ 10ቱ ትእዛዛት ይህን አይነቱን አድራጎት ይከለክላል።



- (መ) በቅዱስ መጽሐፍ የሰውን ንብረቱን ብቻ ሳይኾን ነጻነቱን መስረቅ የከፋ ወንጀል ነው ። ስለዚህ የሰረቀ ፈጽሞ ይገደል ይላል (ዘጸ. 21፥16)።
- (ሠ) የክርስቶስ ትምህርት ወንድምኽን እንደራስኽ አድርገኽ ውደድ ነው። ይህን የመሳሰለ ምላሽ በመስጠት የሃይማኖቱን ትክክለኛ ትምህርት በማስረጃ ያቀርቡ ነበር (ማር. 12፥31)።[58]

ታሪክ እንደሚያስረዳው ባሮቹን ከአፍሪካ ገዝተው ወይም በመስረቅ አፍነው ሲያጓጉዟቸው በተጨናነቀ መርከብ ውስጥ አጭቀው በቂ ምግብ፣ በቂ ውሃና በቂ አየር የሚያስፈልጋቸውን ያኽል ሳያገኙ በማስቃየት ነበር ። በዚህ ምክንያት በባርያ ማጓጓዣዋ መርከብ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ባርያዎች ሲሞቱ ወዲያውኑ አስከሬናቸው ወደ ውቅያኖስ ይጣል ነበር። በአንድ በእንግሊዝ ጋዜጣ እንደተገለጸው ገና በአፍሪካ ውስጥ እያሉ በእስር ቤት ኾነው መጓጓዣ መርከቡ እስከሚቀርብ ድረስ ሲጠብቁ በመንገላታት የሞቱት ቍጥር ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሲደርስ ። ከእስር ቤት ከሞት ተርፈው ሲጓዙ የሚሞቱት አስከሬናቸው በአትላንቲክ ውቅያኖስ ውስጥ እየተወረወሩ የአሣ ምግብ የኾኑት በቍጥር ኹለት ሚልዮን እንደሚደርሱ ተዘግቧል።[59] ከሞት የተረፉት ደግሞ ከተሸጡ በኋላ በሥራው ክባድነት የተነሳ ይሞታሉ።

በቨርጂንያ ግዛት በወጣው ሕግ መሠረት አንድ ጥቁር አፍሪካዊ (ኔግሮ) ለማምለጥ ቢሞክር ተይዞ ይገረፋል ወይም ይገደላል ጀርባው እና ውስጥ እግሩ በእሳት ይለበለባል ፤ ዳኝነት ይታይ አይባልም። ጥፋት አጥፍቶ የተገኘ አገልጋይ ለሌላው ባርያ ግርፋቱን ዐይቶ እንዲፈራ በአደባባይ ፀግንድ ላይ በገመድ አንጠልጥለው በገዛ ወገኑ ያስገርፉታል፣ ይሰቅሉታል ፣ ይገድሉታል፤ ደሙም ደመ ከልብ ኾኖ ይቀራል ። ለጥቁር የበዳይ እና የተበዳይ ጉዳይ የሚመለከት ዳኛም ኾነ ወይም ሕግ የለም።

ይህንን በሰው ዘር ላይ የደረሰውን በደል የእንግሊካን ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳስ ሮዋን ዊሊያም የባርነት የነጻነት ቀን ኹለት መቶኛውን ዓመት በሚከበርበት ግንቦት 2007 ቀደምት አባቶቻቸው ያደረሱትን በደል በማንሳት ይቅርታ ጠይቀዋል ።

[58] **Mark A. Noll & Nathan O. Hatch** *Christianity in America USA 1983*
[59] The Londoner May 2007 p. 8




አፍሪካውያንን ለባርነት የሚያግዙበት መርከብ

በሰሜኑ ክፍል የሚኖሩት ባሮች ደቡብ ክፍል እንዳለ ሥርዓት ብዙ አያሰቃዩም ። እንዳንዶችም ሳያሰቃዩዋቸው እስከነአካቴው በነጻነት እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ አንቶኒ ጆንሰን የሚባለው ጥቁር የተከበረ የመሬት ከበርቴ ኾኖ ይኖር ነበር። በሰሜኑ ሕፃናቱ ኹሉ በነጻነት ከደቡብ ክፍል በተሻለ ኑሮ ይኖሩ ነበር ። ስለዚህም አንዱ ምክንያት በሰሜኑ ክፍል ታላላቅ የእርሻ ቦታ እንደ ደቡብ ባለመኖሩ ኢኮኖሚው በእርሻ ላይ ብቻ የተመሠረተ ባለመኾኑ ነው። በተጨማሪ በአሜሪካ የባርያ አሳዳሪ ያልኾኑ ከላይ የተጠቀሱት ስለሰዎች እኩልነትና ነጻነት ተቆርቋሪ የሃይማኖት ቡድኖች ነበሩ ። በዚህ የተነሳ የደላዌር ግዛት (እስቴት) በመጀመሪያ ለባርያ ነጻነትን ፈቀደ።

ባርያ ማለት አይኾንም ብሎ ሊቃወም የማይችል ፤ ነጻነት የሌለው ማለት ነው። ለዚህም ከላይ እንደተገለጸው አይኾንም ብለው የሚናገሩላቸው ብዙዎች በየዘመናቱ ተነስተዋል ። አጥብቀው ስለክርስትና እምነት የሚሰብኩ ሰባክያን ተነስተው ነበር።

ባርነትም ብቻ ሳይኾን ነዋሪው ሕዝብ ከቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት አስተዳደር ነጻ ለመውጣት ጥያቄ መጠየቅ ጀመረ። የክርስትና እምነት ሰባክያን ከ1730 እስከ 1750 ባሉት ዓመታት ታላቅ ቅስቀሳ በማድረጋቸው አማንያን ተበራክተው ነበር (Great. Awakening)። ስለዚህ የክርስትና እምነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በተግባር ይታይ በማለት በየቦታው እንቅስቃሴ ተጀመረ።

በዚህ በ1750 ባለው ዘመን ከአውሮፓ በተለይ ከእንግሊዝ ወደ አሜሪካ የፈለሱት የተለያዩ የእምነት ቡድኖች በፍጥነት መስፋፋት እና ማደግ ጀመሩ ። ዘመኑ ከላይ ባየነው በሰንጠረዥ እንደተረዳነው ብዙ ታላላቅ ትምህርት ቤቶች የተከፈቱበት ጊዜ ነበር። በነዚህም ትም



ህርት ቤቶች ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ፤ የመንግሥት ግብር ስለተጫናቸው ድሆች፤ ስለ ሥራ አጦች ፤ የቁማር ሱስ ስላለባቸው ሰዎች ፤ ስለሌሎችም ማኅበራዊ ጉዳዮች በየትምህርት ቤቱ ይነጋገሩባቸው ነበር። ብዙ የወንጌል ሰባኪዎች በተለይ በተለያየ አመለካከት እየተነሱ በጣም ይሰብኩ ነበር ። በማሣቹሴትስ ግዛት በ1734 ጆናታን ኤድዋርድ የተባለ የዳች ሬፎርምድ ቸርች ሰባኪ አጥብቆ የባርነት ሥርዓትን በመቃወም ጭምር ስለነጻነት ይሰብክ ነበር።

## ምዕራፍ ፬

## የአሜሪካ ነዋሪዎች የነጻነት ትግል

**ለኹሉ ዘመን አለው ፣ ከሰማይ በታች ለኾነው ነገር ኹሉ፤ ጊዜ አለው ። ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሰላምም ጊዜ አለው። (መጽ. መክ. 3፥1-9)**

በቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት ላይ ጥያቄው ቀጠለ ፤ ነጻነትን ለመጐናጸፍ፣ የወንጌል ሰባክያን ቅስቀሳ እና እንቅስቃሴ ድህነትን አጥፍቶ እኩልነትን ፣ ባርነትን አጥፍቶ ነጻነትን ለማግኘት የሚደረገው ስብከት እያደር በአሜሪካ በየቦታው ተሰራጨ ፤ በዚህም የተነሳ ጠብ እና አለመግባባት ተፈጠረ። በ1773 በነዋሪው ኅብረተሰብ ላይ ድህነት ያስከተለውን ነገር ተቃውሞ በማሰማት ለብሪታንያ የቅኝ ገዢው መንግሥት ግብር ላለመክፈል ዐመፅ ተጀመረ። በተለይም የሉተራን ተከታዩ ፓስተር ሙለንቤርግ መጽሐፈ ምክብብን በመጥቀስ ሲሰብክ ፤ ወንጌል ሰባኪዎች ፖለቲካ ውስጥ መግባት የለባቸውም በማለት ተቃውሞ ደርሶበት ነበር ።

ይህንን ዐመፁን የማይደግፉት ሰባክያን ጦርነት ለምን ይደረጋል ኢየሱስ ክርስቶስ ጦርነት እንዲደረግ አልፈቀደም ስለፍቅር አስተማረን እንጂ በማለት ሲገልጹ ዐመፁንና ጦርነቱን የሚደግፉ ሰባክያን ደግሞ በበኩላቸው ለነጻነት ሲባል መዋጋት አለብን የሚለውን አመለካከታቸውን ለመደገፍ ለስብከታቸው መነሻ የሚያደርጉት ከላይ እንደተገለጸው መጽሐፈ መክብብን ነበር።

ለኹሉ ዘመን አለው፤
ከሰማይ በታች ለኾነው ነገር ኹሉ፤ ጊዜ አለው ።
ለመወለድ ጊዜ አለው ፥ ለመሞትም ጊዜ አለው ፤

ለመትከል ጊዜ አለው፤ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው፤
ለመግደል ጊዜ አለው ፤ ለመፈወስም ጊዜ አለው ፤
ለማፍረስ ጊዜ አለው ፤ ለመሥራትም ጊዜ አለው ፤
ለማልቀስ ጊዜ አለው ፤ ለመሳቅም ጊዜ አለው ፤
ዋይ ለማለት ጊዜ አለው ፤ ለመዝፈንም ጊዜ አለው ፤
ድንጋይን ለመጣል ጊዜ አለው፤ ድንጋይንም ለመሰብሰብ ጊዜ አለው ፤
ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው፤ ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው፤
ለመፈለግ ጊዜ አለው ፤ ለመጥፋትም ጊዜ አለው ፤
ለመጠበቅ ጊዜ አለው ፤ ለመጣልም ጊዜ አለው ፤
ለመቅደድ ጊዜ አለው ፤ ለመስፋትም ጊዜ አለው ፤
ዝም ለማለት ጊዜ አለው ፤ ለመናገርም ጊዜ አለው ፤
ለመውደድ ጊዜ አለው ፤ ለመጥላትም ጊዜ አለው ፤
<u>ለጦርነት ጊዜ አለው፤ ለሰላምም ጊዜ አለው።</u> በማለት ይጠቅሳሉ።[60]

ከአውሮፓ የሚገባው ወረቀት ፣ ቀለም ፣ ሻይ ቅጠል ሌሎችም ላይ የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት የቴምብር የቀረጥ ሕግ በማውጣት ዋጋ ጨመረ። (Stamp Acts) በዚህ የነዋሪው ተቃውሞ ከፍተኛ ኾነ። የቅኝ ተገዢዎቹ በከተማዋ እየዞሩ የመንግሥት ቀረጥ የሚሰበስቡትን ቀራጮች ከከተማዋ እንዲወጡ ማባረር ጀመሩ። የብሪታንያ መንግሥት አስገድደው ቀረጥ (ታክስ) የሚያስከፍሉ ወታደሮችን ወደ ቦስተን ላከ፤

ስሕተቱ ግን በብሪታንያ የሚኖሩት ሕዝቦች በፓርላማቸው ውስጥ ተወካዮቻቸው ግብር እንዳይከፍሉ የሚከራከሩላቸው ሲኖሩ በአሜሪካ ግን በቅኝ ተገዢዎቹ ተወክሎ በፓርላማ አቤቱታቸውን የሚያቀርብላቸው የሚከራከርላቸው አልነበረም፤ በዚህ የተነሳ ፓርላማው ቀረጥ የማስከፈል መብት የለውም የሚል ቅስቀሳ መቀጣጠል ጀመረ፤ ዐመፁ እየገፋ ኼደ ። ሕዝቡም ከብሪታንያ ከእንግሊዝ ግዛት የሚመጣውን ሸቀጥ ላለመግዛት ወሰነ ፤ የብሪታንያ ነጋዴዎች ተጨነቁ ፤ ነገሩ እየተካረረ መጣ።

ጥላቻው ከብሪታንያ የቅኝ ገዢው መንግሥት ጋር እየተካረረ መጥቶ መጋቢት 5 ቀን 1770 በቦስተን ዐሥር የቅኝ ገዢው መንግሥት ወታደሮች እና ዐሥራ ስድስት የቅኝ ተገዢዎች አሜሪካውያን ነዋሪዎች

[60] Toby Mac & Michael Tait *Under God* p. 21, 23



መካከል ግጭት ተፈጥሮ ሰው ሞተ ። ግጭቱ ካለፈ ከወር በኋላ ሕዝቡ ከብሪታንያ የሚመጣውን ሸቀጥ አንገዛም ስላሉ ፓርላማው በአንድ በኩል የሻይ ቅጠል የሸቀጥ ግብር (ታክስ) ዋጋ ቀነስኩላችሁ ብሎ ሲያውጅ በሌላ በኩል የቦንዳ (Stok) መግገርያውን ዋጋ ቀረጥ ጨመረ ። በዚህም ሳቢያ በታኅሣሥ 16 ቀን 1773 በቅኝ አገዛዝ የተያዙት የአሜሪካ ነዋሪዎች ዐመፃቸውን እያጠናከሩ ኼዱ ። ምስጢራዊ አሠራር የሚሠሩ የተደራጁ ቡድኖች ልክ እንደ አገሬው ቀወላጅ ኢንድያኖች አለባበስ ልብስ ለብሰው በመሰባሰብ 342 ሳጥን ሻይ ቅጠል ከሦስት ታላላቅ መርከቦች ላይ እና ከወደቡ እያነሡ በቦስተን ባሕር ላይ ዘረገፉት። ይህ የቦስተን ሻይ ቅጠል ቀረጥ ተቃውሞ "የቦስተን ቲ ፓርቲ"[61] በመባል ይታወቃል ። 10,000 ሺ ፓውንድ የሚያወጣ ሻይ ቅጠል ውቅያኖስ ውስጥ ገባ ። የብሪታንያ መንግሥት የበለጠ ተበሳጨ፤ ወዲያው ፓርላማው ዐዲስ የመቅጫ ሕግ (Intolerable Acts) አወጣ ። ጠቡን ግን እስከነ አካቴው የበለጠ እንዲካረር አደረገው እንጂ መፍትሔ አልኾነም ።

ይህንን በፓርላማ የወጣውን ዐዲስ ሕግ በተመለከተ የነጻነት ጥያቄ ለመጠየቅ ከ13 የቅኝ ግዛቶች የተወጣጡ የ12ቱ ግዛቶች ተወካዮች ያሉበት በፔንሲልቫንያ ግዛት በፊላዳልፊያ ከተማ ውስጥ የመጀመሪያው አገር አቀፍ ወይም ኮንቲኔንታል ኰንግረንስ ተብሎ የሚታወቀው ስብሰባ በነዋሪዎቹ ተካኼደ።

በዚህ ጉባኤ ምክር ለማድረግ (ለኰንግረስ) የተወከሉትን የመጀመሪያዎቹን የአሜሪካ ነጻ አውጭዎች ነበሩ ። እነዚህም ከየግዛቱ የተወጣጡት ሰዎች አገሪቷ ከቅኝ ገዢው መንግሥት ነጻ እንድትኾን ታገሉ፤ አገሪቷን የሚመሩ ፕሬዘዳንቶችም ኾኑ።[62]

## (፩) የመጀመሪያው ፕሬዘዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን (ኤጲስቆፓል)

ከቨርጂንያ የተወከለው ጆርጅ ዋሽንግተን፡- በቅድመ አያቱ የመጀመሪያዎቹ የእንግሊዝ ሰደተኞች ዘርያ ነው። ቅድመ አያቶቹ በቨርጂንያ ቀደም ብለው የሠፈሩ ሲኾኑ የቨርጂንያ አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አማኞች ነበሩ ። እሱም በ27 ዓመቱ ማርታ ዋሽንግተንን አገባ ። ይህችም ሴት ትጉህ የኤጲስቆፓል (የአንግሊካን) የክርስትና እምነት ተከታይ ነበረች ። ጆርጅ ዋሽንግተን የዚሁ የክርስትና እምነት ተከታይ

[61] THE BOSTON TEA PARTY
[62] George Sullivan MR. *PRESIDENT A Book of U.S.A Presidents p. 1ff--*

ይኹን እንጂ በኋላ ዘመን በክርስትና እምነት አማኝ መኾኑ አጠራጣሪ እንደነበር በአንዳንዶች የታሪክ ጸሐፊዎች ተተችቷል ። እምነት የሌለው ዴይስትስ (Deists) ወይም ዲያቲዝም[63] የሚባለውን የፍልስፍና እምነት ከሚከተሉት አንዱ እንደነበር ይናገራሉ ። ይህ የእምነት አመለካከት በአውሮፓ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ በነበረ ጥላቻ መነሻ ኾኖ የተፈጠረ ነው ። ጆርጅ ዋሽንግተን ከቤተሰቡ የወረሰው መሠረቱ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን አማኝ ነው ። ኾኖም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ-ጠቃሚነት ብዙ ጊዜ ይናገር ነበር ።

> ያለ እግዚአብሔር እና ያለ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክለኛ ፍትሕ ዓለምን መምራት እና ማስተዳደር በፍጹም አይቻልም ፤ ይል ነበር።

ጆርጅ ዋሽንግተን በሞያው ደግሞ በግብርና ላይ ተሠማርቶ መሬት ቀያሽ እና ገበሬ ነበር ። እንዲሁም በወታደርነት ሙያ አለቃና ኮማንደር ኾኖ ያገለገለ ነው ። በብሪታንያ መንግሥት እና በፈረንሳይ መንግሥት መካከል በነበረው አለመግባባት በቅኝ ገዢው በብሪታንያ ጦር በወታደርነት ተሰልፎ በአህዮ ሸለቆ በ1753 ተልኮ በውጊያ ላይ ተሳትፏል። በኋላ ግን እንደ ሌሎቹ ነዋሪዎች ኹሉ የብሪታንያ መንግሥት ቅኝ አገዛዝ እሱንም ስላስመረረው ተቃውሞውን በግልጽ ያሰማና ይናገር ነበር። የነጻነቱ እንቅስቃሴ በተፋፋመበት ወቅት በክፍሉ ወታደሮች ከቨርጂንያ ተመርጦ ፊላዳልፍያ ላይ መስከረም 5 ቀን 1774 በተከፈተው የመጀመሪያ የኰንግረስ ስብሰባ እንዲካፈል ተላከ።

በዚህ የመጀመሪያ ኰንግረስ ላይ የተካፈሉ ተወካዮች 56 ነበሩ ። እነዚህ ሰዎች በጊዜው ባገሪቱ ውስጥ እውቅና የነበራቸው ፤ በሀብት የበለጸጉ ፤ ከቤተሰብ የወረሱት የእርሻ መሬት እና ባርያ የነበራቸው ፤ በኮሌጆች ገብተው የተማሩ ምሁራን ነበሩ።

ከነዚህም ውስጥ ጆርጅ ዋሽንግተንን ጨምሮ የፍሪሜሶን[64] (ምስጢራዊ ማኅበር) አባላት እንዳሉበት ይነገራል። ይህም ምስጢራዊ

[63] Deism = a movement or system of thought advocating natural religions based on human reason rather than revelation, emphasizing morality, and in the 18th century denying the interference of the creator with the laws of the universe.
[64] Freemasonry = the beliefs and practices of a group of linked national organizations open to men over the age of 21, united by a common code of morals and certain traditional 'secrets'. Freemasons believe in God, whom they call 'the Great Architect of the Universe' (The H. Encyclopedia 2000 p.415)



ቡድን የተፈጠረው በእንግሊዝ አገር ነው። በአሜሪካ የተፈጠረበትም ዘመን በዚሁ በጆርጅ ዋሽንግተን ዘመን ሲኾን የተፈጠረበት አንዱ ምክንያት ይህንኑ የካቶሊክን የክርስትና እምነት ለመቃወም እንደ ኾነ ይነገራል። የዚህ የፍሪሜሶን አባል የሚኾኑ ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በላይ የኾኑ ወንዶች ብቻ የሚሳተፉበት ምስጢራዊ ማኅበር ነው ። እምነታቸው ይህን የሚታየውን ጠፈር ጨምሮ የፈጠረውን አምላክ እናምናለን የሚል ነው ። በግልጽ ግን እምነት ተብሎ አምልኮት ሲፈጸም ታይቶ አይታወቅም።

ይህ የመጀመሪያው የኰንግረስ ስብሰባ በሳም አዳምስ ጸሐፊነት በፊላዳልፊያ ካርፔንተር አዳራሽ በጸሎት እንዲከፈት ሐሳብ ቀረበ ። ነገር ግን ኹሉም አልተደሰቱም ፤ ምክንያቱ ከተለያዩ የክርስትና እምነት ክፍል ስለመጡ የጐሪጥ ይተያዩ ነበረና ነው ። ኾኖም ግን መሰባሰቡ ቀጥሎ ጸሎት ተደርጎ ንግግሩ ተጀመረ። አንዳንድ የየግዛቱ ተወካዮቹ ከብሪታንያ መንግሥት ጋራ ለመኾን ፈለጉ፥ በዚህም የተነሳ አስጨናቂ የኾነው የሕግ ቀንበር እንዲነሳላቸው የብሪታንያ መንግሥትን ለመጠየቅ ወሰኑ ። ውሳኔው እና ንግግሩ ከተፈጸመ በኋላ ጸሐፊው አደም "ክርስቲያኖች በአንድነት በመኾን ልዩነታችንን ትተን እንደ አንድ ሰው ኾነን አጎንብሰን እና ተንበርክከን ለኀያሉ ጌታ ለሚፈልጉት እና ተስፋ ለሚያደርጉት የሚረዳ ስለኾነ መጸለይ አለብን አለ ።" በዚህ ጊዜ ቄሱ (ሬቨረንድ) ጃኮብ ዱሼ ጸሎቱን ይመራ ጀመር ፤ ይጸልይ የነበረው አንዱ ክፍል መዝሙር 34 (35) ነበር።

ጆን አደምስ ለባለቤቱ ደብዳቤ ሲጽፍ የስብሰባው ተካፋዮች ነጻነታቸውንና መብታቸውን ለማግኘት በእንባ በታጀበ ድምጽና ጸሎት ለዐራት ቀኖች እየጸለዩ እንዳሳለፉ ገልጸላታል ። ዛሬ በዶላሩ ላይ ያለው "በእግዚአብሔር እናምናለን"[65] የሚለውም ጥቅስ አንዱ መነሻ ይህ ነው።[66]

ይኸም ኹሉ ኾኖ ለብሪታንያ መንግሥት እና ለንጉሥ ጆርጅ ሣልሳዊ የቀረበው ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ትክክል ያልኾነውን የፓርላማ ውሳኔ በመቃወም በድጋሚ ለግንቦት ወር 1775 ለመገናኘት ወስነው በቀጠሮ ተለያዩ ። ነገር ግን የስብሰባው ጊዜ ሳይደርስ ሌላ ዐመፅ ተካኼደ። ሕዝቡ ከብሪታንያ ከእንግሊዝ ግዛት የሚመጣውን ሸቀጣሸቀጥ ላለመግዛት ወሰነ። ይኸን ተቃውሞ ለማዳከም የቅኝ

[65] IN GOD WE TRUST
[66] Gary De Mar., *P.,59*

ገዢው የብሪታንያ መንግሥት በአገር እና በመንግሥት ላይ የሚያም ትን፣ የሚከዱትን በማሰር እንዲሁም በስቅላት እንዲቀጡ ያደርግ ጀመር። ጠቡና ዐመፁ ግን የበለጠ ተፋፋመ እንጂ አልበረደም።

ይህ ኹኔታ በክርስቲያኖች ዘንድ በሐሳብ መከፋፈልን አመጣ። የእስኮትላንድ ፕሬስቢቴሪያኖች፣ ሉተራኖች፣ ባፕቲስት፣ ዩኒቴርያንና ፒሩታንስ (ኰንግርጌሽናሊስት) ይበልጡን በአሜሪካ ጐን ነጻነት እን ልጋለን በማለት ለትግል ተሰለፉ ። በግማሽ የሚኾኑት የአንግሊካን ቤተክርስቲያኖች እና ካቶሊኮች ቀኝ ገዢውን የብሪታንያ መንግሥት ደገፉ ። ሦስተኛው የሃይማኖት ቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጦርነትን አይ ፈቅድም የሚሉ የጦርነትን ሐሳብ የሚቃወሙ በጦርነቱ ላለመግባት ወሰኑ። እነዚህም ሞርቭያውያን፣ ኳከር፣ አሚሽና ሜኖናይት ናቸው። ምክንያታቸው ሃይማኖታችን አይፈቅድም በማለታቸው ከኹለቱም ወገን ያልኾኑ ሰላም ፈላጊዎች ስለነበሩ (Pacifists) ሲሳደዱ ኖሩ።[67]

በዚህ የተነሳ ጆርጅ ዋሽንግተን በዚያው ጥቂት የኾኑትን ጓደ ኞቹን ይዞ ሸፈተ ፤ ጦርነት ተቀሰቀሰ ። ቀስ እያለ ብዙ ሰው ወደ ዐመፁ መግባት ጀመረ ። የአንግሊካን ቀሳውስቶች የተሾሙት ከዋናዋ ቤተ ክርስቲያን ከእንግሊዝ ስለኾነ የብሪታንያ የቅኝ ገዢውን ንጉሥ ለመርዳት ቃል ስለገቡ ከአሜሪካውያን ጎን አልተሰለፉም ። በዚህም ሳቢያ ጆርጅ ዋሽንግተን ለጸሎት በቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቅዳሴው ሳ በቃ ፤ ቅዱስ ቁርባን ሳይቀበል ረግጦ ወጣ ተብሎ ይነገራል ። በጸሎ ቸው ንጉሡን ያኑርልን ፣ ይጠብቅልን በማለት ሥርዐቱን ጠብቀው ይጠሩ ነበር ። ይህም የብሪታንያን የቅኝ ገዢ መንግሥት የማይደግፉ ትን አንዳንዶቹን የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትን አስኮርፏል። በፕሮቴስታንት ፓስተሮቹም ዘንድ መከፋፈልን ፈጥሯል።[68]

የብሪታንያን የነገሥታት ቤተሰቦች በጸሎት አለማንሳት በሥሩ መተዳደርን አለመፈለግ ስለኾነ ይህ ኹሉ ተጨማምሮ ንጉሥ ጆርጅ ሣልሳዊ እና መንግሥቱን በጣም አስቆጣ ። ስለዚህ መንግሥት ተጨ ማሪ ወታደር ወደ አሜሪካ ላከ ። በሌላ በኩል ደግሞ የነጻነት ተዋጊ ዎቹ አሜሪካውያን ገበሬውን፣ ብረት ቀጥቃጩን ፣ አንጥረኛው ሌሎች ንም ሠራተኞች ለጦርነቱ ያዘጋጁ ጀመር ። በሚያዚያ ወር በ1775 እነዚሁ ጥቂት አሜሪካውያን ከብሪታንያ ወታደሮች ጋር በሌክሲንግተን

[67] David Mauk and John Oakland., *p., 355*
[68] Jeffrey B. Webb., *p., 120*



እና ኮንኮርድ ማሣቹሴትስ ላይ የጦርነት ትግል ገጠሙ። የቅኝ ገዢዎቹ በጦርነቱ የማረኩትንና ያመፁትን ብዙ ሰዎች በእስር ቤት አጐሩ።

ከጥቂት ወራት በኋላ ሰኔ 17 ቀን በባንከር ሂል ሌላ ውጊያ ተደረገ። በቦስተን አጠገብ እንዲሁ ከባድ ጦርነት ተካኼደ። በዚህም ወቅት የአሜሪካውያኑ የጦር መሪ የታወቀው የቨርጂንያ ገበሬ እና ወታ ደር ጆርጅ ዋሺንግተን ነበር ፤ ከብሪታንያ ጦር 273 ወታደሮች፤ ከአሜ ሪካኖች ጦር 93 ወታደሮች በጦርነቱ ላይ ወደቁ። ከዚህ በኋላ አሜሪ ካውያኑ በጥቂቱ ድልን መቀዳጀት ጀመሩ።

(፪) የነጻነቱ አዋጅ (ሐምሌ 4 ቀን 1776)

በበጋው ወራት በፊላዳልፊያ የኹለተኛው ኰንግረስ ስብሰባ ላይ ከብ ሪታንያ ቅኝ አገዛዝ መንግሥት ነጻነት የሚወጡበትን አዋጅ ረቂቅ የሚያረቁ የኮሚቴ አባላቶች ተመረጡ።


እነዚህም ቶማስ ጀፈርሰን ከቨርጂንያ፤ ጆን አዳምስ ከማሣቹሰ ትስ፣ ቤንጃሚን ፍራንክሊን ከፔንሲልቫኒያ፤ ሮጀር ሼርማን ከነክቲኬት እና ሮበርት ሊቪንግስተን ከኒው ዮርክ ነበሩ።

የመጨረሻው ረቂቅ በኮሚቴው ጸሐፊው በቶማስ ጀፈርሰን ታዘ ጋጅቶ ቀረበ። አንዳንድ ቃላቶችን በጋራ ካስተካከሉ በኋላ ሰኔ 28 ስብ ሰባ ላይ ቀርቦ በሐምሌ 4 ቀን የ13ቱ ግዛቶች ተወካዮች በጠቅላላው 56 አባላት በፊርማቸው አጸደቁት።[69]

በዚህም ከብሪታንያ መንግሥት ነጻ መኾን ብቻ ሳይኾን የተከ ፋፈለውና የተለያየው የክርስትና አማኞች በክርስትና ሃይማኖታቸው ተቻችለው በትዕግሥት እንዲኖሩ፤ ኹሉም እኩል መብት እንዲኖረው ተስማሙ። ከዚህም በላይ የባርያን ንግድ በመቃወም ማንኛውም አገል ጋይ ባርያ ነጻ እንዲኾን አወጁ ። በዚሁ መብት ከአሜሪካ ውጭ በፈረንሳይ እና የፈረንሳይ የቅኝ ግዛት በነበረችው በሀይቲ ባርያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ነጻ ኾኑ።[70] ዋናው ምክንያት ቶማስ ጀፈርሰን በፈረን ሳይ የተጀመረውን የነጻነት ዐመፅ ይደግፍ ስለነበር እና ባርያን ነጻ ለማውጣት ዋና ምኞቱ ስለነበረ ነው።[71] ኾኖም ግን በደቡብ ያለው የአ

[69] Applewood Books *The Declaration of Independence p., 14*
[70] Warren J. Halliburton & William Loren Katz *American Majorities and Minorities p., 29*
[71] The History of French Revolution 1789

ሜሪካ አህጉር የሚኖሩ ሀብታሞች የግል ባርያ ሊኖረን ይገባል በማለት አዋጁን ሳይቀበሉ አስከፊውን የባርነት ሥርዓት ሳያስወግዱ ለብዙ ዓመታት ቆዩ።



የነጻነት አዋጁን ለማጽደቅ ሲፈራረሙ[72]

የነጻነት አዋጁ እና መነጋገሪያው እንዲህ የሚል ነበረ ። ንጉሥ ጆርጅ ሣልሳዊ የታላቋ ብሪታንያ ንጉሥ ከሕዝቦቹ ጋራ ያለውን ውልና ፥ ስምምነት እንዲሁም ቃል ኪዳን አፈረሰ በማለት ከዚህ የሚከተለው አዋጅ ለሕዝብ እንዲነበብ ወሰኑ።

ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩልነት ነው ። ይኽም የተሰጣቸው ከፈጣሪያቸው ሲኾን የመኖር መብታቸውን ከእነሱ መለየት የማይቻል ነው ፤ ከነዚህም መኻል ሕይወት፣ ነጻነት እና ደስታን ማግኘት ነው ። ይህ የጨበጥነው እውነታ በራሱ ማስረጃ ነው። እነዚህንም መብቶች ለማረጋገጥ መንግሥታት በአዳም ልጆች ተመሠረቱ። እነዚህም መንግሥቶች ኀይላቸው ሥልጣን ከተቀበለው ሕዝብ በጎ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ (የመነጨ) ነው። የማንኛውም የመንግሥት አካል እነዚህን ዓላማዎች መፈጸም ካቆመ ወይም አፍራሽ ከኾነ ፤ ይህንን ለማስወገድ የሕዝቡ መብት ነው። እንዲሁም ዐዲስ መንግሥት ለማቋቋም፤ መሠረት ለመጣል፤ በሕዝቡ ዘንድ በጣም የተሻለ የኾነ መንገድ፥ ደስታ እና ደኅንነት እንዲገኝ ይህ መመሪያ ነው።

[72] Wikimedia.org



ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ ነጻ መውጣታቸውን የሚገልጸውን ይህን ዝነኛውን የነጻነት አዋጅ በቶማስ ጀፈርሰን ሐምሌ 4 ቀን ለሕዝብ ተነበበ። እንዲሁ ሐምሌ 9 ቀን ምሽቱ በድስት ሰዓት ላይ በዮርክ ደሴት ላይ ላሉት ወታደሮች ተነበበ ፤ በዚሁ ቀን በኒው ዮርክ ያለው የንጉሥ ጆርጅ ሣልሳዊ ሐውልትን ገፍትረው ጣሉት፤ ወታደሮቹም ነጸ ወጡ። የነጸነት አዋጁ[73] ለአሜሪካ ሕዝብ በድጋሚ ተነበበ።[74]

ይህ የነጻነት አዋጅ የታወጀበት ቀን እስከ ዛሬ ድረስ የነጻነትን እና የእኩልነት መብት የተሰጠበት ቀን ስለኾነ የአሜሪካ ሕዝቦች በጣም ያከብሩታል ። በዚህ ቀን በየዓመቱ በአሜሪካ ከተሞች ርችት እየተተኮሰ በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል። ሕዝቡ ኹሉ ውጭ ቆመው ርችቱን እያደነቁ የነጻነት በዓሉን በመዘመር እና በመዝናናት ያከብሩታል ፤ በቤተ ክርስቲያኖች የተለየ የጸሎት አገልግሎት ይደረጋል፤ የአሜሪካ ባንዲራ በየቦታው ወጥቶ ይውለበለባል።[75]

በዚህ በነጻነት አዋጅ ጉባኤ በኰንግረስ ስብሰባ ወቅት ጆርጅ ዋሽንግተን የጦር መሪ ኾኖ እንዲቀጥል ተደረገ ። የነጸነት አዋጁ ወዲያው እንደታወጀ ቀደም ሲል የእንግሊዝ ሠፋሪዎች (ፒሩታንስ) ያከበሩት የምስጋና ቀን ዕለተ አኰቴት (Thanks giving) በደመቀ ኹኔታ እንዲከበር ተወሰነ። ከእስኮትላንድ፣ ከሆላንድ እንዲሁም ከሌሎችም ቦታዎች በቁጥር ወደ 20ሺ የሚደርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅዎች ወደ አሜሪካ እንዲገቡ ተደረገ። የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት ክፍል ምንም ነገር እንዳያስገባና ሥልጣን እንዳይኖረው ተወሰነ ፤ ወዲያው በየቦታው ያለውን የብሪታንያ ንጉሥ የመታሰቢያ ሐውልት አፈረሱ።

[73] DECLARATION OF INDEPENDENCE
[74] **B.J. Lossing's.**, *p., 2*
[75] ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ በቦልቲሞር ከተማ የደረሰኩት የነጻነት በዓል በሚከበርበት ሐምሌ 4 ቀን ነበር። በዚህ ቀን ነዋሪው ሕዝብ በምሽት ላይ ከቤቱ ወጥቶ የምሥራች ማብሠሪያ ርችት በሚተኮስበት (ዳወን ታውን) በባሕሩ ወደብ አጠገብ ተሰብስቦ ርችቱን እያደነቀ ይዝናና ነበር።

በብሪታንያ መንግሥት ግብር እና እንዲሁም የተሳሰረ ሕግ መጠላለፍ የሰለቸው የጦሩ ዋና መሪ ጆርጅ ዋሽንግተን ከቦስተን የቀሩትን የቅኝ ገዢውን ባለሥልጣኖች ጠራርጎ አስወጣ ። በ1778 በሰኔ ወራት በድጋሚ ከፊላዳልፍያ የቀሩትን አስወጣ ። አሜሪካውያኑ ከ5 ዓመት ትግል በኋላ በሚያስተማምን ኹኔታ በጥቅምት ወር 1781 ጦርነቱን አጠናቀቁ። ከኹለት ዓመት በኋላ መስከረም 3 ቀን 1783 እጃቸውን ያልሰጡ የብሪታንያ ወታደሮች በሙሉ ተማረኩ። የዐሥራ ሦስቱን የቅኝ ግዛት የኾኑት ግዛቶች ከብሪታንያ ቅኝ ግዛት ነጻ ወጥተው "ዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ" ተብለው ተሰየሙ።

በብሪታንያ መንግሥት እጅ የቀሩት ካናዳ ፤ የአሜሪካ የሰሜን ምዕራብ ቦታዎች፣ እንዲሁም ኖቫ እስኮሺያ (ዐዲሲቷ እስኮትላንድ) የሚባሉት ቦታዎች ብቻ ነበሩ ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ምክንያት የእንግሊዝ ሕዝቦች በታሪክ 13 ቁጥርን ዕድለኛ ቁጥራችን አይደለም ይሉታል ። ምናልባት የዐሥራ ሦስቱን የቅኝ ግዞቶች ቦታዎች ላይ ነጻነት ተዋጊዎች ያደረሰባቸውን ሽንፈት ስለሚያስታውሳቸው ሊኾን ይችላል። ከጆርጅ ዋሽንግተን ጋር ለነጻነት የታገሉት የታወቁት ሰባቱ ሰዎች ለአሜሪካ የነጻነት አዋጅ ካወጁ በኋላ ከብሪታንያ ቅኝ ገዢዎች ጋራ ያለው ጦርነት እስከሚያበቃ ፊላዳልፍያ ከተማ ውስጥ በኤጲስኮፓል ክራይስት ቤተ ክርስቲያን የተፈራረሙበትን የነጻነት አዋጅ ደብቀው አቆዩት።

## (፫) የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት፣ ኰንግረስ እና የጸሎት ቤት

**የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት፣ የመጀመሪያው ኰንግረስ በ1787[76] የኰንግረስ ጸሎት ቤት የካቲት 30 ቀን 1789 ተመሠረተ ።[77] ከዚያም ጳጳስ**

[76] ኰንግረስ ማለት፥ ሕግ አውጪ ክፍል ነው ። ሴኔት እና ሀውስ ኦፍ ሪፕሬዘንታቲቭ ኹለቱ በአንድነት በኰንግረስ ይሰበሰባሉ። ሴናት ማለት= ከተለያዩ ግዛቶች (ከእስቴቶች) የሚወከሉት 2 ሰዎች ከ50 ግዛቶች በአጠቃላይ መቶ ሰዎች የሚሳተፉበት ነው። የሀውስ ኦፍ ሪፕሬዘንታቲቭ ቁጥር ደግሞ 435 ነው ፤ እነዚህ በየኹለት ዓመቱ ይመረጣሉ።

[76] **Gary De Mar.** *P., 52*

[77] **Did You Know?**

A paid minister, whose salary has been paid by taxpayers since 1789 opens every session of Congress with prayer,

Bible verses are etched in stone all over the federal buildings and monuments throughout Washington, D.C.



ሳሙኤል ፕሮቮስት እና ቄስ (ሪቨረንድ) ዊልያም ሊንን ደመወዝ የሚከፈላቸው የምክር ቤት እና የተወካዮች ምክር ቤት (የሴናት እና የሃውስ ኦፍ ሪፕሬዜንታቲቭ) የመጀመሪያው አገልጋዮች ኾኑ።[78] ኹል ጊዜ ስብሰባዎችን (ጉባኤውን) በጸሎት መክፈት በዚያን ጊዜ ተጀመረ። ይህ ዛሬ በኀምሳው ግዛቶች (ስቴቶች) ያሉት አስተዳደር እንዲሁም የምክር ቤት እና የተወካዮች ምክር ቤት (ሴናት እና ሀውስ ኦፍ ሪፕሬዘንታቲቭ) ጉባኤዎች የሚጀምሩት በጸሎት ነው። በዋናው የኰንግረስ አዳራሽ ምክር ቤት (ካፒቶል) ውስጥም የጸሎት ቤት አለ።

የሃምሳ ሰባት ዓመቱ ጆርጅ ዋሽንግተን በዚሁ ዓመት በሚያዚያ ወር በኒው ዮርክ ከተማ በፌድራል አዳራሽ የውሕደቱ የመጀመሪያው ፕሬዘዳንት ኾኖ ያለምንም ተፅዕኖ መጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦለት እጁን በላዩ በመጫን አገሩን ለማገልገል ቃለ መሐላ ፈጸመ ። ከቃለ መሐላው በኋላ በራሱ ሐሳብ "ቃሌን በመሐላ እሰጣለሁ ለዚህም አምላክ ሆይ እርዳኝ ብዬ እማጸናለሁ" (I SWEAR, SO HELP ME GOD) በማለት ተጨማሪ ቃል ጨመረ ። በዚህም ተጨማሪ ቃሉ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን ጠንካራ እምነት እንዳለው ያሳያል ። ከዚህ በኋላ በአሜሪካ የሚመረጡት ፕሬዚዳንቶች ይህን ባህል በመከተል ሲመረጡ መጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ ይቀርብላቸውና በላዩ ላይ እጃቸውን አድርገው ቃለ መሐላ ይፈጽማሉ።

ጆርጅ ዋሽንግተን ቃለ መሐላ ከፈጸመ በኋላ በቅዱስ ጳውሎስ የጸሎት ቤት ከፍተኛ የጸሎት ሥርዓት ተከኼደ።[79] ይህም ከዘውድ መጫን በቀር በኢትዮጵያውያን ነገሥታት ዘንድ ሲፈጸም እንደኖረው እና አኹንም በብሪታንያ ነገሥታት እንደሚደረገው የንግሥና ሥርዓት አይነት ነበር።

አንዳንዶች እንደሚሉት ጆርጅ ዋሽንግተንን የአሜሪካ ንጉሥ ለማድረግ ብዙዎች አስበው ነበር፤ እሱ ግን ለስምንት ዓመት የረዥም ጊዜ የሚያንገሸግሽ የጦርነት ትግል ላይ ስለኖረ በነገሥታት ሕግ እና ሥርዓት ፤ ባህል እና የልማድ ሰንሰለት መታሠርን አልፈለገም ። በብሪታንያ ንጉሥ ተብሎ የሚጠራውን እና ጠቅላይ ሚኒስትር የሚባለውን በአንድ ላይ አድርጎ ፕሬዚዳንት መባልን መረጠ ። ፕሬዚዳንት

Fifty-two of the fifty-five founders of the Constitution were members of the established Orthodox Churches in the colonies. (**Toby Mac & Michael Tait** *Under God* p.154, USA 2004)

[78] **George Sullivan** MR. *PRESIDENT A Book of U.S.A Presidents., p., 21*

የሚባለውም የመሪዎች መጠሪያ የተጀመረው በዚሁ በጆርጅ ዋሽንግተን ጊዜ ነው። በአሜሪካ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚባል ነገር የለም። በጣም ታዋቂ የነበሩ ኹለት የሚረዱት ሰዎች መረጠ ። እነዚህም የመጀመሪያው የአገር ግዛት ሚኒስትር አድርጎ የሾመው ቶማስ ጃፈርሰን ሲኾን ሌላው ደግሞ የገንዘብ ሚኒስትር አድርጎ የሾመው አሌክሳንደር ሀሚልተንን ነበር ። በመቀጠልም በሚያዚያ 30 ቀን 1789 ታላቁ ፍርድ ቤት (ሱፕሪም ኮርት) ተመሠረተ ። የውጭ ጉዳይ ምኒስተር ፣ የጦር ሚኒስተር፣ የፖስታ ቤት እና የፕሬዘዳንቱ ዓቃቤ ሕግ (አተሮንሪይ ጀነራል ዲፓርትመንት) ተመሠረተ። በፓርላማ ምትክ ኰንግረስ ካፒቶል ሲተካ በቤተ መግሥት ቦታ ደግሞ ዋይት ሀውስ ተተካ ማለት ነው።

ጆርጅ ዋሽንግተን ቀደም ብሎ መንፈሳዊ ተጓዦች የእንግሊዝ ሰፋሪዎች ወደ ዐዲሲቷ ዓለም በመጡ ጊዜ የመሠረቱት ዕለተ አኰቴት (ታንክስ ጊቪንግ) የኅዳር ወር የመጨረሻው ሐሙስ በኅዳር 26 ቀን 1789 እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የሕዝብ የበዓል ቀን ይኹን በማለት በአሜሪካ በቋሚነት በየዓመቱ እንዲከበር አደረገ።

### (፬) የሕገ መንግሥቱ መረቀቅ

በ1787 የተጀመረው ሕገ መንግሥት (CONSTITUTION) መረቀቅ ከኹለት ዓመታት በኋላ መጋቢት 4 ቀን 1789 ጸደቀ። ኹሉም ባርያ አሳዳሪዎች ስለነበሩ በዚህ ሕገ መንግሥት በመጨረሻው ዕለት ታላቁ መነጋገሪያቸው የነበረው ባርያ ነጻ ማውጣት አለበት ወይም የለበትም የሚለው ጉዳይ ነበር።[80] ይህ ጉዳይ የጉባኤው ተሰብሳቢዎችን ያስፈራ ታላቅ የመነጋገሪያ አርእስት ነበር ። በዚህ ጉዳይ ብዙ ክርክር እና ጭቅጭቅ ተደርጓል ፤ ቤንጃሚን ፍራንክሊን አጥብቆ ሲከራከር ።

> ሰውን በባርነት መያዝ ስሕተት ስለኾነ አገራችንን በሰማይ ቤት ለፍርድ ያቀርባታል ይል ነበር ።

ይህ አቀራረቡ የብዙዎችን አመለካከት ለውጧል ። ከፊላደልፊያው ስብሰባ በኋላ ሚኒስትሮች ሀሚልተንን “ለምን ሕገ መንግሥቱ የእግዚአብሔርን ስም ወይም የክርስቲያንን እምነት አልተጠቀሰበትም ሲሉት” መልሱ “ረሳነው ነበር ያላቸው”[81] ቶማስ ጃፈርሰንን አንዳንድ የክርስትና ቡድኖች ሕገ መንግሥቱን ግልጽ እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ ሕገ

[80] **Warren J. H. & William L. K.** *American Majorities & Minorities p., 31*

[81] **Gary De Mar.**, *p., 13*



መንግሥቱ ቤተ ክርስቲያንን እና የመንግሥትን አስተዳደር የሚለይ ግርግዳ ነው። በማለት መለሰላቸው።[82] ቀደም ሲል እንዳየነው ይህ አንዱ የካልቪን አስተሳሰብ ነው ። ቶማስ ጃፈርሰን በጆን ካልቪን ትምህርት ተመርኩዞ ሃይማኖትና መንግሥት መለያየት አለበት የሚለውን ሐሳብ ይደግፍ ነበር።

ሕገ መንግሥቱ መንፈሳዊነትን የሚቃወም መንፈስ የለውም። እግዚአብሔር የለም አይልም ፤ የክርስትና ሃይማኖትን የሚቃወም አይደለም ፤ ይህ ቢኾን ኖሮ ኹሉንም ያበጣብጥ ነበር። የኰንግረሱ አባላት ከተለያየ የክርስትና እምነት የተሰባሰቡ አማንያን ነበሩ። ኮንግርጌሽናሊስት፣ ኤጲስኮፓል፣ ዳች ሪፎርምድ፣ ፕርስቤቴሪያን፣ ኳከር፣ ሉተራን፣ ዩኒቴርያን የሮማ ካቶሊክ እና ሜቴዲስት በኰንግረሱ ውስጥ ተባብረው ይሰሩ ነበር ። የማንኛውንም የክርስትና አመለካከት ያላሰፈሩት በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን አመለካከት የሐሳብ ልዩነት እንዳይኖር እንዳያለያያቸው በመፍራት የተደረገ ይኾናል የሚልም አስተያየት አለ።

ለምሳሌ ቶማስ ጃፈርሰን የአንግሊካን ኤጲስኮፓል እምነት ተከታይ የነበረ ሲኾን በኋላ አመለካከቱ ተለውጦ የዩኒቴሪያን ሐሳብ እንደተቀበለ ይነገራል። ይህ እምነት በምስጢረ ሥላሴ ላይ የተለየ አስተሳሰብ እና አመለካከት ነበረው። ስለዚህ በሕገ መንግሥቱ ውስጥ የእግዚአብሔርን ስም ለመጥቀስ ተቸግሮ ነው የሚል አመለካከትም አለ ። ሌላው አመለካከት ደግሞ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የቅኝ ገዢው የብሪታንያ መንግሥት በጊዜው ብዙ ተከታይ ያለው ዋና ሃይማኖት ስለነበረ አኹንም ከነጻነት በኋላ የበላይነቱን እንዳይዝ በመፍራት ሲባል የተደረገ ሊኾን ይችላል።

በሃይማኖት እና በኅብረተ ሰብ ጥናት እንደሚታየው በዓለም ላይ ያሉ አገሮች ኹሉ መንግሥታቱ ከአገሪቱ እምነት ጋራ የተቆራኙ ናቸው ። ለምሳሌ ራሽያን ብንወስድ የአገሪቱ ሕዝብ አብዛኛው ክፍል እምነቱ የኦርቶዶክስ ክርስትና ስለኾነ ኦርቶዶክስን ይደግፋል ። እንግሊዝ ፤ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያንን ። ኢትዮጵያ፤ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ። ህንድ፤ የሂንዱ ሃይማኖትን ። ግብፅ የእስልምና ሃይማኖትን ። እስራኤል የአይሁድ ሃይማኖትን ። ጀርመን የሉ

[82] **Jeffrey B. Webb,** *the complete Idiot's Guide to Christianity (New York 2004) p., 45*

ተር የክርስትና ሃይማኖትን። ሳውዲ ዐረብያ የእስልምና ሃይማኖትን። አሜሪካ ግን ይህ እንዳይኾን የሃይማኖት ነጻነት እንዲኖር በሕግ ተደንገገ ። በተዘዋዋሪ ግን አሜሪካ የተሐድሶ ፕሮቴስታንት የጆን ካልቪን የክርስትና እምነት ተከታይ ናት። ይህ በመኾኑ ምንም እንኳ የሃይማኖት ነጻነት ቢባል ከክርስትና ውጭ የእስልምና ፣ የሂንዱ የሌሎችም ከክርስትና ውጭ የኾኑ ሃይማኖቶች ውስጥ ተከታይ የነበሩ ለአሜሪካ አገር መሪ ፕሬዚዳንትነት ተመርጦ አይታወቅም ። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አገሮች ዋና ሃይማኖታቸው እንደ አሜሪካ ሕግ ላይ ሳይሰፍር በተዘዋዋሪ ከመንግሥት ጋር ግንኙነት አላቸው፤ እንደዚሁ ኹሉ ምሳሌ ብንወስድ ሳወዲ ዐረብያ የክርስቲያን መንግሥት ወይም መሪ (ንጉሥ) ይኖራታል ብሎ ማሰብ የማይኾን ነገር ነው።

ጆን ካልቪን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመተዳደር ከአገሩ መንግሥት ጋር እንድትሠራ ወይም ሃይማኖት እና አገር መለያየት አለበት በማለት ጽፎ አስተምሯል ፤ በነገሥታትም የማያምን ነው። በመጀመሪያም ከእንግሊዝ ተጉዘው በአሜሪካ የሰፈሩት ፒሩታንስ የጆን ካልቪንን ሐሳብ የያዙ ነበሩ ። እነዚህም የብሪታንያን ነገሥታትን የተቃወሙ ናቸው ። ነገር ግን ስለነገሥታት በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። ይህም ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጋር ሲያከራክራቸው የቆየ ጉዳይ ነበር ። ለምሳሌ

> የሳባ ንግሥት በእግዚአብሔር ስም የወጣለትን የንጉሥ ሰሎሞንን ዝና በሰማች ጊዜ በእንቆቅልሽ ትፈትነው ዘንድ መጣች። (መጽ. ነገ. ቀዳ.10)
>
> የመሳሰለው አንዱ መከራከሪያ ይኾናል።

በአኹኑ ጊዜ የንግሥና ሥርዓት ብሪታንያ እና በአንዳንድ የአውሮፓ አገሮች እንዲሁ በእስካንዲኔቪያን አገሮች በክብር ተጠብቆ ይገኛል። ይህ የነገሥታት ባህልና ሥርዓት ያመለጣቸው አሜሪካኖች የብሪታንያን የነገሥታት ቤተሰቦችን እንደ ብርቅ ያዩዋቸዋል ። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያም ንጉሠ ነገሥት እንደ ብርቅ ይታዩ ነበር።

ከላይ እንደተገለጸው ጆን ካልቪን ቤተ ክርስቲያን ራሷን ችላ በመተዳደር ከአገሩ መንግሥት ጋር እንድትሠራ ወይም ሃይማኖት እና አገር መለያየት አለበት በማለት ስለጻፈ ፤ የካልቪንን መመሪያ የተቀበሉት አሜሪካውያን መሥራቾች ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሃይማኖትን ወይም የፈጣሪን ስም በቀጥታ ላለማስገባት ሞክረዋል። በሕገ መንግሥቱ ውስጥ እግዚአብሔር ተብሎ አይገለጽ እንጂ ሃይማኖታዊ



ቃላት አሉበት ። ሕገ መንግሥቱ እንደ መጽሐፈ አስቴር እና እንደ መሐልየ ማሕልይ ዘሰሎሞን ዓይነት ነው ብለው አንዳንዶች ያምናሉ፤

አንዳንዶችም ደግሞ የሚሰጡት ሐሳብ ሕገ መንግሥቱ በፍሪሜሶነሪ[83] እምነት ላይ የተመሠረተ ነው ይላሉ ፤ በሌላ በኩል ሕገ መንግሥቱ ዐሠርቱ ቃላተ ኦሪትን የሚጠቁሙ ሕግጋት በውስጡ ሰፍረዋል ። ለምሳሌ የሰንበት ቀን ዕረፍት፣ ሰድብን፣ እናት አባትን ማክበር፣ አትግደልን፣ አታመንዝርን፣ አትስረቅን፣ በሐሰት አትምስክርን ፤ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ እና የሕገ መንግሥቱ ማጠቃለያ ዓመተ እግዚአ ( IN THE YEAR OF THE LORD) የሚለውን የዐሠርቱ ቃላተ ኦሪት ሕግ በተዘዋዋሪ በውስጡ መኖሩን የሚገልጽ ቃላቶች ያሉበት ሕገ መንግሥት እንደኾነ ይነገራሉ።

ይህ ሕገ መንግሥት ከተጀመረ ከ1783 በኋላ ካሉት የፕሮቴስታንት ቡድኖች ሜቶዲስት እምነት በፍጥነት በጣም መስፋፋት ጀመረ። በአሜሪካ ያለው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን (አንግሊካን) በጣም እየተዳከመ መጣ፤ በአሜሪካ ውስጥ የአንግሊካንን ቤተ ክርስቲያን ስሙን መጥራት እንኳን ጠሉት። በ1789 ስሙን ቀይሮ ለማደስተሞከረ ፡ ወደፊት እንደምናየው የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ፕሮቴስታንት ኤጲስኮፓል ተብሎ በአሜሪካ እና በእስኮትላንድ ይጠራ ጀመር።

በዐዲሲቷ ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ ፡ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ መንግሥት ጣልቃ ከገባ ነጻ አትኾንም ስለዚህ ማንኛውም ሃይማኖት በራሱ ጥረት ያለ መንግሥት ርዳታ እና ጣልቃ ገብነት ነጻ ኾኖ ራሱን መቻል አለበት የሚለው የሕገ መንግሥቱ መርሆ ብዙዎች የፕሮቴስታንት የክርስትና ቡድኖች እንዲስፋፉ ልቅ አደረገው ። የአሜሪካ መንግሥት በተዘዋዋሪ የክርስትና ሃይማኖትን ይደግፋል። በይበልጥም የፕሮቴስታንት የክርስትና እምነትን ይደግፋል ። ስለዚህ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን በነጻነት የፈለገውን እምነት ለማምለክ በራሱ ሐሳብ እንደ ንግድ ቤት በመክፈት እምነቱን ያስፋፋል ፤ በዚህም ከፍተኛ ውድድር ይደረጋል።

ዛሬ በአሜሪካ "ትድናለህ! ና ወደኔ" እንጂ ኃጢአት ስለሠራህ ትኰነናለህ ወይም ገሀነመ እሳት ትገባለህ ተብሎ አብዛኛው የፕሮቴስታንት ቡድን አይሰብከም። ምንም ይሥራ ምንም ያድርግ ኢየሱስ ይወድሃል ወደዚህ ቅረብ የሚለው የመስበኪያ ዘዴ እንደባህል ኾኗል። ይህ

---

83 (Freemasonry)

ኹሉ የስብከት ጥንቃቄ አንዱ እና ዋነኛ ምክንያት የገንዘብ ገቢውም እንዳይቋረጥ ይመስላል።

የአሜሪካንን ሕገ መንግሥቱን ያረቀቁት እና የተፈራረሙት የአሜሪካ መሥራቾች ሃምሳ ዐምስት ናቸው ። እነዚህን መሥራች ሰዎች አሜሪካውያን አባቶቻችን ናቸው በማለት በአክብሮት ዘወትር ስማቸውን ያነሳሉ።[84] የአሜሪካ ሕገ መንግሥት ተረቆ ሲጸፍ የግለሰብ መብቶች አልተጠቀሱበትም ነበር። ስለዚህ ተጨማሪ የመብት ሕጎች ተዘጋጁ ።

## (፭) የመብት ሕግ መረቀቅ

ከመጀመሪያው ሕገ መንግሥት (CONSTITUTION) በተጨማሪ መሠረታዊ የኾኑ በቁጥር 10 የሚደርሱ የመብት ሕግ (BILL OF RIGHTS) የተባሉት ለመጀመሪያ ጊዜ በታኅሣሥ 15 ቀን 1791 ተዘጋጅተው እና ተሻሽለው ወጡ ። ይህ የዜጎች የመብት ሕግ በከበርቴዎች ዘንድ በባርነት ለሚሰቃዩት ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጠው ውጤት ብዙ ባይኾንም፤ ወደፊት እንደምናየው ለእርስ በእርስ የትግል ጦርነት ግን መነሻ ኾኗል።

ይህ የዜጎች የመብት ሕግ እያንዳንዱ ግለሰብ መብቱን እና ነጻነቱን የሚያስከብር ሲኾን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው።[85]

1. የሃይማኖት ነጻነት፥ በነጻነት የሃይማኖት መጽሐፍትን ማሳተም፥ በነጻነት የመናገር ፤ የነጻ ጋዜጦች የማሳተም (የሕትመት) ፤ ሰላማዊ የስብሰባ ጉባኤዎችን ማካሄድ ፥ በኅብረት ወይም በግል አምልኮ ማድረግን እና መንግሥት እንዲለወጥ የመጠየቅ መበት።
2. የራስ የኾነ መሣሪያ ገዝቶ የመያዝ መብት፤ ይህም በሕግ የተፈቀደበት ደረጃ ድረስ።
3. መንግሥት በግቢ ውስጥም ኾነ በቤት ውስጥ ያለ ባለቤቱ ፈቃድ መግባት እንዲሁ ፖሊሶችም ኾኑ ወታደሮች ብጥብጥ ሳይኖር በሰላማዊ ጊዜ ያለምንም ስምምነት በዜጋዎች ቤት መገኘት እንደማይኖርባቸው የተሰጠ መብት።

[84] Jeffrey B. Webb,, *p., 119*

[85] *The new Encyclopedia Britannica 2002 10 P 68.*



4. ያለምንም መረጃ እና ማስጠንቀቂያ መንግሥት ያንድን ግለሰብ ንብረት መፈተሽ፣ አልያም መውሰድ፣ መሻት እንደሌለበት የተሰጠ መብት።
5. አንድ ሰው በአንድ ወንጀል ኹለት ጊዜ ለምርመራ ሊቀርብ ወይም በራሱ ላይ እንዲመሰክር መደረግ የማይኖርበት መኾኑን የተሰጠ መብት።
6. አንድ ሰው ወንጀል ቢፈጽምና ቢፈረድበት በድጋሚ ጠበቃ በመያዝ በዳኝነት እንዲታይለት የማድረግ መብት።
7. ጉዳዮች በዳኛ የሚመረመሩ መኾኑን።
8. ከልክ ያለፈ ያለምንም ምክንያት ሕዝብን ያለ መከላከያ መቅጣት ወይም ጭካኔ መፈጸምን።
9. ከሕገ መንግሥቱ በላይ ሕዝቦች መብት እንደላቸው።
10. በሕገ መንግሥቱ እንዲሁም በሕዝብ ውሳኔ ካልኾነ በስተቀር የፌዴራል መንግሥት ምንም ኀይል የሌለው መኾኑን።

ይህ ሕግ ዐሥር የኾነበት ምክንያት እግዚአብሔር ለሙሴ ዐሠርቱን ትእዛዛት በመስጠት ሕዝበ እግዚአብሔር የተባሉትን እስራኤላውያን ያስተዳደረበት ሕግ ስለኾነ በእሱ ምሳሌነት የተዘጋጀ ነበር።

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘጸአት የተጻፈ የዐሠርቱ ትእዛዛት ሕግ (ኦሪ. ዘጸ. 20) ዛሬ በአሜሪካ አገር በየግዛቱ (እስቴቱ) በሐውልት ላይ ተቀርጾ በየደባባዩ እና በከተሞች በአዳራሽ ግድግዳዎች ላይ ሳይቀር ተስጦ ይገኛል ። በተጠናው ጥናት ወደ 4000 ሺ የሚደርሱ ዐሥሩቱ ቃላተ ኦሪት የተጻፈባቸው ሐውልቶች በአሜሪካ በየመዝናኛ ቦታ (ፓርክ) እንዲሁም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግቢ ውስጥ ይገኛሉ።[86]

በዚህ በኦሪት ዘጸአት በተጻፈው ዐሥርቱ ቃላት ምሳሌነት ይህ የመብት ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘጋጀ ተብሎ ይታመናል ። ማሻሻል እንደሚቻል በመገለጹ በየጊዜው እንዳስፈላጊነቱ እየታየ ሲሻሻል እና ሲጨመርበት ኖሯል። ከመጀመሪያው ዐሥር አንቀጽ ተነስቶ ዛሬ ወደ 27 በመድረስ ዐዲስ የመብት ሕግ እየተጨመረበት ተበራክቷል። ይኼም ሕግ ሲሻሻል ሲጨመርበት በመጨረሻ በፊርማው የሚያጸድቀው የአገሪቱ ፕሬዚዳንቱ ነው።

[86] Gary De Mar., *p.*, 72


## (፮) የነጻነቱ አዳራሽ

የነጻነቱ አዳራሽ የታነጸው ከ1732 እስከ 1756 ባለው ጊዜ ነው። መጀመሪያ ይህ ቤት የተሠራው ለፔንሲልቫኒያ ለአገር ግዛቱ አዳራሽ እንዲኾን ታስቦ ነበር።

ይህ የአዳራሽ ሕንጻ ከአሜሪካ ካሉት ሕንጻዎች በዘመኑ ትልቅ ሕንጻ ነበር።[87] ነገር ግን በኋላ ቀስ እያለ የአሜሪካውያን የነጻነት አዳራሽ በመባል ተሰየመ። ማለትም ስብሰባ የሚሰበሰቡበት እና የመጀመሪያ የነጻነት አዋጅ እንዲታወጅ የተፈራረሙበት ፤ ሕገ መንግሥቱ የጸደቀበት ፤ ዳኝነት የታየበት፤ አሜሪካ ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ ተብሎ የአሜሪካ ልደት ቀን የተጀመረበት ፤ ጆርጅ ዋሽንግተን እና ጆን አደምስ ለፕሬዚዳንትነት የተመረጡበት አዳራሽ ነው።



የነጻነቱ ደወል



የነጻነቱ አዳራሽ

## (፯) የነጻነቱ ደወል

"በምድሪቱም ለሚኖሩባት ኹሉ ነጻነትን ታውጃላችኹ"
(ኦሪ. ዘሌ. 25፥10)

ይህ የነጻነት ደወል በቅዱስ መጽሐፍ በኦሪት ዘሌዋውያን የሰፈረውን ቃል መሠረት ያደረገ ነው።

[87] Edward M. Riley Startin *America The story of independence Hall., p., 6*



ይህ የፖለቲካ የነጻነት ደወል ለአሜሪካውያን የአገር ወዳድነት እና የነጻነት ክብር የተጐናጸፉበት የአዋጁ ምልክት ነው። ይህ ደወል አሜሪካ የገባው ከብሪታንያ ከእንግሊዝ አገር ነው ። የብሪታንያ መንግሥት በፊላደልፊያ የሕግ ምክር ቤት (ካፒቶል) ሕንጻ ለማሠራት ሲያስቡ ለዚህ ሕንጻ ደወል እንዲዘጋጅ ከብሪታንያ መንግሥት ለዋይት ቻፕል የደወል ኩባንያ ትእዛዝ ተላለፎ የተሠራ ነው ። ከዚያም ከብሪታንያ ከእንግሊዝ አገር ተጓጉዞ አሜሪካ ከደረሰ በኋላ ብዙ ሳይጠቀሙበት ለመጀመሪያ ጊዜ በሐምሌ 4 ቀን 1776 የነጻነት አዋጁ ለሕዝብ እንዲነበብ ሲወሰን ሕዝቦችን ለመጥራት እና ለማሰባሰብ ተደወለ።[88] ይህ ደወል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የነጻነት ደወል የሚል ስያሜ አገኘ ። በአሜሪካውያን ዘንድ በጣም ብርቅ ኾኖ የሚታይ የነጻነት ምልክት ነው። እሱን ለማየት በዓመት ውስጥ ወደ ሦስት ሚልዮን የሚጠጉ አሜሪካውያንና ሌሎች አገር ጎብኝዎች ወደ ፊላደልፊያ ይጓዛሉ።

## (፰) የአሜሪካ ባንዲራ

የአሜሪካ ባንዲራ የነጻነት ጦርነቱ ሲያበቃ የውሕደቱ የነጻነት ምልክት ኾኖ በግልጽ የታየበትና የተገለጸበት ቀን ሰኔ 14 ቀን 1777 ነው ። በዚያን ጊዜ 13 ኮከብ፥ 13 ሰረዝሲኾን 7 ቀይ 6 ነጭ አግድም ተደባልቆ የታየበት ጊዜ ነው ። እነዚህም ምልክቶች የሚገልጹት ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ ነጻ የወጡ ግዛቶች (ስቴት) የሚያሳዩ ናቸው። ከመጀመሪያዎቹ 13 ኮከቦች ዐዳዲስ ሌላ ኮከቦች በየዘመኑ እየተጨመሩ ዛሬ ባንዲራው ላይ ያሉት 50 ኮከቦች በመኾን ተበራክተዋል። ይህ የሚያመለክተው-የአሜሪካ ግዛቶችን (እስቴት) የሚወክሉ መኾናቸውን ነው።

የባንዲራው ቀለም ቀይ፣ ነጭ እና ሰማያዊ ነው። ትርጉሙም ነጭ ንጽሕናን፤ ሰማያዊው ፍርድን፤ ቀይ ደግሞ ጀግንነትን የሚያመለክት ነው ። ይህም በጦርነቱ ለተዋደቁት ጀግኖች መሥዋዕትነት የተከፈለበት የመታሰቢያ ምልክት እንዲኾን ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ከዚህም በላይ የሕዝቦቹ መለያ "በእግዚአብሔር እናምናለን"[89] የሚል መፈክር በባንዲራው ጀርባ ላይ አለ።

ባንዲራ ሲሰቀል የታወቀውን የእናት አገር የባንዲራ መዝሙር ሲዘምሩ ሕዝቡ እንዲሁም ከተማሪዎች ጀምሮ እስከ ፕሬዚዳንት ያሉት ቀኝ እጃቸውን ደረታቸው ላይ አድርገው "በአንድ እግዚአብ

[88] Stephanie Abraham H., *p., 328*
[89] IN GOD WE TRUST

ሔር ሥር የሚተዳደር ሕዝብ"[90] (ONE NATION UNDER GOD) የሚለውን ጨምረው ይዘምራሉ ። ይህ የተጨመረው በሰኔ 14 ቀን 1954 ፕሬዚዳንት ዲዋይት አይዘናሀወር ባንዲራ ሲሰቀል በካፒቶል ሕንጻ ደረጃ ላይ ቆሞ "አንድ እግዚአብሔር ሥር የሚተዳደር ሕዝብ" ብሎ በመዘመር ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ እንዲጸድቅ አደረገ።[91]

## (፱) የአሜሪካ ማኅተም እና ገንዘብ (ዶላሩ)

የማኅተሙን ቅርጽ ያቀነባበሩት በ1782 የፊላዳልፊያው ጠበቃ ዊልያም ቦርተን እንዲሁ የኮንግረንሱ ጸሐፊ ቻርለስ ቶምሶን ናቸው ። ራሱ መላጣ የኾነ ንሥር አሞራ (Bald Eagle)[92] አንዱ የነጻነት ምልክት ነው። ይህ አሞራ የሚገኘው በሰሜን አሜሪካ ብቻ ሲኾን የሚመገበው የባሕር አሣ ነው። ይህ አሞራ በማኅተሙ ላይ 13 የወይራ ቀንበጥ በቀኝ እግሩ ጨብጦ ፤ 13 ቀስት በግራ እግሩ ጨብጦ ፤ ደረቱ ተገልጦ ተቀርጿ ይታያል ። የወይራው ቀንበጥ የሰላም ምልክት ሲኾን፥ የቀስቶቹ ምልክት ደግሞ ዩናይትድ እስቴት ለራሷ ተከላካይ እንደኾነች የሚያመለክት ነው ፤ በአናቱ ላይም 13 የንጉሥ ዳዊት የኮከብ ምልክቶች አሉ።

በገንዘቡ (ዶላሩ) ላይ ፒራሚድ በወንዝ አጠገብ እንዳለ ኾኖ ተስሎ ይታያል ። ይህም አሜሪካ ጠንካራ ኾና ራሷን ችላ እንደምትቆም የሚያመለክት ነው። በ13 የድንጋይ ማዕዘን የተሳለው ፒራሚድ አናት ላይ ያለው ዐይን ደግሞ አሜሪካ በእግዚአብሔር እንደምትመበቅ የሚያመለክት ነው። ሌላም ብዙ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተገናኘ ትርጉም አለው ። ይህም አሜሪካ በእምነት ላይ የተመሠረተ መንግሥት ያላት መኾኑን ያመለክታል። ይኽ ታላቁ ማኅተም[93] የሚባለውን እርግማ የነደፈ የፍሬምሶነሪ እምነት ሐሳብ እንዳለበት የሚነገርለት ቤንጃሚን ፍራንክሊን ነው ይባላል ። የዚህ እምነት ተከታዮች "የሚታየው ፍጥረተ ዓለም ታላቅ የኾነ ቀያሽ አለው"[94] ብለው የሚያምኑ

[90] **Stephanie Abraham H.**, *p., 331*
[91] **Gary De Mar.**, *p., 56*
[92] **Stephanie Abraham H.**, *p., 128*
[93] The Great Seal
[94] 'the Great Architect of the Universe'



ናቸው ። በዶላሩ ላይ በዕብራይስጥ የመዝሙረ ዳዊት ጥቅስ (YAM YAWCHOD) ተጽፎ ይገኛል ።

> ትርጒሙም፥ ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፥ እነሆ ያማረ ነው፤ የሚል ነው።
> (መዝሙር 132(133))

ከነጻነቱ በኋላ በቀኝ አገዛዝ ሥር ከነበሩት 13ቱ ግዛቶች ሌላ ተጨማሪ ግዛቶች ከምዕራቡ እና ከደቡቡ መሬት እየጨመሩ መስፋፋት ጀመሩ። ከሜሪላንድ እና ከቨርጂንያ በፖቶሚክ ወንዝ አጠገብ ቦታ ተወስዶ የመንግሥት አስተዳደሩ እና የፕሬዚዳንቱ መኖሪያ ዋይት ሀውስ ተመሠረተ። ቀጥሎም የካፒቶል መሠረት መስከረም 18 ቀን 1793 ተጣለ፤ በዚህ ጊዜ በበዐሉ ላይ ምስጢራዊ የኾነውን የሜሶነሪ ምልክት ያለበትን የነሐስ ሽርጥ (Masonc aprone)[95] ፕሬዚዳንት ዋሽንግተን ለበሰ ። ይህም የለበሰው ልብስ ከላይ እንደተገለጸው በዶላሩ ላይ ይታያል ። ምንም እንኳን በፈጣሪ ላይ እምነት ቢኖረውም ይህም ከላይ የተገለጸው ምስጢራዊ አሠራር ከክርስትና እምነት ውጭ የኾነ አስተሳሰብ ላይ ስለተመሠረተ የርኩስ መንፈስ ያለበት ነው በማለት በተለይ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች አጥብቀው ይቃወሙታል ። ይህ የአሜሪካ ዶላር ከተገለጸው በላይ የተወሳሰበ ምስጢራዊ ምልክቶች አሉት።

ጆርጅ ዋሽንግተን ዋና ከተማዋን ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ (D.C.) የሚል ስያሜ ሰጣት። ይህም ስም የተሰየመው አገሪቷን በመጀመሪያ ባገኛት በጣልያኑ መርከበኛ በክርስቶፎር ኮለምበስ ስም ነው።

ጆርጅ ዋሽንግተን አገሪቷን ለኹለት ጊዜ የምርጫ ዙር ለስምንት ዓመት አስተዳደረ። በድጋሚ ሦስተኛ ዙር እንዲመራ ቢጠየቅ እኔ ሽምግያለኹ እና ከእንግዲህ በኋላ ደግሞ ሌላ ከእኔ ወጣት የኾነ አገሪቷን ያስተዳድር አለ። የአስተዳደር ጊዜ ለዐራት ዓመት እንዲኾን በሕጕ እንዲደነገግ አደረገ።

ማንኛውም ፕሬዚዳንት ለኹለተኛ ዙር ድጋሚ እንዲያገለግል ከተመረጠ ለስምንት ዓመት ብቻ አገልግሎ ሌላውን ዙር መቀጠል እንደሌለበት ገለጸ። በነዚህ ዓመታቶች፣ ብሔራዊ ባንክ፣ የፖስታ አገልግሎት፤ በኒው ዮርክ የወታደር ማሠልጠኛ (የሚሊተሪ አካዳሚ) እና ሌሎችንም መሠረተ።

[95] **Masonic**= conception of God as the "Architect of the Universe"

ጆርጅ ዋሽንግተን ለአሜሪካ ብዙ ሥራ ከሠራ በኋላ በመጨረሻ ማውንት ቨርን በሚባል በአደገበት የእርሻ ቦታ በ1799 ዐረፈ ። ለመታሰቢያው በቆመው ሐውልት ላይ በሚታየው በብረቱ ቆብ ጫፍ "ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው" የሚል ተጽፎበታል።[96] ዛሬ የእሱን መኖሪያ የነበረውን ቤት እንዲሁም የመቃብሩን ቦታ ለመጎብኘት ብዙ አውሮፓውያንና አሜሪካውያን ጐብኝዎች ወደ ማውንት ቨርን ይጓዛሉ።

አሜሪካውያን እነዚኽን ነጻ ያወጧቸውን ሰዎች የአሜሪካ መሥራች አባቶቻቸው እንደኾኑ እና እንደሚወዷቸው ይናገራሉ ፤ ስለእነሱም ታላቅነት ዘወትር በተገኘው አጋጣሚ ይናገራሉ። በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ታላላቅ የመታሰቢያ ሐውልቶች አቁመውላቸዋል ። የፕሬዚዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን መታሰቢያ ሐውልት እና ምስል በአሜሪካ ምድር የሌለበት ከተማ የለም። ከዚያም በላይ ከሃምሳ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ በምዕራቡ ክፍል ከካናዳ ጋር የሚዋሰነውን ቦታ የዋሽንግተን ግዛት ብለው በስሙ ሰይመውለታል። ዋናውን የመንግሥት ከተማም ዋሽንግተን ዲስትሪክት ኦፍ ኮለምብያ በምህፃረ ቃል ዲ.ሲ. ተብሎ ይጠራል።

## (፲) ፪ኛው ፕሬዘዳንት ጆን አደምስ (ኮንግርጌሽናል)

ከፕሬዘዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን ቀጥሎ የተመረጠው ጆን አደምስ ነው። ይህም ሰው በጣም ሃይማኖተኛ የኮንግርጌሽናል ወይም የፒዩሪታንስ እምነት ተከታይ ነበር። በኋላ ግን በቦስተን ባለው የኮንግርጌሽናል ሰባኪ አማካኝነት ስለዩኒቴርያን በተሰበከ ጊዜ የዩኒቴርያን እምነት አመለካከት አደረበት።

ጆን አደምስ የታወቀ ጠበቃ ነበር ። ለነጻነቱ ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የተወለደው በሪየንሬ ወይም ኩንሲ ማሣቹሴትስ እየተባለ በሚጠራ ቦታ ነበር ። በሀርቫርድ ዩንቨርሲቲ በ1755 በሕግ ተመርቆ ብዙ ተግባሮች አካኺዷል። ስለባርያዎች ነጻነት የምትታገለውን ሚስቱን አቢጋኤልን በ1764 አገባ ። በ1765 አደምስ የአሜሪካ ቅኝ ገዢ ክፍል የሚያስከፍለው የቀረጥ ሕግ (እስታምፕ አክት) ባለመደገፍ ተቃዋሚዎች ከኾኑት ጋር በመተባበር ብሶቱን አሰምቷል ። ከ5 ዓመት በኋላ በቦስተን ከብሪታንያ ወታደሮች ጋራ አለመግባባት ሲፈጠር እሱም ዋናው ተቃዋሚ ነበር ። በማሣቹሴትስ ግዛት ተወክሎ በመ

[96] Harry Smith., *p., 83*



ጀመሪያውና በኹለተኛው የኰንግረስ ስብሰባ ላይ ተገኝቷል ። የነጻነት አዋጁን እና ሕጉን ካረቀቁት የኮሚቴ አባላት አንዱ ነበር ። በኋላም በጆርጅ ዋሽንግተን ሥር ምክትል ፕሬዘዳንት በመኾን ተመርጦ ነበር።[97]

በ1789 እና በ1792 የጆርጅ ዋሽንግተን ካቢኔት ሲከፋፈል ጆን አደምስ እና አሌክሳንደር ሀሚልተን ፌደራሊስት በመኾን ሪፑብሊካን የኾነውን ቶማስ ጄፈርሰንን የሚቃወም ነበር።

ጆን አደምስ በኒው ኢንግላንድ የኮንግሬሽናል (ፒዩሪታንስ) የክርስትና እምነት ተከታይ እና መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር የሚያጠና እንደነበር ይታወቃል። ይኽም ጥናቱ ለአስተዳደሩ እና ፕሬዚዳንት ኾኖ የመሪነት ቦታውን ሲይዝ ረድቶታል፤ ለዚህም የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ፤

> አቅሜ ብቃቴ ዕውቀቴና ጊዜዬ በሚፈቅድልኝ መጠን ኹሉ በትንሹ አእምሮዬ ብዙ መጽሐፍትን መርምሬያለሁ ለማለት እደፍራለሁ ። ከኹሉም ይበልጥ የተረዳሁት ግን መጽሐፍ ቅዱስን የሚወዳደር ሌላ አንድም መጽሐፍ ያለማንበቤን ነው ይላል።

ጆን አደምስ የነጻነት አዋጅ ያወጁበትን ሃምሳኛ ዓመት በሚከበርበት ቀን ሐምሌ 4 ቀን 1826 ቶማስ ጄፈርሰን ከዐረፈ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ተከትሎ በደቂቃ ልዩነት በሚኖሩበት ቦታ ኾነው ኹለቱም የነጻነት ታጋዮች ዐርፈዋል።

## (፲፩) ፫ኛው ፕሬዚዳንት ቶማስ ጄፈርሰን (ኤጲስኮፓል)

ሦስተኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የኾነው ቶማስ ጄፈርሰን ነው ። ይህ ሰው የከበርቴዎች ልጅ ነበር ። የተማረውም ዊልያም ኮሌጅና ሜሪ ኮሌጅ ነው። የተዋጣለት ጠበቃ፣ ገበሬ፣ መሐንዲስ፣ ሙዚቀኛ፣ ዐዲስ ሐሳብ የሚያፈልቅ፣ ሳይንቲስት፣ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ፤ የብዙ ነገሮች አጠቃላይ ዕውቀት ያለው፤ ላቲን እና ግሪክን ጨምሮ ስድስት ቋንቋዎችን መናገር የሚችል ሰው ነበር ። ይህንም ችሎታ ሊያገኝ የቻለው በልጅነቱ በጣም አንባቢና ጎበዝ ተማሪ ኾኖ ስላደገ ነው ። በ17 ዓመት ዕድሜው ኮሌጅ ሲገባ በየቀኑ 15 ሰዓት ትምህርቱን ያለማቋረጥ ያጠና ነበር ። በዚህም የተዋጣለት የሕግ ባለሙያ ኾነ።

[97] George Sullivan., *p., 25 - 30*

ቶማስ ጃፈርሰን በ1772 ማርታ ዌይሌስን አግብቶ ልጆች ወልዷል ። ነገር ግን ከዐሥር ዓመት የጋብቻ ኑሯቸው በኋላ ይህቺ የሕግሚስቱ ሞታበታለች።

ቶማስ ጃፈርሰን ሐምሌ 4 ቀን 1775 በፊላዳልፊያ የኹለተኛው ኰንግረስ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ከብሪታንያ የቅኝ አገዛዝ የተላቀቁበት የነጻነት አዋጅ የመጀመሪያውን ረቂቅ እንዲያረቁ ከተመረጡት አንዱ ነው። የነጻነት አዋጁን በሚያረቁበት ጊዜ በአርቃቂዎቹ የኮሚቴው መሪ እንዲኾን ተመርጦ ነበር ። ኹሉም የሰው ዘር እኩል ነው የሚለውን ሐሳቡን በአዋጁ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ አንዱ የኮሚቴ አባል ነው ። የኹለተኛው ፕሬዚዳንት የጆን አደምስ ምክትል ፕሬዘዳንት ኾኖም አገልግሏል።

ቶማስ ጃፈርሰን በ1801 ሦስተኛ የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ኾኖ ሲመረጥ ባለቤቱ ከሞተች 19 ዓመት በኋላ ነበር። ስለዚህ በፕሬዘዳንት መኖሪያ ቤት ብቻውን ሲኖር ዳውሊ ማዲሰን በኋላ የዐራተኛው ፕሬዘዳንት ሚስት የኾነችው ቤት ልጁ ትረዳው ነበር ። በአገሪቱ ውስጥ የሃይማኖት ነጻነት ፤ ነጻ የማንበቢያ መጽሐፍት ቤት፤ የነጻ ትምህርት ቤት እንዲኖር አዋጅ አሳውጇል።

ፕሬዘዳንት ኾኖ በተሾመበት ዘመን የምዕራቡ የአሜሪካ ክፍል ከሚሲሲፒ ወንዝ ወደ ቋጥኝ የበዛበት ተራራማ ቦታ ያለውን፤ ፈረንሳይ በጦርነት ኢንዲያኖችን እያስለቀቀች በቅኝ አገዛዝ የያዘችውን ሠፊ የጫካ እና የእርሻ መሬት ወደ ፈረንሳዩ ንጉሥ ወደ ናፖሊዮን ዲፕሎማት ቤንጃሚን ፍራንክሊን እና ሀሚልተንን ልኮ ከሉዚያና ጀምሮ ያለውን ቦታ በ1803 በ$15 ሚልዮን ዶላር ገዛው ። ይህ የግዛት ቦታ የፈረንሳይን አገር ዐምስት እጥፍ የሚኾን ነበር ። ከዚያም በ1808 በኰንግረስ የባርያ ንግድን ወደ አገሪቷ ማስገባትን እንዲቆም አስወሰነ።

ፕሬዘዳንት ቶማስ ጃፈርሰን ከዐመፁ በፊት በቅኝ ግዛት በነበሩ ጊዜ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ወክሎ ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድር ነበር። በክርስትና እምነት አመለካከቱ ስለምስጢረ ሥላሴ መረዳት ስላልቻል ወደ ዩኒቴሪያን አስተሳሰብ ተወሰደ። ይህም ማለት ምስጢረ ሥላሴ የማይቀበል እምነት ነው ። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን አስተያየት ሲገልጽ ግን እንዲህ ይላል ፡

**ብዙ ጊዜ ደጋግሜ የተናገርኩትና ወደፊትም የምናገረው መልእክት አለኝ። መጽሐፍ ቅዱስ ዜጎችን በሙሉ ቀና ያደርጋል ፤**



**ባሎችን የተሻሉ ጨዋና ከኹሉም በላይ ደግሞ ጨዋ አባት እንዲኾኑ ይረዳቸዋል።**

ቶማስ ጀፈርሰን በሞንቶኪሎ ወይም ትንሿ ተራራ እየተባለች የምትጠራ ቦታ ከቤተሰቡ የእርሻ መሬትና ከእርሻው መሬት ጋር 187 ባርያዎች አብሮ ወርሶ ነበር ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህች የመጀመሪያ ሚስቱ ስትሞት የሚስቱን ጥቁር አገልጋይ እኅት የኾነችውን ሳሊ ሄሚንገስን የምትባለውን ወሸሞ ከዚህች ጥቁር ሴት ዐምስት ልጆችን ወለደ ። ይህች ሴት እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ለ44 ዓመት ካጠገቡ ያል ተለየች ነበረች። እነዚህን ከጋብቻ ውጪ ከጥቁር የተወለዱ ልጆች ዐምስት ልጆች (ዲቃላዎች) ነጻ እንዲወጡ ተናዞላቸዋል ። ምናልባት በነጻነት አዋጁ "ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩልነት ነው።"[98] ብሎ ያረቀቀውና የባርያ ንግድን እንዲቆም ያሳወጀው አዋጅ ከጥቁር ጋር ባለው የጠበቀ ግንኙነትና ልጆቹንም ጭምር ነጻ ለማውጣት ሊኾን ይችላል የሚል አስተሳሰብ አለ።

ሐምሌ 4 ቀን 1776 እስከ 1826 ከብሪታንያ ቅኝ አገዛዝ ነጻ የወጡበት 50 ኛው ዓመት የሚከበርበት ቀን ነበር። በዚህ ቀን 2ኛ እና 3ኛ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመኾን ያገለገሉ ጓደኛሞች ከላይ የተገለጸው ጆን አድመስ እና ቶማስ ጃፈርሰን ነጻነት ባወጁበት ሐምሌ 4 ቀን በሚኖሩበት የትውልድ ቦታቸው እና የመኖሪያ ቤታቸው ኾነው በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ተከታትለው ዕንዳረፉ ተሰማ ። ይህ ተከታትለው ማረፋቸው አስደናቂ ገጠመኝ ነው ። በዋሽንግተን ዲ.ሲ. በቆመለት የመታሰቢያ ሐውልቱ ላይ "ሕይወትን የሰጠን እግዚአብሔር ነጻነትንም ሰጠን" የሚል ተጽፎበታ።

## (፲፪) ፬ኛው ፕሬዘዳንት ጀምስ ማዲሰን (ኤጲስኮፓል)

ጀምስ ማዲሰን (1751 – 1836) ፖርት ኮንዌ ተብሎ በሚጠራ ቨርጂንያ ግዛት ተወለደ። የኮሌጅ ትምህርቱን የተማረው ኒው ጀርሲ ነው። በቨርጂንያ በተለያዩ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አገልግሏል ። ፕሬዚዳንት ከመኾኑ በፊት የፕሬዚዳንት ቶማስ ጃፈርሰን የአገር ግዛት ሚኒስትር (የእስቴት ሴክረታሪ) በመኾን አገልግሏል።"[99]

[98] Harry Smith., *p., 82*
[99] Harry Smith., *p., 84*

በ1812–14 ባሉት ኹለት ዓመታት ውስጥ የብሪታንያ መርከቦች ከአትላንቲክ ውቅያኖስ ጨርሰው ሳይወጡ ተቆጣጥረውት ይኖሩ ነበር። ይህም የአሜሪካንን የንግድ ወደቦች በመያዝ መፈናፈኛ ለማሳጣት የታሰበ ጉዳይ ነበር ። በዚህ ጊዜ ኰንግረስ በብሪታንያ ላይ ጦርነትን አወጀ፤ ካናዳን ለመያዝ ሙከራ አደረጉ ። ብሪታንያ እና ፈረንሳዮች የአሜሪካ መርከብን ተዋግተው ያዙ ። ከዚያም የእንግሊዝ የጦር መርከብ በፖቶሚክ ወንዝ በኩል ገብተው የመንግሥት አስተዳደር ከተማዋን ሊይዙ ተቃረቡ ፤ በዚህ ጊዜ ይህ ዐራተኛው ፕሬዚዳንት ጀምስ ማዲሰን ከባለቤቱ ከዶውሊ (የሦስተኛው ፕሬዚዳንት የቶማስ ጀፈርሰን ሴት ልጅ) ጋራ ለሽሽት ተዘጋጁ ። ዶውሊ ጠቃሚ የኾኑትን ነገሮችን እና የጆርጅ ዋሽንግተን የተከበረ የሥዕል ፎቶግራፉን ሌሎቹንም የተከበሩ ንብረቶች አስጭና ወደ ቨርጂንያ ጫካ ለመሰወር ሸሹ ። በፖቶሚክ ወንዝ የመጣው የብሪታንያ ጦር ዋና ከተማዋን ዋሽንግተን ዲሲን ያዘ። የፕሬዚዳንቱን መኖሪያ ቤት ዋይት ሀውስና የኰንግረስ መሰብሰቢያ ካፒቶልን በጦርነቱ ወቅት ለመበቀል ሲሉ አቃጠሉት።

ከአትላንቲክ በፖቶሚክ ወንዝ የመጣው የብሪታንያ ጦር ውሎ አድሮ በአሜሪካውያኑ ጦር ድል ተመትተው ወጡ። ጦርነቱ ከተፈጸመ በኋላ ፕሬዚዳንቱና ባለቤቱ ከሽሽት ተመለሱ። ነገር ግን የፕሬዚዳንት መኖሪያ ቤታቸው ተቃጥሎ አገኙት ። እስከ ሚታደስና እስከሚሠራ ጊዜያዊ ቤት ተሰጥቷቸው መኖር ጀመሩ ። የፕሬዚዳንቱ መኖሪያ በቃጠሎ ጠቁር መልኩና ውበቱ ጠፍቶ ነበር። ቀስ እያለ እየተለወጠ በነጭ ቀለም ሲቀባ ጥቁረቱ ጠፍቶ የደመቀ ነጭ ኾኖ አማረ ፤ እድሳቱ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ዳውሊ እና አሜሪካውያን በጉጉት ይጠብቁት ነበር። በየጊዜው ብቅ እያለች ስታይ የነበረች የፕሬዘዳንቱ ሚስት ዳውሊ አንድ ቀን ኹሉም ነጭ ኾኖ አየች፤ ቤታችን ነጭ ኾነ ለማለት "ዋይት ሀውስ" አለችው ። ስኞ የወጣ ስም ማክሰኞም ተከተለና የፕሬዘዳንቱ መኖሪያ ቤት ዋይት ሀውስ እንደተባለ ቀረ።[100]

## (፲፫) ፭ኛው ፕሬዚዳንት ጀምስ ሞንሮ (ኢ.ኢ.ስኮፓል)

ጀምስ ሞንሮ የተወለደው ሚያዚያ 28 ቀን 1758 በቨርጂንያ ነው ። ቤተሰቦቹ በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባል ኾነው ያገለግሉ ስለነበር

[100] George Sullivan., *2001*



እሱም በነሱ እግር ባለማቋረጥ በአገልግሎቱ ይካፈል ነበር ። በቨርጂንያ አገልጋይ ባርያዎች እና የእርሻ ቦታም ነበራቸው።

ጀምስ ሞንሮ በዊልያም እና በሜሪ ኮሌጅ ገብቶ ትምህርቱን አጥንቷል። ከዚያም በጄኔራል ዋሽንግተን የወታደር ጦር ማሠልጠኛ በኒው ዮርክ ገብቶ ከዋሽንግተን ጋራ በመኾን በብራንድወይን ፣ በጀርመን ታውን እና ሞንሞንት ላይ ከቅኝ ገዢው ብሪታንያ መንግሥት ጋር በነበረው የነጻነት ጦርነት ዋና የጦር መሪ በመኾን አገልግሏል ። በጦርነቱ ጊዜ የ18 ዓመት ወጣት ነበር ። ከዐመፁ በኋላ የሕግ ትምህርት ከቶማስ ጀፈርሰን አጥንቶ ወደ ፖለቲካው ገባ ። ከዚያም ለሴናተር ምርጫ ተወዳድሮ አሸንፎ ተመረጠ ። በመቀጠልም የፈረንሳይ ሚኒስትር በመኾን ከፈረንሳይ ጋር ሉዊዚያናን ለመግዛት ድርድር ከገጠሙት አንዱ ነበር። ለቨርጂኒያ የጠቅላይ ግዛቱ አስተዳዳሪ በመኾን ኹለት ጊዜ ተመርጦ አገልግሏል ። የነበረው ሙያ ወታደር ፣ ጠበቃ ፣ ኰንግረስ ፣ ሴናተር ፣ አገረ ገዢ (ገቨርነር) ፣ ዲፕሎማት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር (ፎሬይን ሴክሬተሪ) ኾኖ አገልግሏል ።

በመጨረሻ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት በ1816 ተመረጠ ። በድጋሚ በ1820 ለኹለተኛ ጊዜ ተመርጦ አገልግሏል ። የተሳካለት ፕሬዚዳንት በመኾን ስፓኝ ተይዞ የነበረውን እንዲኹም ይጓጉለት የነበረውን የደቡብንና የመካከለኛውን የአሜሪካ ክፍል ነጻ እንዲወጡ አድርጓል። ከዚህ በኋላ ነው ዐዲሲቱ ዓለም ከአውሮፓውያኑ ቅኝ ገዢዎች እጅ ሙሉ በሙሉ ነጻ መኾናቸውን ያወጀው። በዚህም ድርጊት ሚሲሲፒ፣ ኢሊኖኒስ ፣ ፍሎሪዳ፣ አላባማ፣ ሜይን፣ ሚዙሪ ፣ በስሩ እንዲጠቃለሉ ያደረገ ፕሬዚዳንት ነው።

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን የከፋፈለው የባርነት ሥርዓት መፍትሄ ይኾናል በማለት በ1821 ጥቁሮችን ወደ አፍሪካ ምድር መልሷል ። እነዚህም ወደ አፍሪካ የተመለሱት አሜሪካ ያገለግሉ ይሰቃዩ የነበሩት ጥቁሮች (ባርያዎች) ላይቤሪያ የምትባለውን አገር መሠረቱ ዋና ከተማዋንም በዚሁ ፕሬዚዳንት ጀምስ ሞንሮ ስም ሞንሮቪያ ብለው ሰየሙ ። ላይቤሪያ ያሉት የእርሻ ማሳዎች እንደ ደቡብ የአሜሪካ ክፍል ምርት ባለመስጠታቸው ባሪያዎችን መልሶ ወደ አፍሪካ መላኩም አልቀጠለም ቆመ ።

## (፲፬) ፮ኛው ፕሬዚዳንት ጆን ኩንሲ አደምስ (ዩኒቴሪያን)

ጆን ኩንሲ አደምስ ፕሬዚዳንት ልጅ ፕሬዚዳንት ሲኾን የመጀመሪያው ነበር ። አባቱ ኹለተኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበረ ጆን አደምስ ነው ። ጆን ኩንሲ አደምስ የተወለደው ሐምሌ 11 ቀን 1767 በብሬን ትሬ፥ ማሣቹሴትስ ነው ። በሐርቫርድ ዩንቨርሲቲ እንደ አባቱ የጠበቃነት ሙያ ተምሯል ። ሴናተር ፣ የአገሪቷ ዋና ጸሐፊ ፤ የኰንግረስ አባል በመኾን አገልግሏል ። ከ፭ኛው ፕሬዘዳንት ጀምስ ማንሮ ሥር በመኾን በእስፓኝና በብሪታንያ ተይዞ የነበረውን ቀሪ ቦታ በስምምነት ወደ ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ እንዲጠቃለሉ አድርጓል ።

ጆን ኩንሲ አደምስ የተረጋጋ ሕይወት ነበረው ። ኹል ጊዜ ከመኝታው የሚነሳው ሊነጋ ሲል በ11 ሰዓት (5 a.m.) ላይ ነው ። ከተነሳ በኋላ ውጭ ወጥቶ እሳቱን ያቀጣጥልና መጽሐፍ ቅዱሱን ቁጭ ብሎ ማንበብና መጸለይ ይጀምራል ። ማንም ሰው ከእንቅልፉ ሳይነቃ በዋይት ሀውስ አጠገብ በሚያልፈው ፖቶሚክ ወንዝ ኼዶ ልብሱን አውልቆ ይታጠባል። አንድ ቀን ወደመኻል ገብቶ ሲታጠብ ሌባ ልብሱን ይዞበት እየሮጠ ኼደ ። ፕሬዚዳንቱ ቆየት ብሎ አንድ ወጣት ልጅ በውሃው ዳር ሲያልፍ አይቶት ጠርቶት በሩጫ ወደ ቤተ መንግሥቱ ወደ ዋይት ሀውስ ኺድ እና አቶ አደምስ የሚለብሰው ልብስ ይፈልጋል ብለህ አምጣልኝ አለው ። ልጁም ኼዶ ለባለሟሎቹ ነግሮ ልብሱንም አመጡለት።[101] ጆን ኩንሲ አደምስ ዘወትር ስለሚያነበውና ጠቃሚ ምክር ስለሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ የምስክርነት ቃል ሲሰጥ እንዲህ ይል ነበር።

> በዓለም ላይ ከሚኖሩት ሰዎች አንዱ ነኝና እኔም በተራዬ በዓለም ላይ እየኖሩ ላሉት ሰዎች ኹሉ የማስተላልፈው መልክት አለኝ። መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ትጉ። በየትኛውም የዕድሜ ክልልም ኾነ በምንም አይነት ኹኔታ ብትኾኑ ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ተነቦ የሚያበቃ አይደለምና አንብቡት ይላል።

ጆን ኩንሲ አደምስ የባርነት አገዛዝን አይደግፍም ። ለኹለተኛ ጊዜ በ1828 ለአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ተወዳድሮ በአንድረው ጃክሰን ተሸነፈ ። ከእሱ ቀጥሎ የተመረጠው ፕሬዚዳንት አንድረው ጃክሰን የፐር

[101] George Sullivan., *2001*



ስቤተርያን አማኝ የነበረ ሲኾን ይህ ሰው ዛሬ በአሜሪካ $20 ዶላር ላይ የፎቶ ምስሉ የሚገኘው ነው።

ጆን ኩንሲ አደምስ በመጨረሻ በደም ብዛት (ስትሮክ) ድንገት ተይዞ በታመመ በኹለተኛው ቀን በ80 ዓመቱ በ1848 ዐረፈ።

## (፲፭) ቤንጃሚን ፍራንክሊን (ኤጲስቆፓል)

ቤንጃሚን ፍራንክሊን በአሜሪካ የፕሬዚዳንትነት ቦታ ይዞ አልመራም ። ነገር ግን በሚንስትርነት ሰርቷል ። በጣም የሚያስገርም ታላቅና አስደናቂ ችሎታ የነበረው ለአሜሪካ የነጻነት የዐመፅ ትግል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ እንዲሁም የነጻነት አዋጁ ላይ እና ሕገ መንግሥቱ ላይ ከፈረሙት አንዱ ነው ። ከእንግሊዝ ጋራ ጦርነቱ ሲያበቃ የሰላም ስምምነት እንዲደረግ አድርጓል ፤ ወደ ፈረንሳዩ ንጉሥ ናፖልዮን በቶማስ ጃፈርሰን አማካኝነት ተልኮ የምዕራቡን ክፍል ለመግዛት ድርድር አድርጓል።

ቤንጃሚን የተወለደው ከችግረኛ ቤተሰብ ሲኾን ዐሥራ አምስተኛው ልጅ ነው። የትውልድ ቦታው ቦስተን ማሣቹሰትስ ነው ። ወላጆቹ ከእንግሊዝ አገር ወደ አሜሪካ በ1683 የተሰደዱ ናቸው ። ቤንጃሚን በ12 ዓመት ዕድሜው በወንድሙ የመጽሐፍ ማተሚያ ቤት ይሠራ ነበር ። ወንድሙ ጀምስ መጽሐፍ አታሚ ነበር፤ ይህንንም የመጽሐፍ የማተም ሥራ አስተማረው። ለሚሠራበት የጉልበቱ ዋጋ ልብስ ፣ ምግብና መኖሪያውን ይችለው ነበር ። በዚህ ኹኔታ ለዐምስት ዓመት ሠራ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ብዙ ዕውቀት አግኝቶ በ17 ዓመት ዕድሜ ሌሎች በትምህርት ቤት ገብተው ተምረው ከሚያገኙት የበለጠ ዕውቀት አገኘ፡፡ በ24 ዓመቱ የራሱ የኾነ የማተሚያ ቤት ከፈተ።

ከዚህ በኋላ በፊላደልፊያ የታወቀ ጋዜጣ አታሚና የተከበረ የንግድ ሰው ኾነ ። በነጻነቱ አዋጅ ላይ ከፈረሙት አንዱ ነው ። የብሪታንያ ቅኝ ገዢው መንግሥት ዐመፅ ያመፁበትን ኹሉ በስቅላት ይቀጣ ነበረ ። በነጻነቱ አዋጅ ላይ 55 ሰዎች ሲፈራረሙ የተናገረው ንግግር "ከተሰቀልን በአንድ ላይ ኹላችንም እንሰቀል፤ አለበለዚያ ብቻችንን እንሰቀል" አለ ይባላል።

ቤንጃሚን ፍራንክሊን የአሜሪካ ኑሮ የሚሻሻልበትን መንገድ ለመፈለግ የተለያዩ ሙከራዎችን ያደርግ ነበር ። የመብራት ችግርን ለማስወገድ እንዲሁም በቀዝቃዛው የበረዶ ወራት ዘመናዊ ምድጃ

እንዲኖርና ቤቶች ውስጥ ሙቀት እንዲኖራቸው ጥረት አድርጓል ። በ1748 ስለኤሌክትሪክ ምርምር ስላደረገ የኤልክትሪክ መብራት የመጀመሪያው ፈልሳፊ ዝነኛ ሳይንቲስት ኾኗል።[102]

ቤንጃሚን ፍራንክሊን በአሜሪካ በጣም የተከበረና ታላቅ ዝና ያለው ሰው ነው።

ሕይወቱን በሙሉ የባርነት ሥርዓትን ለማስቀረት ታግሏል ። በዕድሜው መጨረሻ ላይ ኹለቱን አገልጋይ ባርያዎች ነጻ አድርጓቸዋል ። ቀደም ሲል ተገልጸ እንደነበርው የአሜሪካውያን የነጻነት ትግል የባርነትንም ሥርዓት ለማስወገድ መንገድ ከፍቷል።

## ምዕራፍ ፰
## ጥቁር አሜሪካውያን

**እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ... ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ባረካቸው።**
**(ዘፍ. 1፥27)**

እግዚአብሔር በአርአያው የፈጠረውን ፥ የባረከውን የሰው ዘር ፤ በቀለም፣ በጎሳ ፣ የተነሳ በኦሮው ተሻሽያለሁ ፤ በዕውቀት በሀብት በልጽጌ አለሁ ፤ የተመረጠ ዘር ነኝ ብሎ መለየት ኃጢአት ነው።

ነጭ የቀለም ዘር በቀለሙ የተለየውን የጥቁር ዘር እንደ ዕቃ በመቁጠር ኢሰብአዊ የኾነ የግፍ ግፍ ሲፈጽምበት ኖሯል። የባርነት ሥርዓት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አሳፋሪ የኾነ ምዕራፍ አለው ። ስለ ዚህም በአሜሪካ የዘር ፣ የቀለም አድልኦ እና ግፍ መፈጸም ተገቢ አይደለም የሚሉ በመነሳታቸው ዘረኞቹ መካከል መከፋፈልን ፈጠረ። ይህም መከፋፈል ለእርስ በእርስ ጦርነት እንዲዳረጉ አደረጋቸው። ይህም ጦርነት ለአሜሪካ የታሪክ ጠባሳ ትቶ አልፏል።

የባርነት ሥርዓት ለአሜሪካ ሕገ መንግሥቱ ለተጀመረው የዲሞክራሲ መንፈስ፤ ለማኅበራዊ ኑሮ እና ለፖለቲካ የዕድገት እንቅፋት እና መርዝ ኾኖ ሲያበጣብጥ ኖሯል። የአሜሪካ ነጻነት ከታወጀ በኋላ እስከ 1830 ድረስ 610,000 ባርያዎች ከቨርጂንያ ግዛት በባርነት አገልግሎት ላይ ነበሩ ። በጆርጅያና በሰሜን በደቡብ ካሮላይና እንዲሁም በዘጠኙ ግዛቶች ደግሞ 40,000 ባርያዎች ነበሩ። ቶማስ ጀፈርሰን

[102] **Harry Smith.**, *p., 85*



የባርያ ንግድን ሲከለክል በግዞት ሥር የነበረው የባርያ ቁጥር ከነዚህ ቁጥሮች እጥፍ ደርሶ ነበር።[103]

በሰሜኑ የአሜሪካ ክፍል የነበረው የብሪታንያ መንግሥት ቅኝ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ እንዲሁም ነጻነት ከታወጀ በኋላ የሠራተኛ የልፋት ዋጋ በትክክል ይታሰብ ነበር ። ኾኖም ግን አንድ ሀብታም ከበርቴ ከ20 ያላነሱ አገልጋዮች (ባርያዎች) ነበሩት። ባርያ ለመሸጥም ይኹን ለመግዛት የሚፈልግ ሀብታም ከበርቴ ወይም አትራፊ ነጋዴ ሁል ጊዜ በጋዜጣ ማስታወቂያ እንዲወጣለት ያደርጋል ። በተጠየቀው መሠረት ባርያ በቁጥር ተመዝግቦ እንዲሁም ከእርሻ መሬት ጋር ከነዋጋው ተተምኖ (LAND & NEGROES) ጫረታ (አክሽን) በማውጣት ለገበያ ይቀርብ ነበር።

በሰሜኑ ክፍል በ1794 ከባርነት ነጻነት የተሰጠው የሜተዲስቱ የጥቁር ሰባኪ ሪቻርድ አለን በፊላዳልፊያ ከነጮች ቤተ ክርስቲያን ተገንጥሎ በመውጣት ከጓደኞቹ ጋር የመጀመሪያውን የሜተዲስት ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ። ይኸን በተመለከተ ስለሜተዲስት የክርስትና ሃይማኖት በሚናገረው ክፍል በሰፊት እናየዋለን።

ቶማስ ጀፈርሰን የባርያን ንግድ እንዳስቆመ በኒው ዮርክ ከተማ በሀርለም የተወሰኑ ቡድኖች ተሰባስበው የዘር ልዩነትን በመቃወም ጥቂት የኒው ዮርክ ነጋዴ ኾነው ከገቡት ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር አቢሲንያ ባፕቲስት ቸርች በማለት የራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በ1808 መሠረቱ።[104] በኋላ ዘመን ይህን ታሪካዊ ቦታ የተለያዩ የአፍሪካ መሪዎች እና የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ጎብኝተውታል ። ከነዚህ ጎብኚዎች አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ይገኙበታል ። ንጉሠ ነገሥቱ ከጉብኝታቸውም በላይ ከፍተኛ ምታሰቢያም አበርክተዋል ።

ወንጌል እኩልነትን እና ነጻነትን ክርስቶስን ስለምትሰብክ አብዛኛው የባርያ አሳዳሪዎች ባርያዎች ስለክርስትና እንዲማሩ አይፈቅዱላቸውም። እንዲያውም ያስንፋቸዋል ፤ ሥራ እንዳይሠሩ ያደርጋቸዋል የሚል አመለካከት ነበራቸው ። አንዳንዶቹ ቀና አመለካከት ያላቸው የባርያ አሳዳሪዎች ደግሞ በድብቅ ያስተምሯቸዋል። በዚህ የተነሳ ጥቁሮች እስራኤላውያን ከግብፁ ፈርኦን የባርነት ቀንበር እግዚአብሔር በሙሴ መሪነት እንዴት ነጻ እንዳወጣቸው የሚያሳየውን ታሪክ ከጊዜ

[103] **Jackie Staddon.**, *p., 30.*
[104] The brief History of Abyssinian Baptist Church. WWW. Abyssinian.org

ወደ ጊዜ በደንብ እየተረዱ እና እያወቁ መጡ። ጥቁር ሰባኪዎች ከአ
ንዱ የእርሻ ቦታ ወደ ሌላው እርሻ ቦታ እየተደበቁ በመሰባሰብ ይሰ
ብኩ፣ ይጸልዩ፣ መዝሙር ይዘምሩ ነበር።

በዚህ ዘመን ሰማዕት ኾኖ ስለሞተው ሕዝቅኤል ስለሚባል አገ
ልጋይ (ባርያ) የሚነገር ታሪክ አለ ። የዚህን ሰው ታሪክ ምስክር ኾኖ
የተናገረው ሲላስ ጃክሰን የሚባል ሰው ነው ። ሲላስ የባፕቲስት ቤተ
ክርስቲያን አማኝ የኾነ የክበርቴ ቶማስ አሽቢ ባሮች ውስጥ ከነበሩት
አንዱ ነው። ሲላስ ከዘጠኝ ዓመት ዕድሜው ጀምሮ በጥጥ ፣ በትምባሆ
በስንዴ፣ የእርሻ ቦታ ማሣ ላይ ከሕዝቅኤል ጋራ ከበርቴውን አብረው
አገልግለዋል ፤ ሕዝቅኤል የደረሰበትን ታሪክ ያውቃል።

ሕዝቅኤል የቁልምጫ ስሙ ዜኪ ነው፤ ከሌሎች አገልጋዮች
ጋር ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ድረስ ያለምንም ዕረፍት ከጠዋት እስከ ማታ
በትምባሆ እርሻ አብረው ከሚያገለግሉት አንዱ ነው ። ከበርቴው
ቶማስ አሽቢ ጉማሬውን ይዞ ትንሽ ፈዘዝ ብሎ ሲያለምጥ ያየውን አገ
ልጋይ ባርያ ከግንድ ጋር ጥፍር አድርጎ በማሰር ተዝለፍልፎ እስከሚወ
ድቅ ድረስ ይገርፋል ወይም ደግሞ ሌላውን ባርያ በማዘዝ ያስገርፋል፤
ቅዳሜ ማታ ቀለባቸው ተሰፍሮ ይሰጣቸዋል ። እሑድ ቀን እሱ ወደ
ቤተ ክርስቲያኑ እና ወደ መዝናኛው ሲኼድ እነሱም ባለቻቸው የእረ
ፍት ጊዜ በጎጇቸው ተሰብስበው ሲጸልዩ፣ ሲዘምሩ አንዳንዴም ሲዝናኑ
ይውላሉ ። ዋናው አሰባሳቢ ሰባኪያቸው ይሄው ሕዝቅኤል ነው ።
በአንድ ወቅት እነዚህ አገልጋዮች ሲጸልዩ ከዚያም ሲነጋገሩ አሳዳሪው
ጌታቸው ቶማስ አሽቢ በቦታቸው ኼዶ ተደብቆ የሚነጋገሩትን ያዳም
ጣቸው ነበር ። ሕዝቅኤል የሚናገረውን እና የሚሰብከውን ሰማ ።
በማግስቱ ሕዝቅኤል ከእርሻ ቦታው ላይ ሲሠራ አልታየም ጠፋ ፤ ከጓ
ደኞቹ ተነጥሎ የት እንደገባ አልታወቀም ።

ከበርቴው ቶማስ አሽቢ በኋላ ጊዜ ዕድሜው ሸምግሎ ለሞት
ሲቃረብ በመጨነቅ የባፕቲስቱን የነጭ ቄስ አስጠራ ፤ ለቄሱም ወደ
ሲኦል መውረዴ ነው! ምን ይሻለኛል? በማለት የንሥሐ ኑዛዜውን ይና
ዘዝ ጀመር ። ዋናው አስጨናቂ ኃጢአቱም ሕዝቅኤልን በአሰቃቂ
ኹኔታ መግደሉ ነው። ቶማስ አሽቢ በጭካኔ ሲደበድበው ሕዝቅኤል
እየለመነው እንደ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ይጸልይለት ነበር።[105] ይህን
የመሳሰለው የጭካኔ ሥራ ብዙ ተፈጽሟል (የሐ. ሥራ 7፥54)።

---

[105] Albert J. Altschul, Wade in the River, the story of the African ch. Faith p.132



እንደሚታወቀው ፒዩሪታንስ እና ኳከር የክርስትና ሃይማኖት
ቡድኖች ከ17 ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የባርያ ሥርዐት (ከበርቴዎችን)
አጥብቀው ይቃወሙ ነበር ። ነገር ግን መንግሥትንና ሌሎችንም የሃይ
ማኖት መሪዎችን ስለሚመለከት ባርነትን ማላቀቅ አስቸጋሪ ኾነባቸው
ኖረ ። ኹል ጊዜ ከመናገር ወደ ኋላ ስላሉ በ1830 በሜሪላንድ እና
በቨርጂንያ የግል የባርያ ባላባቶች ባሮቻቸውን እንዲለቁ አደረጉ ።
እንደገና በ1850 በዋናው ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ በመንግሥት ትእዛዝ
የባርያ ንግድ እንዲቆም ተደረገ። ይህም አዋጅ የባርያ አሳዳሪዎችን
አላስደሰተም ነበር ።

> በዐሥሩ የኦሪት ትእዛዛት ውስጥ አንዱ "ጎረቤትህን (ወንድም
> ኽን) እንደራስህ አድርገህ ውደድ" ስለሚል ይህም ማለት ኔግ
> ሮው ጎረቤትህ መኾኑንን ዕወቅ ፤ እግዚአብሔር ሕዝቦቹን
> አንድ ደም አድርጎ ነው የፈጠራቸው ፤ ይህም ወንድምኽ
> ነው (ኦሪ..ዘሌ.19፥17)።[106]

በማለት የፒሩታንስ (የካልቪን ተከታዮች) መንፈሳዊ መሪዎች ይቃወሙ
ነበር ። ቀደም ባለው ጊዜ በብሪታንያ በቅኝ ገዢው መንግሥት እንዷ
ሁም በኅብረተሰቡ ተሰሚነት ነበራቸው። የባርያ ባለቤቶችም እነዚህን
የክርስቲያን እምነት ተከታዮች ያሳምፁብናል በማለት ይፈሩ ነበር።

የኹለተኛው የክርስትና እምነት የቅስቀሳ ዘመን (Great Awake
ning) ከፍተኛ የስብከት ወንጌል የተካኼደበት ከ1820 እስከ 1850
ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ ነው። ይህም ዘመን የድንኳን ውስጥ ስብሰባ
(ቴንት ሚቲንግ) የሚባለው የመሰባሰቢያ ዘዴ የተጀመረበት ጊዜ ነው ።
በዚህ ዘምን ታዋቂ የነበረውን የፕሬስብቴርያኑን ቻርለስ ፊኒይን ብዙ
ሰዎች ይከተሉት ነበር ። በስብከቱም አድማጭ እና ተከታይ የተነሳ
በኒው ዮርክ ከተማ የወንጀለኛ ቁጥር ቀንሶ እንደነበረ ይነገራል። በኒው
ዮርክ ከተማ ሐምሌ 4 ቀን 1827 የነጻነት በዓል በሚከበርበት ቀን ባር
ነት በሕግ መወገዱ ታወጀ።

ቀድሞ የነገረ መለኮት ተማሪ በኋላ ደግሞ ሥነ ፍጥረት
(የባዮሎጂ) ተማሪ የነበረ እንግሊዛዊው ቻርለስ ዳርዊን አዝጋሚ
ለውጥ (ኢቮልሽን) የሚለውን የፍልስፍና ሐሳቡን ይዞ በ1858 ብቅ
አለ። ቻርለስ ዳርዊን በጻፈው መጽሐፍ "ጠንካራው አሸንፎ ይኖራል"
በማለት ባወጣው የፍልስፍና ትንታኔ ብዙዎችን ከፋፈለ። ወደፊት እን

---

[106] **Lutz Norma Jean** *The History of the Black Church USA 2001 p., 12*

ደምናየው ዘረኝነት የተጠናወታቸው ኩ ክላክስ ክላን ነጭ ፍጥረት በተፈጥሮው የበላይ ነው ብለው በዘረኝነት በማመን የባርያውን ሥርዓት ትክክለኛነት ለማሳመን በማስረጃነት ይጠቀሙበት ነበር ። ይህንን ተቃዋሚ ክፍል ደግሞ የአሜሪካ መሥራቾች አባቶቻችን "ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩል ነው" ብለው ሕግ ቀርጸውልናል በማለት ሲከራከሩ ኖሩ።

ይህን የባርያ አገዛዝ የጭካኔ ሥራ በመቃወም የተነሳ ክርስቲያኖች "ማንኛውም የሰው ዘር በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ነው"። እንዲሁ የአሜሪካ የነጻነት አዋጅ እና ሕገ መንግሥት የተደነገገው በዓለማት ፈጣሪ በእግዚአብሔር እምነት ላይ እና በሰው ዘር ነጻነት ፣ እኩልነት ላይ ስለኾነ ሰውን ማሰቃየት ትክክል አይደለም በማለት የአቦሊሺኒስት ንቅናቄ ተመሠረተ።

## (፮) ባርነት መጥፋት አለበት (አቦሊሸኒስት)

> አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባርያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ኹላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁና። (ገላ. 3፥28)

አቦሊሸኒስት (ABOLITIONIST MOVEMENT) ባርነት የማፍ ሥርዓት ነው ። የሰው ዘር ልዩነት በሃይማኖትም ኾነ በሰበአዊነት ሚዛን ሲገመገም ስሕተት ነው። ስለዚህ ከምድረ ገጽ መጥፋት አለበት ብለው የሚያምኑ በሰሜኑ ክፍል የሚኖሩ ነጮች እንዲሁም ጥቁሮች የቤተ ክርስቲያን ሰባኪዎች የጀመሩት ንቅናቄ ነበር።

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች ሌሎችም ለጥቁር አሜሪካውያን ነጻነት እንዲገኝ ይሰበክ የነበረው ስብከት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በአሜሪካ በ1783 ሕገ መንግሥቱ ሲታወጅ "ኹሉም የሰው ዘር የተፈጠረው በእኩል እና በነጻነት ነው።" የሚለው የባርነት ሥርዓትን ለማስቀረት፤ የሰው ልጆች በምድር ላይ በነጻነት የመኖር መብትን እንዲኖር ታስቦ የተደነገገ ነው። ኾኖም ግን የባርነት ሥርዓቱን ለማስቆም ሙሉ ለሙሉ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ከቀድሞዎቹ ተቃዋሚዎች የመጀመሪያዋ የባርነት ሥርዓትን ተቃዋሚ የፕሬዚዳንት ጆን አደምስ ባለቤት አቢጋኤል አደምስ ነበረች እንዲሁም ቀደም ብለን እንዳየነው ታላቁ ቤንጃሚን ፍራንክሊን ተቃውሞ አሰምቶ ነበር ።



ሕገ መንግሥቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሰሜን ምሥራቁ አሜሪካ በኒው ኢንግላንድ በ1831 የባርነት ነጻ አውጭ ቡድን ተቋቋመ ፤ የዚህ የነጻነት አውጭው መሪ ዊልያም ሎይድ ይባል ነበር ። በፊላዳልፊያ እንዲሁም በደላዌር እንቅስቃሴው ቀጠለ።

በዚሁ ዘመን የባርነት ግፍ ያንገሸገሸው የባፕቲስት የወንጌል ሰባኪ ናታ ተርነር ከ16 ተከታዮቹ ጋራ በመኾን ሸፍቶ 60 ነጮችን ገደለ ። በኋላ ተይዞ በቅላት ተፈረደበት ። ይህ የባርነት ሥርዓት እንዲጠፋ በተግባር ጭምር የታገሉ የታወቁት ሰዎች ብዙዎች ነበሩ ። ከነዚህም መካከል በሮወን ዊልያም ዌልስ (1814-1884) ፍሬድሪክ ዳግላስ፤ ሀሪዬት ተብማን እና ሌሎችም በመተባበር እነዚህ በግፍ በባርነት የተያዙት ጥቁር አሜሪካውያን በአንዳንድ ሃይማኖተኛ ነጮች ጭምር እየተረዱ ከደቡብ ወደ ሰሜን በማስኮብለል እና በማሸሽ ተረዳድተዋል ። ይህ የማሸሽ ሥራ "አንደር ግራውንድ ሬይል ሮድ"[107] ወይም ባርያን የማስመለጥና ወደ ሰሜኑ ክፍል ለማስገባት የሚደረገው ስልት ነበር። ግፉ የመረራቸው ወደሰሜን መኮብለል ያልቻሉት አንዳንድ ጊዜም ወደ ደቡብ ሜክሲኮ ፣ ሀይቲ እና ካረቢያን ደሴቶች እየኮበለሉ ያመልጡ ነበር።

በዚህ ወቅት ታዋቂው "አንክል ቶም ካቢን"[108] የተባለ የጥቁሮችን ስቃይ የሚናገረው ታሪካዊ ልብ ወለድ መጽሐፍ በ1852 ተጻፈ። ጽሑፍን የደረሰችው ከነጭ አሜሪካውያን ዝርያ የነበረች የጥቁሮች መብት ተከራካሪ ሀሪዬት ቢቸር ነች ፤ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ዋና መነሻዋ የኾናት የደቡብ ከበርቴዎች የሚኮበልሉትን ወይም አምልጠው የሚኼዱትን ባርያዎች አሳደው በመያዝ ሲያሰቃዩዋቸው በማየቷ ነበር ። ድርሰቱ በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የተደረሰ ሲኾን፤ የመጽሐፉ ይዘት ለብዙዎች ጥቁሮች መሥዋዕት ኾኖ የተንገላታውን በኋላም በስቃይ የሞተውን የአንድ ጥቁር አገልጋይ ታሪክ የሚተርክ ነው። ይህ አንክል ቶም ካቢን የተሰኘው መጽሐፍ በመላው አሜሪካ በተሠራጨ ጊዜ ብዙዎች መጽሐፉን በመግዛት አነበቡት፤ ኹለት ሚልዮን አሜሪካውያን አንብበው ተቀሰቀሱበት። ባርነት ከአሜሪካ መጥፋት አለበት የሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስቃይ ከአንክል ቶም ድርሰት ጋር በማመሳሰል የተደረሰው ይህ የመቀስቀሻ

[107] Under Ground Rail Road
[108] Uncle Tom's Cabin

ጽሑፍ ብዙዎችን አነሳሳ ። ባርነት መቅረት አለበት የሚለው እንቅስቃሴ እንዲፋጠን አስተዋጽኦ አድርጓል።

ሀሪዬት ቢቸር በዚህ መጽሐፏ ዝናን አገኘች። በዘመኗ ታዋቂ ከተባሉት ሰዎች ጋር ተገናኝታለች። ከነዚህም ውስጥ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የኾነውን ለነጻነት የታገለውን አብርሃም ሊንከንን በ1862 አግኝታለች ፤ እሱም ይህን መጽሐፏን አንብቦ ኖሮ ፤ ስለመጽሐፏ በማንሳት "አንቺ ትንሽ ሴት ስትኾኚ የጻፍሽው መጽሐፍ ታላቅ ኾኖ ከፍተኛ ጦርነት አስነሳ" በማለት ገልጸላት ነበር።

## (፱) ፍሬድሪክ ዳግላስ

ሌላው የጥቁሮች መብት ተከራካሪ ፍሬድሪክ ዳግላስ ነበር።[109] ይህ ሰው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የጥቁሮች መብት ተከራካሪ በመኾን የባርነት ሥርዓት እንዲጠፋ ይታገል የነበረ የሰብአዊ መብት አባት ተብሎ የሚጠራ ነው።

ፍሬድሪክ ዳግላስ የተወለደው ከጥቁር ቤተሰብ ሲኾን አባቱ ማን እንደኾነ አያውቅም ፤ ትክክለኛ የኾነው የልደት ቀኑ አይታወቅም። ምክንያቱም ለጥቁሮች (ኔግሮ) የልደት ምሥክር ወረቀት በማይሰጥበት ዘመን ስለተወለደ ነው ። ማንበብና መጻፍ ለጥቁሮች ወንጀል በኾነበት ጊዜ በተገኘው አጋጣሚ ከሚቀባበሉት ጌቶቹ ቀስ እያለ ተምሯል። ፍሬድሪክ አን ሙርይ በምትባለው በኋላ ሚስቱ በኾነች ጥቁርሴት ተረድቶ ከጌቶቹ አምልጦ ኒው ዮርክ ግዛት ገባ ፤ ከዚያም እየተዘዋወረ የባርነት ሥርዓት ለሚቃወሙት ንግግር ያደርግ ነበር።

ፍሬድሪክ ዳግላስ “የሰሜኑ ኮከብ” የሚል ጋዜጣ በማዘጋጀት ጽሑፍ ያቀርብ ነበር። የሰሜኑ ኮከብ ምሳሌነቱ ከደቡቡ የእርሻ ቦታ የሚንገላቱትን ባርያዎች የሚያስኮበልሏቸው ሌሊት በጥሻ ውስጥ በማስመለጥ ሲጓዙ አቅጣጫ የሚመራ ኮንፓስ አልነበራቸውም ። እንደ ኮምፓስ የሚያገለግሏቸው በሰማይ ላይ የሚታዩት ሰባቱ የሰሜን ኮከቦች ነበሩ ። እነዚህ ኮከቦች በጠራ ሰማይ ላይ ያሉበትን ቦታ በማየት መሪ አድርገው በእኩለ ሌሊት በጥሻ ውስጥ እየተሽሎከለኩ ሲጓዙ ያድራሉ ። ቀን ቀን በጢሻ ውስጥ ተኝተው ይውላሉ ። ከዚያም ወደ ነጻው ፊላዳልፊያ፤ ወደሌሎቹ የሰሜን ግዛቶችና ካናዳ ይገቡ ነበር።[110]

[109] 1817 – 1895
[110] **Susan Altman.**, *p.,66*



ፍሬድሪክ ዳግላስ በአሥር ዓመት ውስጥ 400 ጥቁሮች ከአሳዳሪዎቻቸው ኮብልለው እንዲያመልጡ ረድቷል። ከአብርሃም ሊንከን ጋራ በዚሁ በባርያ የጭቆና ሥርዓት ጉዳይ ተገናኝቶ ተነጋግሯል ፤ እንዲህም ይል ነበር።

> ክርስትና የግብዞች አይደለም የእውነተኞች እንጂ።[111] ኔግሮን ካዳንክ ሕዝቦችን ታድናለህ፤ ኔግሮን ካጠፋህ ሕዝቦችን ታጠፋለህ ፤ ስለዚህ ኹለቱንም አድን ። ከኹሉ ታላቁ ሕግ ግን ነጻነት፣ እኩልነት፣ ለኹሉም አሜሪካኖች ይኹን።

ፍሬድሪክ ዳግላስ የካቲት 20 ቀን 1895 በልብ ድካም ሞተ።

## (፲) ሀሪዬት ተብማን

> የእስራኤል ልጆች ከባርነት የተነሳ አለቀሱ ፤ ጮኹም ስለባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ፤ እግዚአብሔርም የለቅሷቸውን ድምጽ ሰማ (ዘጸ. 2፥23)።

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው እስራኤላውያን በግብፃውያን በፈርኦን ለ400 መቶ ዓመታት በባርነት ተይዘው ይኖሩ ነበር ። በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ከወገናቸው የነጻነት መሪ የሚኾናቸው ሙሴን አስነሳ።

በአሜሪካ ለነዚህ ለሚሰቃዩት ባርያዎች (ኔግሮ) ተቆርቋሪ እና ተከራካሪ በመኾን ብዙዎች ተነስተው ነበር። ከነዚህ ውስጥ ታዋቂዋ ሀሪዬት ተበማን አንዷ ነች። ይህች ሴት ወገኖቿን ከስቃይ በማውጣት የረዳች ነቿ።[112]

ሀሪዬት ተወልዳ ያደገችው በሜሪላንድ ግዛት ነው። አሳዳሪዋ ጌታው ብሮዳስ የተባለ ሰው ነበር። ሦስቱን ወንድሞቿን እና እሷን ጨምሮ ለደቡብ ጆርጅያ የእርሻ ቦታ ባለአባቶች ሊሸጧቸው መኾኑን ሰማች። "ኧንደር ግራወንድ ሬይል ሮድ" የሚባለውን ወደ ሰሜን ማስመለጫ ዘዴ ትሰማ ነበረና ለመጥፋት ቆርጣ ተነሳች ። ወንድሞቿንም ከሷ ጋራ እንዲያመልጡ ለማሳመን ሞከረች ። የምትጠፋ መኾኗን ለሌሎቹ ቤተሰቦቿ አላማከረችም ፤ ከመሸጣቸው በፊት ማታውኑ ጉዞ ጀመሩ። ወንድሞቿን እየመራች በጥሻው ውስጥ ይዛ መጓዝ ጀመረች። የሜሪላንድ ጫካ በጣም ጭለማ ነው ። ወንድሞቿ ፈሩ ፤ ከተያዙ በጣም እንደሚገረፉ ፤ ከዚያም በላይ በደቡቡ አርቀው እንደሚሸጧ

[111] **Earle E. Cairns** *Christianity in the United States., p., 259*
[112] (1821 – 1913)

ቸው ፤ ብዙ መከራ እንደሚደርስባቸው አሰቡ ። ስለዚህ እኛ እንገ ዝም፤ እንቺም ብቻሽን አትኼጂም በማለት እምቢ አሏት ። "እኔ እኼዳለሁ ብቻዬን አይደለሁም እግዚአብሔር ከእኔ ጋራ ነው ፤ የሚ ገጥመኝም ቢኖር ነጻነት ወይም ሞት ነው።" በማለት ጉዞዋን ቀጠለች። ቀን ቀን ጢሻ ውስጥ እየተኛች ሌሊት ሌሊት እየተጓዘች የባርያ አስ መላጮቹም እየረዷት ጉዞዋን ቀጠለች ። በመጨረሻ ፊላዳልፊያ ደረ ሰች፤ በዚያም ነጻነቷን አገኘች። በፊላዳልፊያም እንደ ደረሰች ኑሮዋ ተስተካክሎ በደሞዝ ተቀጥራ መሥራት ጀመረች።

ሀሪዬት ተብማን ወደ ፔንሲልቫንያ ኼዳ ራሷን ከባርነት ነጻ ከወጣች በኋላ “አንደር ግራውንድ ሬይል ሮድ” ተብሎ በሚታወቀው የድብቅ የማመላለሻ ምስጢራዊ ዘዴዎች በመጠቀም ብዙዎች ወገኖ ቿን ወደሰላማዊውና ነጻነት ወዳለበት ሰሜኑ ክፍል ማውጣት አለብኝ ብላ ተነሳች።[113] የመጀመሪያው ጉዞዋን ያደረገችው ወደ አደገችበት ከተማ ቦልቲሞር ነበር ። በዚያም የእኅቶቿን ልጆች ፤ የአክስቶቿን ልጆች አንድ ወንድሟን ሌሎችንም አገልጋዮች አጓጉዛ ነጻ አወጣች። ከጊዜ ወደ ጊዜ የማስመለጥ ዘዴ ልምዱን አካበተች ። ጓደኞቿን እያ ስተባበረች ዋሻ ለዋሻ ፤ ጥሻ ለጥሻ እያሽሎከለከች ሳትፈራ እየደበ ቀች ወደሰላማዊ ቦታ በሰሜን በሚገኙ ግዛቶች እና ካናዳ ብዙዎች እን ዲወጡ አድርጋለች። 90 ጊዜ ተመላልሳ በደቡብ ክፍል ድረስ ወርዳ እያስመለጠች ነጻ አውጥታለች። ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን ይህ ጉዳይ የባ ርያ ባለአባቶችን አስቆጣ፤ አበሳጨ።

መንግሥት ባርያ ንግድ በ1850 ቢያስቆምም በጌቶቻቸው ሥር ያሉትን ባርያዎች እንዲያመልጡ መርዳት የሚያስቀጣ መኾኑን ገለጸ፤ ማንኛውም ሰው ባርያን በቤቱ አስጠግቶ ሲረዳ ቢገኝ ንብረቱና ቤቱ እንደሚወረስ ፤ የእርሻ ቦታውና ከብቶቹ እንደሚወረሱ ሕግ አወጣ ፤ ባርያ ሲያመልጥ የሚይዙና የሚሰልሉ ሰላዮች አዘጋጀ ። ሀሪዬት ይህን በደንብ ተረዳች። ነገር ግን የማስመለጫ ዘዴዎች ብዙ ነበራት። ከተያዙባት ለሌላው ማስተማሪያ ማስፈራሪያ እንዲኾኑ ጀርባቸው እስከሚተለተል እንደሚገረፉም ታውቃለች። ለዚህም ጥንቃቄ ታደርግ ነበር።

ሀሪዬት በአጠቃላይ ወደ 300 ሰዎችን በማውጣትዋ የደቡብ የባርያ ከበርቴ ባለርስቶች ተበሳጩ። በሜሪ ላንድ ግዛት በማስታወቂያ ሰሌዳ (ፖስተር) ላይ በኹሉም ቦታ ፎቶግራፏ ተለጥፎ እርሷን በሕ

[113] Susan Altman., *p., 256*



ይወትም ወይም ሞታም ይዞ ላቀረበ $40,000 ዶላር ሽልማት ለመስጠት በጋዜጣ ጭምር አወጡ።[114] ጊዜውም ከ1850 እስከ 1860 ነበር። ነገር ግን ማንም ሰው አላገኛትም ። በወገኖቿ የተሰጣት ቅጽል ስሟ ሙሴ ነበር። ይህም ማለት እንደተገለጸው ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከግብፅ ምድር ከባርነት ከጨካኙ ፈርኦን ነጻ ያወጣ መሪ ነበረ፤ እሷም ብዙዎ ችን ከስቃይ ከለቅሶ ሰላወጣች በሙሴ መሰሏት።

የባርነትን አገዛዝ የሚቃወመው አብርሃም ሊንከን፥ የዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ ፕሬዚደንት ኾኖ ከተመረጠ በኋላ ሀሪይት ተብ ማን የውሕደቱ ጦርነቱ ሲጀመር አገልግሎት እንድትሰጥ ተፈቀደላት። በመጀመሪያ ነርስ ኾና አገለገለች ከዚያም ለጦሩ ሰላይ በመኾን አገል ግላለች ። ከጦርነቱ በኋላ 48 ዓመት ኖራ ዕድሜ ጠግባ መጋቢት 10 ቀን 1913 በ93 ዓመቷ ሞተች።[115]

ይህ ሰውን በሰው መግዛት በሰብአዊነትም ይኹን በሃይማኖት አይደገፍም የተባለው የነጻ ማውጣት እንቅስቃሴ (አቦሊሽኒስት ሙቭ መንት) የመጀመሪያው የሰብአዊ መብት እንቅስቃሴ ተብሎ ይጠራል። በደቡብ ግዛት በሚፈጸመው ግፍ በሰሜኑ ያሉት ብዙዎች አይደሰቱም በጣም ብዙ ክርክሮች ተደረጉ ። በዚህም የተነሳ ከ1820 እስከ 1840 ድረስ ወደ 75,000 ሺህ የሚደርሱ በባርነት ቀንበር ውስጥ ይኖሩ የነ በሩ ጥቁሮች በድብቅ በተለያየ መንገድ አምልጠው ወደሰሜኑ ግዛቶች እና ካናዳ ገብተዋል ። ነገር ግን ገና ያልተለቀቁና ለቅሷቸው ያልቆመ ብዙዎች ነበሩ።

## መዕራፍ ፯
## ሰሜን እና ደቡብ የሕዝቦች ጦርነት

የፈርዖን ልብ ደነደነ ፤ ሕዝቡን ለመልቀቅ እምቢ አለ።
(ዘፀአ. 5 ፤ 7፥14)

በቅዱሱ መጽሐፍ ታሪክ እንደምንረዳው ፈርኦን እስራኤላውያን ባሮ ችን ለመልቀቅ ያልፈለገው ጡብ የሚሠራና ሌላውም የጉልበት ሥራ ይቆማል ብሎ በመፍራት ነው። የነዚህ አገልጋዮች ጉልበታቸውን እና ሥራቸውን ይፈልግ ስለነበር ትንሽ ከቦዘኑ አሠሪዎች በጣም አድርገው

[114] Harry Smith., *p., 151*
[115] PBS HOME VIDEO Alfre Woodard *Underground Railroad*